# በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም

# የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና ጥናት


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

በ

አንተነህ አየነው ዋለ


ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር የኤም ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ውስጥ ከፊሉን ለማሟላት የተዘጋጀ ጥናት፡፡


ሰኔ፣2011 ዓ.ም

ጅማ-ኢትዮጵያ

# በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም

# የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና ጥናት


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል


ለድህረ ምረቃ መረሐ ግብር


በ

አንተነህ አየነው ዋለ

አማካሪ፡- ጌታቸው አንተነህ (ዶ/ር)


ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር የኤም ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ውስጥ ከፊሉን ለማሟላት የተዘጋጀ ጥናት፡፡

ሰኔ፣2011 ዓ.ም

ጅማ-ኢትዮጵያ

በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም

የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና ጥናት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም

1.ጌታቸው አንተነህ (ዶ/ር) ፊርማ------------------------

የውስጥ ፈታኝ ስም

2.------------------------------------ ፊርማ-----------------------

የውጭ ፈታኝ ስም

3.------------------------------------- ፊርማ-----------------------

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና-----------------------------------------------------------------------------------------I

አጠቃሎ-------------------------------------------------------------------------------------------II

አህጽሮተ ቃላትና ዝርዝራቸው------------------------------------------------------------------III

የአማራ ክልል እና የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ካርታዎች--------------------------------------
V

ምዕራፍ አንድ-----------------------------------------------------------------------------------------1

1. መግቢያ------------------------------------------------------------------------------------------------1

1.1 የጥናቱ አደረጃጀት------------------------------------------------------------------------1

1.2 የጥናቱ ዳራ----------------------------------------------------------------------------------2

1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት----------------------------------------------------------------3

1.4 የጥናቱ አላማዎች---------------------------------------------------------------------------3

1.4.1 ዋና ዓላማ---------------------------------------------------------------------------------3

1.4.2 ዝርዝር ዓላማዎች-----------------------------------------------------------------------3

1.5 ጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች--------------------------------------------------------------4

1.6 የጥናቱ አስፈላጊነት-----------------------------------------------------------------------4

1.7 የጥናቱ ወሰን---------------------------------------------------------------------------------4

1.8 የጥናቱ ውስንነት-----------------------------------------------------------------------------5

1.9 በመስክ ቆይታ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች----------5

1.9.1 የመስክ ቆይታ-----------------------------------------------------------------------------5

1.9.2 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች-------------------------------7
VI

ምዕራፍ ሁለት------------------------------------------ -------------------------------10

2. የተጠኝ አካባቢና የማህበረሱ ዳራዊ ገለጻ--------------------------------------------------10

2.1 መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ-------------------------------------------------------------10

2.2 አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ-----------------------------------------------------10

2.3 ቋንቋና ሃይማኖት------------------------------------------------------------------------11

2.4 በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የሚገኙ ሰው ሰራሽ ቅርሶች-----------------------------12

3.3.5 የርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ታሪካዊ አመሰራረት-------13

ምዕራፍ ሶስት-------------------------------------------------------------------------------21

3. ክለሳ ድርሳናት-----------------------------------------------------------------------------21

3.1 ንድፍ ሀሳባዊ ቅኝቶች---------------------------------------------------------------------21

3.1.1 የሃይማኖት ምንነት----------------------------------------------------------------------21

3.1.2 የገዳም ምንነት-----------------------------------------------------------------------------22

3.1.3 የገዳማዊ ህይወት አጀማመር በኢትዮጵያ--------------------------------------------23

3.1.4 የተረክ ምንነት-----------------------------------------------------------------------------25

3.1.4.1 የተረክ ዓይነቶች--------------------------------------------------------------------------27

3.1.4.1.1 ተረት---------------------------------------------------------------------------------------30

3.1.4.1.2 አፈ ታሪክ-------------------------------------------------------------------------------
32

3.1.4.1.3 ሚት------------------------------------------------------------------------------------32

3.1.5 ተረክን የማጥናት አስፈላጊነት እና የአጠናን ስልት----------------------------------34

3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት-------------------------------------------------------------------35

ምዕራፍ አራት-----------------------------------------------------------------------------------43

4. የአጠናን ዘዴ-----------------------------------------------------------------------------------43

4.1 የጥናቱ አካላይ-----------------------------------------------------------------------------43

4.2 የቦታ ናሙና አመራረጥ-----------------------------------------------------------------------43

4.3 የመረጃ ሰጪ ናሙና አመራረጥ-------------------------------------------------------------43

4.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች---------------------------------------------------------------44

4.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች-----------------------------------------------------------------48

ምዕራፍ አምስት-------------------------------------------------------------------------------50

5. የመረጃ ትንተና-------------------------------------------------------------------------------50

5.1.1 የገዳሟን ጥንታዊነት የሚዘክሩ ተረኮች---------------------------------------------51

5.1.2 ለገዳሟ የተገባላት የቃል ኪዳን ተረኮች-----------------------------------------------55

5.1.3 የገዳሟን ቅድስና እና ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች-------------------------57

5.1.4 በገዳሟ የተፈፀሙ የፈውስ ተረኮች-----------------------------------------------------67

5.1.5 በገዳሟ የተፈፀሙ የገቢራተ ተዓምራት ተረኮች-------------------------------------71

5.1.6 ከገዳሟ መመስረት ጋር በተየያዘ የሚነገሩ ትንቢት ነክ ተረኮች------------------74

5.1.7 ከራዕይ ጋር በተየያዘ የሚነገረው ተረክ-------------------------------------------------76

5.1.8 የገዳሟን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ ተረኮች-------------------------------------------78

ምዕራፍ ስድስት------------------------------------------------------------------------------81

6.1 ማጠቃለያ------------------------------------------------------------------------------81

6.2 የይሁንታ ሀሳቦች----------------------------------------------------------------------85

ዋቢ ጽሁፎች---------------------------------------------------------------------------------87

ዓባሪዎች-------------------------------------------------------------------------------------93

ዓባሪ አንድ፡-ከገዳሚ የተሰበሰቡ ተረኮች-----------------------------------------------------93

ዓባሪ ሁለት፡-አጥኝው በመስክ ላይ መረጃ ሲሰበስብ የሚያሳዩ ፎቶዎች-----------------104

ዓባሪ ሶስት፡-ከገዳሚ የተሰበሰቡ ፎቶዎች-----------------------------------------------------105

ዓባሪ አራት፡-ለመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉ ጥያቄዎች----------------------------------- 108

ዓባሪ አምስት፡-በገዳሚ ህግና ስረዓት መሰረት ርዕሰ ርዑሳን ተብለው እየተሾሙ ያገለገሉ አባቶች ስም ዝርዝር በጊዜ ቅደም ተከተል----------------------------------------------110

ዓባሪ ስድስት፡-ለመረጃ ስብሰባ በተንቀሳቀስኩበት ወቅት ለህጋዊነት ከተጠቀምኳቸው ደብዳቤዎች በከፊል------------------------------------------------------------------------------- 112

ዓባሪ ሰባት፡-የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መገለጫ----------------------------------------------- 113

ዓባሪ ስምንት፡- ከ18ኛው ክ/ዘመን በፊት የተሰሩና ጥንታዊ ታሪክ ያላቸው ቋሚ ቅርሶች 114

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ይዘት እና ማህበራዊ ፋይዳ ተንተኖ ማጥናትና ማሳየት በሚል ዋና አላማ የቀረበ ነው፡፡ ይህች ጥንታዊትና ታሪካዊት ገዳም ከተመሰረተች ከ3740 ዓመት በላይ ስለሆነ የኦሪትም የሐዲስ ኪዳኑም ስርዓት የተፈጸመባት እንደ ጊዜ ቅደም ተከተላቸው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ጥናት ስምንት መረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን ስድስቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ የጥናቱ ዓላማም የተሳካ ይሆን ዘንድ ጽሁፋዊ ማስረጃዎችን ከመጠቀም በተጨማሪ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በማስታዎሻ፣ በምስል፣ በመቅረጸ ድምጽ እና እንደአስፈላጊነቱ በቪደዮ ካሜራ በማጠናቀር መረጃዎቹ ክግብ ለማድረስ ተችሏል፡፡ እነዚህ ተረኮች በገላጭ የምርምር ዘዴ በመጠቀም እና በተረክ ትንተና ንድፍ ሃሳብ መንደርደሪያነት ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም የተጠኝ አካባቢና የማህበረሰቡ ዳራዊ ገለጻ ተቃኝቷል፡፡ በጥናቱ ሃያ ስድስት የሚሆኑ ተረኮች የተሰበሰቡ ሲሆን ከይዘታቸው አንጻር የገዳሚን ጥንታዊነት የሚዘክሩ፣ የቃል ኪዳን፣ የገዳሚን ቅድስናና ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ፣ የፈውስ፣ የገቢራተ ተዓምራት፣ ትንቢት ነክ፣ የራዕይ እና ሉዓላዊነትን የሚያስጠብቁ ተረኮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## ምስጋና

ጥናቱ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው እንዴት መስራት እንዳለብኝ አቅጣጫ በመጠቆም፣ በማረምና በማስተካከል እንደ መምህር ሳይሆን እንደ ታላቅ ወንድም፣ አስቤ ሳይሆን አስበው ስልክ በመደወል ጥናቴ የተሳካና ያማረ ይሆን ዘንድ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለመምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ጌታቸው አንተነህ ይግዛው የከበረ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡

ይህን የትምህርት ዕድል እንዳገኝ ያገዙኝ አካላት ብዙ ናቸው፡፡ በተለይ ግን የጅማ ዩንቨርሲቲ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪ መምህር ሀብታሙ እንግዳው፣ ጨንቆኝ በነበረበት ሰዓት በመምከር፣ የህይወት ተሞክሮዎን በማካፈል ላበረታቱኝና ተስፋ ለሰጡኝ መምህሬ ዶ/ር ለማ ንጋቱ፣ በወቅቱ የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ለነበረው አቶ ብርሃኑ ዋለ እንዲሁም ትምህርቴን ጀምሬ እስከምጨርስ ክፍለ ጊዜየን ለሸፈናችሁልኝ ለአብረሃ ወ አጽበሐ መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራን በሙሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ይህንን ጥናት በምሰራበት ጊዜ በፎቶ፣ በድምፅና በቪዲዮ የምታውቁትን ነገር ካለምንም ማንገራገርና መለመን ደስ እያላችሁ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ የገዳሟ የእምነት አባቶችና ሌሎቹ የመረጃ አቀባዮቼ ምስጋና ይገባችኋል፡፡

ወንድሜ ጌትነት አየነው በጥናቴ ወቅት ኢጋጥሞኝ የነበረውን ለአንተ አልነግርህም፡፡ ሆኖም ግን በአንተ ድጋፍ፣ ጥረት፣ ምክር እንዲሁም ተግሳጽ እዚህ አድርሰኸኛል፡፡ ስላደረክልኝ ነገር ሁሉ እግዚያብሄር ዋጋውን ይክፈልህ፡፡

I

## አህጽሮተ ቃላትና ዝርዝራቸው፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡት አህጽሮተ ቃላት በጥናቱ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ ናቸው፡፡

| አህጽሮተ ቃላት | የአህጽሮተ ቃላት ዝርዝር |
|---|---|
| ዘፍ. | ኦሪት ዘፍጥረት |
| ዘጸ. | ኦሪት ዘጻአት |
| ዘኁ. | ኦሪት ዘኁልቁ |
| ዘዳ. | ኦሪት ዘዳግም |
| ኢ.ያሱ | ኢ.ያሱ |
| መዝ. | መዝሙረ ዳዊት |
| መክ. | መጽሃፈ መክብብ |
| ሕዝ. | ትንቢተ ሕዝቅኤል |
| ሆሴዕ. | ትንቢተ ሆሴዕ |
| አሞጽ | ትንቢተ አሞጽ |
| ምሳ. | መጽሐፈ ምሳሌ |
| ማቴ. | የማቴዎስ ወንጌል |
| ሉቃ. | የሉቃስ ወንጌል |


| | |
|---|---|
| ማር. | የማርቆስ ወንጌል |
| ሐ.ሥ. | የሐዋሪያት ሥራ |
| 1ዩሐ. | አንደኛ የዩሐንስ መልእክት |
| ኤፌ. | ወደ ኤፌሶን |
| ገላ. | ወደ ገላትያ |
| ራእ. | የዩሐንስ ራዕይ |
| ጢሞ. | ወደ ጢሞቴዎስ |
| ዕብ. | ወደ ዕብራውያን |

እነዚህ ምህጻረ ቃላት በ1980 ዓ.ም ከታተመው ሰማንያ አህዱ መጽሃፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው፡፡

ማሳሰቢያ፡- በጥናቱ ውስጥ አንድ ነጥብ ወይም ይዘት (.) ለአህጽሮተ ቃላት አገልግሎት ሲውል፣ነጠላ ሰረዝ (፣) ምዕራፍን ከቁጥር መለያ ሆኖ አገልግሏል፤ ሁለት ነጥብ (፡) ደግሞ

አንዱን ቁጥር ከሌላው ለመለየት ሲያገለግል፣ ስረዝ (-) ከዚህ ቁጥር እስከ ዚህ የሚለውም ጠቋሚል፣ ድርብ ሰረዝ (፤) ደግሞ አንድን ጥቅስ ከሌላው ለመለየት አገልግሏል፡፡

ካርታ፡- ጥናቱ የተካሄደበት የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ መርጡለ ማሪያም ከተማ የሚያሳይ የአማራ ክልል፡፡



ምስል1፡- የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ካርታ

(የመረጃ ምንጭ፡-ከእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የተወሰደ፡፡)

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

እምነት የአማኞች ሁለንተና የሚመሰረትበት፣ በእምነቱ ተከታዮችና በልዕለ ተፈጥሮ ሃይላት መካከል ያለውን ትስስር የኃይማኖት መገለጫ ነው፡፡ በአብዛኛው እምነቶች መሰረታቸውን የሚያፀኑት በተረኮቻቸው ነው፡፡ በመሆኑም ሃይማኖታዊ ተረኮችን ማጥናት የማህበረሰቡን ስነልቦናዊ እና ማህበራዊ ማንነት ለመረዳት ያስችላል፡፡ ሃይማኖታዊ ተረኮች ከሚገኙባቸው ቦታዎች መካከል ገዳማት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ጥናት የተከናወነውም በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ ፋይዳቸውን በማሳየት ነው፡፡

ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን አጠቃላይ ገጽታ ማስተዋወቂያ ሲሆን፣ በውስጡም መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ውስንነት እንዲሁም በመስክ ቆይታ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች የሚሉት ጉዳዮች በውስጡ ይዟል፡፡

ሁለተኛው ምዕራፍ የተጠኝ የተጠኝ አካባቢና የማህበረሱ ዳራዊ ገለጻ የቀረበበት ሲሆን በውስጡም መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ቋንቋና ሃይማኖት አካቷል፡፡

ሶስተኛው ምዕራፍ ጥናቱን ለማከናወን የሚረዱ ንድፍ ሀሳባዊ ዳስሳ የተካሄደበት ሲሆን በውስጡም የሃይማኖት ምንነት፣ የገዳም ምንነት፣ የገዳም ህይወት አጀማመር በኢትዮጵያ፣ የተረክ ምንነት፣ የተረክ ዓይነቶች፣ ተረት፣ አፈ ታሪክና ሚት፣ ተረክን የማጥናት አስፈሊጊነትና የአጠናን ስልት የሚሉት ተዘርዝረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አንድ ዲማጽ፣ ሰባት የሁለተኛ ዲግሪ በአጠቃላይ ስምንት ማሚያ ጽሁፎች ተዳስሰዋል፡፡ በመጨረሻም የርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ታሪካዊ አመሰራረት የሚሉ ነጥቦች ተካትተውበታል፡፡

በአራተኛው ምዕራፍ ደግሞ የአጠናን ዘዴ ሲሆን በውስጡም የጥናቱ አካላይ፣ የቦታ ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ ሰጪ ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ተቀምጠዋል፡፡

በአምተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከርዕሰ አድባራ ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም የተሰበሰቡ ተረኮች የተተነተኑበት ክፍል ነው፡፡ ከገዳሟ የተሰበሰቡት ተረኮች ከይዘታቸው አንጻር የገዳሟን ጥንታዊነት የሚዘክሩ ተረኮች፣ ለገዳሟ የተገባላት የቃል ኪዳን ተረኮች፣ የገዳሟን ቅድስናና ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች፣ በገዳሟ የተፈጸሙ የፈውስ ተረኮች፣ በገዳሟ የተፈጸሙ የገቢራተ ተዓምራት ተረኮች፣ ከገዳሟ አመሰራረት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ትንቢት ነክ ተረክ፣ ከራዕይ ጋራ በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች፣ የገዳሟን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ ተረኮች በማለት በስምንት ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

ስድስተኛው ምዕራፍ የማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች ክፍል ሲሆን የጥናቱ አጠቃላይ ውጤት እና ተረኮቹ የተጠኘውን ማህበረሰብ እምነት፣ ፍልስፍና፣ አተያይ፣ የህይወት ዘዬ፣ አስተሳሰብ ከማሳየት አንጻር ያላቸውን ፋይዳ ጠቅለል ባለ መንገድ የቀረበበት ነው፡፡ በመጨረሻም ቢደረጉ መልካም ያልኳቸው የይሁንታ ሀሳቦች ተዘርዝረዋል፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ እና ተረክ ለብዙ ዘመን አብረው የኖሩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ይህም ማለት የሰው ልጅ የቋንቋ ባለቤት ሆኖ በህብረት መኖር ከጀመረ ጀምሮ ተረኮችን መጠቀም እንደጀመረ የብዙዎች እምነት ነው፡፡ በመሆኑም ተረክን በመጠቀም ስለእምነቱ፣ ስለባህሉ፣ ስለማንነቱ፣ ስለሚኖርባት ዓለም አፈጣጠር፣ ስለነገሮች አመጣጥ ወዘተ የሚያስረዳው፣ ምላሽ የሚያገኘው በተረኮቹ ነው፡፡

(Barthes, 1975:237) ተረክ በማንኛውም ውቅትና ጊዜ፣ በማንኛውም ቦታ፣ ማህበረሰብ እንዳለና ጅማሮውም ከሰው ልጅ ጋር ረጅም ጊዜ የቆየ እንደሆነ፣ ሰውን ካለ ተረክ ማሰብ ከባድ እንደሆነ እና በየትኛውም ማህበረሰባዊ ደረጃም ሆነ ቡድን የራሳቸው የሆነ ተረክ እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡

(Degh, 1972: 54& Finnegan,1975:36-37) ሲገልጹ ተረክ የሰው ልጅ የጽህፈት ጥበብ ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ የነበረ፣ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ስለዓለም አፈጣጠር፣ ስለ ነገሮች አመጣጥ፣ ስለእምነቱ፣ ስለባህሉ እና ስለማንነቱ ለመግለጽ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ተረክ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው፣ በማንኛውም ቡድን ወይም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ፣ ዘመንና ባህል የሚሻገር፣ በሁሉም የኪነጥበብ ቅርጾች የተለያዩ ጉዳዮችን ማስተላለፍ የሚችል፣ በቃል ወይም በጽሁፍ፣ በቅርጽ ወይም በስዕል፣ በአካለዊ እንቅስቃሴ፣ በዝርው ወይም በግጥም ቅርጽ ሊቀርብ የሚችል በርካታ የማህበረሰቡን ሁነቶች የሚያሳይ መግባቢያ ነው፡፡ ሲል ይበይነዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረቱ በገዳም ላይ በሚነገሩ ተረኮች በመሆኑ ሃይማኖታዊ ተረክ ከሚባለው ዘውግ ይመደባል፡፡ ሃይማኖታዊ ተረክ መሰረታዊ የሚባሉ ተፈጥራዊ ጥያቄዎችን ምላሽ በመስጠት የሰውን ልጅ በተስፋ እንዲኖር፣ በምግባር የታነጸ እንዲሆን፣ መልካም ነገሮችን እንዲማር ወዘተ የሚያደርግ ነው፡፡

ለዚህ ሃሳብ ድጋፍ የሚሆን Keith Sute (ዓ.ምቱ ያልተጠቀሰ) ሃይማኖታዊ ተረኮች በእምነት ስርዓት ውስጥ በጣም ትልቅ /ከባድ/ ለሚባሉ ጥያቄዎች ምላሽ ማግኛ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ለምንድን ነው የተፈጠርኩት?፣ ለምን ከዚህ ቦታ ተገኘሁ?፣ ከሞትኩ በኋላ እሚሆነው ነገር ምንድን ነው?፣ የህይወት ትርጉሙ ምንድን ነው? ለሚሉ ማንም ሰው በአዕምሮው ለሚያሰላስላቸው ጥያቄዎች ሃይማኖታዊ ተረክ ምላሽ ይሰጣል ካለ በኋላ ሁሉም ሃይማኖቶች መልካም ነገሮችን እንደሚያበረታቱና አማኙም ማህበረሰብ በተጻፈውም ይሁን በቃል ባለው ቅዱስ ሃሳብ እራሱን እንደሚያንጽ ይገልጻል፡፡ በአጠቃላይ ሃይማኖታዊ ተረክ አንድ ማህበረሰብ ለምን እንደተፈጠረ፣ ማን እንደፈጠረው፣ ወደ ፊት የህይወቱ ፍጻሜ ምን ሊሆን እንደሚችል፣ ለሚኖርባት እንቆቅልሽ ለሆነችው ዓለም ምላሽ የሚያገኝበት፣ እምነቱን የሚያጸናበት፣ የእምነቱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥበት፣ እራሱን ከክፉ ነገር የሚያርቅበት ወዘተ መሳሪያው ነው ማለት እንችላለን፡፡

በተለያዩ አካላት የተሰሩ የሃይማኖታዊ ተረክ የጥናት ውጤቶችም የሚጠቁሙት የተጠኘውን ማህበረሰብ ከየት መጣነቱን፣ ማንነቱን፣ ዕምነቱን፣ ባህሉንና አስተሳሰቡን እንደሚገልጹ ነው፡፡ ነገር ግን እስካሁን ድረስ በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮቹ ተሰብስበው ጥናት አልተካሄደባቸውም፡፡ በመሆኑም

ይህን ክፍተት በማየቴና አንዳች የመነሻ ሀሳብ ለማስቀመጥ ተረኮች ከገዳሙ ተሰብስበዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝው ይህን ጥናት ለማጥናት ስበብ የሆነው ጉዳይ፡-

መርጡለ ማሪያም ከተማ ነዋሪና መምህር እንደመሆኔ ከትምህርት ቤታችን የሀገርህን እወቅ ክበብ አባላት ጋር ወደ ቦታው በመሄድ በዕቃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎችን የማዬት ዕድል ማግኘቴና ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ሊኖሩ እንደሚችሉ በማሰቤ፣

-እነዚህ ተረኮች ቢጠኑ ለአማኙ ማህበረሰብ እንዲሁም ለፎክሎር የትምህርት ዘርፍ የሚያበረክተው የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ በማሰቤ፣

-ርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም ታሪካዊ አመሰራረቷ ከ3700 ዓመት በላይ ቢሆንም በገዳሟ ተረኮች ላይ የተሰራ አለመኖሩ፡፡፣

-በገዳሟ የሚገኙ ተረኮች የሚኖራቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ለማሳየት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 ዋና አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ከርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ይዘት እና ማሃበራዊ ፋይዳ ተንትኖ በማጥናት ማሳየት ነው፡፡

ከዚህ ዋና ዓላማ በመነሳትም ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

### 1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

ተጠኝውን ማህበረሰብ በተረኮቹ አማካኝነት መመርመር፤

በገዳሟ የሚነገሩ ተረኮች ከቁሳዊ ባህሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት መፈተሽ፣

ከገዳሟ ጋር ተያያዥናት ያላቸው ተረኮችን መተንተን

### 1.4 የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

ተረኮቹ የተጠኝው ማህበረሰብ ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከማሳየት አንጻር ምን ይመስላል?

በገዳሚ የሚነገሩ ተረኮች ከቁሳዊ ባህሎች ጋር ሊኖራቸው የሚችለው ትስስር እንዴት ይታያል?

ከገዳሚ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች እንዴት መተንተን ይቻላል?

### 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት /ጠቀሜታ/

ጥናቱ በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም ላይ መደረጉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በመጀመሪያ ተረኮቹ የተጠኝውን ማህበረሰብ እምነት፣ ፍልስፍና፣ አተያይ፣ የህይወት ዘዬ መመልከቻ መነጸሮች መሆናቸውን ገልጾ የማሳየት አቅም ሊኖረው ይችላል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ ተረኮቹ የተጠኝውን ማህበረሰብ መቼ፣ ለምን፣ በምን መልኩ እንደሚገለገልባቸው /አውዳዊ አጠቃቀሙን/ ከማሳወቅ አንጻር ጥናቱ የራሱ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡
- ሌላው ደግሞ ወደፊት ስለገዳሚ ጥንታዊነትና ታሪካዊ አመሰራረት ለማጥናት ለሚፈልጉ አካላት እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ከዚህም በተጨማሪ በሌሎች ገዳማት የሚነገሩ ተረኮችን ለማጥናት ለሚነሱ የፎክሎር ተመራማሪዎች መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
- በመጨረሻም የሚሰበሰቡ ተረኮች ተመርምረው፣ ተተንትነው ተጠኑ ማለት የማህበረሰቡን አጠቃላይ ማህበራዊ ሁለንተና ከማሳየት አንጻር የራሱ ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

### 1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት አጥኝ የጥናቱን ወሰን ከቦታና ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር በማለት በሁለት ከፍሎ ይመለከተዋል፡፡ ከቦታ አንጻር ማለት ጥናቱ በመርጡለ ማሪያም ከተማ በምትገኘው

በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን ሲጠቁም ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ማለት ደግሞ ጥናቱ ከገዳሟ ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮች ላይ ብቻ የተወሰነ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ጠቅለል አድርገን ስናየው የዚህ ጥናት ዋና ማጠንጠኛ በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡

### 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ የሚሞላቸው ክፍተቶች ቢኖሩም ውስንነቶችም አሉበት፡፡ ከገዳሟ ጋር በተያያዘ ገዳሟ ከመመስረቷ በፊትና ስለ ታሪካዊ አመሰራረቷ፣ ስለመሰረቷት ነገስታትና ቅዱሳን አባቶች፣ በውስጧ ስለሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች ጥናቱ አያካትትም፡፡ ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ከገዳሟ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች ላይ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ውስንነቱ ነው፡፡

በተጨማሪም ጥናቱ የመረጃ አቀባዮች ውስንነት ይታይበታል፡፡ በዚህም በመርጡለ ማሪያም ከተማ ከሚኖረው ብዙ ሺህ ህዝብ ውስጥ ለጥናቱ መረጃ ሰጪነት የተሳተፉት አስራ ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

ለእነዚህ ውስንነቶች ዋነኛ ምክንያቶች መካከል የመጀመሪያው የሚጠናው ጉዳይ ሃይማኖታዊ ተረክ በመሆኑ ያልተዛባና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ይቻል ዘንድ የሚመርጣቸውን መረጃ አቀባዮች ከእውቀት፣ ከአገላለጽ፣ ከቅንነት፣ በቦታው መወለድና ለብዙ ጊዜ መኖር /ባይወለዱም ለብዙ ጊዜ መኖር/ ወዘተ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተደረገ መረጣ በመሆኑ ነው፡፡

## 1.8 በመስክ ቆይታ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### 1.8.1 የመስክ ቆይታ

ወደ መስክ በቀጥታ ከመሄዱ በፊት አንድ አጥኚ ማድረግ የሚገባውን የቅድመ ዝግጅት ተግባራት አድርጓል፡፡ በቁጥር ኢ/ቋ/ስ/ጽ/አማ/64/11 እና ኢ/ቋ/ስ/ጽ/አማ/65/11 ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም /IES/ እና ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም /ILS/ ቤተ መጽሃፍት አገልግሎት በቀን 16/05/2011 ዓ.ም

የትብብር ደብዳቤ በማጻፍ በገዳማት ተረክና መሰል ለጥናቱ ስራ አጋዥ የሆኑ የጥናት ስራዎችን ለመመልከት ችሏል፡፡ እንዲሁም ስለሚያጠናው አካባቢ አጠቃላይ መረጃ ሊያስገኙ ይችላሉ ብሎ ያሰብኳቸውን መጽሄቶች፣ በራሪ ወረቀቶች ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና ከቤተ መጽሃፍት አንብቧል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከደብዳቤው በፊት ስለርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ስኔ 30፣2010 ዓ.ም ወደ ገዳሟ በመሄድ የጅማ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ የስነ ጽሁፍና ፎክሎር ተማሪ እንደሆነ፣ ለህጋዊነቱም የዩንቨርሲቲውን መታወቂያ እና በመርጡለ ማሪያም ከተማ በአብረሃ ወ አጽበሃ መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ ቤትም መምህር እንደሆነ በመናገርና የስራ መታወቂያ በማሳየት አሁን ግን በገዳሟ ተረኮች ላይ ጥናት መስራት እንደሚፈልግ ሲነግራቸው ህጋዊ ደብዳቤ ካመጣ መስራት እንደሚችል ከስምምነት ላይ ደርሶ ወደ ቤቱ ተመሷል፡፡

ከዚሁም ጎን ለጎን እነዚህ አባቶች በገዳሟ ለብዙ ጊዜ የኖሩና እያገለገሉ የሚገኙ በመሆናቸው ከዚህ በፊት ወደ ገዳሟ ለጥናትና ምርምር መጥተው ስለነበሩ አካላት በመጠየቅ ምንም እንኳን  ገዳሟ ጥንታዊትና የረጅም ታሪክ ባለቤት ብትሆንም ብዙ አጥኝዎች ወደ ቦታው እንደማይመጡ አልፎ አልፎ ጉብኝት በሚመስል መልክ የሚመጡትም ጥናት እንደሚሰሩ ወይም ለሚሰሩ አካላት እውቅና እንደሚፈጥሩ ቃል በመግባት በተግባር ግን የውሃ ሽታ ሆነው እንደሚቀሩና በተለይ ግን በአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ምንም የመጀመሪያም ሆነ የሁለተኛ ወይም የሶስተኛ ዲግሪ ጥናት እንዳልተሰራ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስለገዳሟ የሚነገሩ ተረኮችን የሚያውቁና በቂ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉም በማነጋገር የቅድመ ማረጋገጥና ልየታ ስራ በመስራት ተመልሷል፡፡

በዚህም መሰረት ከትምህርት ክፍሉ በቀን 16/05/2011 ዓ.ም ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የትብብር ደብዳቤ ተጽፎለታል፡፡ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ደግሞ በቀን 20/05/2011 ዓ.ም ለርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም /ሰ/ጉ/ጽ/ቤት ደብዳቤ ከጻፉለት በኋላ ከገዳሟ ሰበካ ጉባኤ አባላትና ከገዳሟ ዋና አስተዳዳሪ ከአባ ኃይለማሪያም ጋር ልክ እንደበፊቱ እነሱንም በጅማ ዩንቨርሲቲ የስነጽሁፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ እንደሆነ በመንገርና መታወቂያ በማሳየት ከገዳሟ ጋር ተያይዘው

በሚነገሩ ተረኮች ላይ ጥናት መስራት እንደሚፈልግ ሲነግራቸው ካለምንም ማመንታት በደስታ ነበር የተቀበሉት፡፡

ስራውን መስራት እንደሚችል ከተነገረው በኋላ ምንም ጊዜ ሳያጠፉ መረጃ ሊሰጡት የሚችሉ ሰዎችን ወደ መምረጥ ገባ፡፡ በመቀጠልም እዚያው ተወልደው ከዚያው ከሚኖሩ የስራ ባልደረቦቹ ጋር ውይይት አደረገ፡፡ እነሱም ከገዳሚ ጋር ተያይዞ ስለሚነገሩ ነገሮች የጠለቀ አውቀት አላቸው በማለት የበፊት የገዳሚ አስተዳዳሪ የነበሩትን አባ ኃይለ ኢየሱስን፣ የአሁኑ የገዳሚ አስተዳዳሪ የሆኑትን አባ ኃይለ ማሪያምን፣ የመጻህፍት ትርጓሜ መምህር የሆኑትን መርጌታ ፈንታየን እና በገዳሚ የቅኔ መምህር የሆኑትን መርጌታ ዲበኩሉን በመጠቀም ጥሩ መረጃ ሊሰጡት እንደሚችሉ ነገሩት፡፡

አጥኝውም የተሰጠውን ጥቆምታ ተቀብሎ ከቀን 25 /06/ 2011 ዓ.ም እስከ12/ 08/ 2011 ዓ.ም ድረስ ከነሱ ብቻ ሳይሆን እነሱ ከጠቆሙት ሌሎች ሰዎችም ጭምር ከርዕሰ ርዑሳን አባ ኃ/ ኢየሱስ (የቀድሞ የገዳሚ ርዕሰ ርዑሳን)፣ ከርዕሰ ርዑሳን አባ ኃ/ ማሪያም (የአሁኑ የገዳሚ ርዕሰ ርዑሳን)፣ ከነ አባ ቃለ ጽድቅ (የገዳሚ ዕቃ ቤት ሃላፊ)፣ ከመርጌታ ዲበኩሉ (በገዳሚ የቅኔ መምህር)፣ ከፋሲካው ደጀን /መምህር/፣ ከገብረ ህይወት አያሌው /መምህር/፣ ከሹምየ አያሌው /መምህር/ በአንድ ወር ከአስራ ሰባት ቀን ውስጥ 26 የሚሆኑ ተረኮችን እንደ መረጃው ባህሪና ግለሰቦች ፍላጎት በቃለ መጠየቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ውይይት፣ በማስታዎሻ ደብተርና ከጽሁፍ ሰነዶች ለመሰብሰብ ችሏል፡፡ ለናሙና ሰጪነት የተመረጡት አንድም በገዳሙ ውስጥ ካላቸው ሃላፊነት፣ ካላቸው የረጅም ጊዜ ቆይታ እና እውቀትን መስረት ያደረገ ነው፡፡

ሌላው በዚህ የመረጃ ስብሰባ ጊዜ የጾታ ስብጥርን በተመለከተ ሁለቱንም ለማሳተፍ ቢሞከርም ሴት ቁልፍም ሆነ ረዳት መረጃ አቀባይ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ምንም እንኳ ገዳም ቢሆንም ሴቶች በብህትና ህይወት የሚኖሩበት ባለመሆኑ ነው፡፡

### 1.8.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይህን ጥናት በሚሰራበት ጊዜ ችግሮች አጋጥመውታል፡፡ ካጋጠሙት ችግሮች ውስጥ የመጀመሪያው የመብራት ችግር ነው፡፡ በመርጡለ ማሪያም ከተማ ባለው የመብራት መቆራረጥ ችግር ምክንያት መስራት ያለብትን የጽሁፍ፣ የመረጃ ማጠናቀር፣ የንባብ

እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን በወቅቱ እንዳይሰራ ከማድረጉም ባሻገር ላልተፈለገ ወጭ ዳርጎታል፡፡ ነገር ግን በቤተሰብ ያለው የመብራት ሁኔታ የተሻለ በመሆኑ ከጥናቱ ቦታ ወደ ቤተሰቦቹ ከቤተሰቦቹ ወደ ጥናቱ ቦታ እንደአስፈላጊነቱ በተደጋጋሚ በመመላለስ ተፈጥሮበት የነበረውን የመብራት ችግር ለመቅረፍ ችሏል፡፡

ቀጣዩ አጋጥሞት የነበረው ችግር የጥናቱን ዋና ርዕሰ ጉዳይ የሆነውን ‹‹ተረክ›› የሚለውን በምን አቻ ቃል ተጠቅም መረጃ መሰብሰብ እንደሚችል ነበር፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ የተካሄደበት ማህበረሰብ ስለዚህ ቃል ምንነት ያለው እውቅና በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን ‹‹ተረክ›› በማለት ፋንታ ምንም እንኳ አቻ ፍች ያላቸው ባይሆኑም ‹‹ታሪክ››፣ ‹‹የሚባሉ ነገሮች››፣ ‹‹ይትበሃል›› አልፎ አልፎም ‹‹ተዓምር›› በሚሉ ቃላት ተጠቀሞ ተረኮችን ለመሰብሰብ ችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተጠኝ አካባቢና የማህበረሰቡ ዳራዊ ገለጻ

### 2.1 መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጎጃም አስተዳድር ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ ነው፡፡ ከሀገራችን ኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ በ 365 ኪሎ ሜትር፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህር ዳር በ 180 ኪሎ ሜትር፣ ከምስራቅ ጎጃም ዞን ዋና ከተማ ደብረ ማርቆስ በ 192 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ወረዳ ነው፡፡ ይህ ወረዳ ከላይ እንደተገለጸው ከአዲስ አበባ በስተሰሜን የአባይን ወንዝ ተሻግሮ የደጀን ከተማን አቋርጠው፣ የብቸናን እና የደብረ ወርቅን ከተማ አልፎ ግንደ ወይን ከተማ ሲደረስ ወደ ቀኝ በመታጠፍ በምስራቅ አቅጣጫ ሲጓዙ በ27 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ወረዳ ነው፡፡ በምስራቅ ደቡብ ወሎ ዞን፣ በምዕራብ ጎንቻ ሲሶ እነሴ /ግንደ ወይን/ ወረዳ፣ በሰሜን ደቡብ ጎንደር ዞን፣ በደቡብ እናርጅ እናውጋ /ደብረ ወርቅ/ ወረዳ ያዋስኑታል፡፡

### 2.2 አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

የእነበሴ ሳር ምድር ወረዳ አጠቃላይ የቆዳ ስፋትን ስንመለከት 1065 ስኩየር ኪሎ ሜትር እንደሆነ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ የወረዳው አስተዳደራዊ አከፋፈልን በተመለከተ የከተማና የገጠር ተብሎ የተከፈለ ሲሆን 33 የገጠር 4 የከተማ በአጠቃላይ 37 ቀበሌዎችን የያዘ ነው፡፡ ከወረዳው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ መሰረት የ2010/11 ዓ.ም አጠቃላይ የህዝብ ብዛት ወንድ 79693 ሴት 84059 ድምር 163752 ሲሆን የገጠር ነዋሪዎች ብዛት ወንድ 67335 ሴት 68272 ድምር 135394 ነው፡፡ የከተማ ነዋሪዎች ብዛት ደግሞ ወንድ 12358 ሴት 15787 በድምር 28145 ነው፡፡ በመቶኛው ስናሰላው 82.68% የሚሆነው ኑሮውን በገጠር የሆነና የኑሮ መተዳደሪያው ግብርና እና አርብቶ አደር ነው፡፡ ቀሪው ወደ 17.31% የሚሆነው ማህበረሰብ ደግሞ በከተማ ኑሮውን ያደረገ ሲሆን በንግድ፣ በእርሻ ስራ እና እንደሌሎች የሀገራችን የወረዳ ከተሞች በተለያየ ከተሜ ነክ ስራዎች ኑሮውን ይገፋል፡፡

እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ በሶስት የአየር ክልል ውስጥ ማለትም በቆላ፣ በወይናደጋና በደጋ የሚገኝ ሲሆን ቆላው 53%፣ ወይና ደጋው 33%፣ ደጋው ደግሞ 14% ይሸፍናል፡፡

የወረዳው ዓመታዊ አማካኝ የዝናብና የሙቀት መጠን ቆላ 1500–1800 ሚ/ ሜትር፣ ወይና ደጋው 1200–1500 ሚ/ሜትር፣ ደጋው ደግሞ 900–1200 ሚ/ ሜትር የሚያገኝ ሲሆን አማካኝ የሙቀት መጠኑ ዝቅተኛ 12.5 ዲግሪ ሴሊሽየስ ከፍተኛ 25 ዲግሪ ሴሊሽየስ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ መልከዓ ምድራዊ ገጽታው 30% በመቶው ተራራማ፣ 20 በመቶ ሜዳማ፣ 45 በመቶ ወጣ ገባና 5 በመቶ ደግሞ ሸለቋማ ነው፡፡

## 2.3 ቋንቋና ሀይማኖት

የወረዳው ህዝብ የዕለት ከዕለት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ትምህርታዊ፣ ሃይማኖታዊ ወዘተ ጉዳዮችን ለማከናወን የሚጠቀመው ቋንቋ አማርኛ ብቻ ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ሁኔታ በተመለከተ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይ ሲሆን፣ በገጠሩ አካባቢ በጣም ውሰን የሆኑ የእስልምና፣ በከተማው ደግሞ ከተለያየ አካባቢ በስራ ጉዳይ የመጡ በጣም ጥቂት የሆኑ የእስልምና እምነት ተከታዮች ይገኛሉ፡፡

ይህ ጥናት የተሰራውም በዚሁ ወረዳ ከሚገኙ አራት የከተማ ቀበሌዎች ማለትም 01(አብረሃ ወ አጽበሐ)፣ 02 (አባ ሰላማ)፣ 03 (ሀገረ እግዚያብሄር) እና 04 (ዕርሃ አርያም) ውስጥ 04 ማለትም በሌላ ስሙ ዕርሃ አርያም በሚባለው ሲሆን መርጡለ ማርያም ከተማ ከባህር ጠለል በላይ 2654 ሜትር ከፍታ ሲኖራት ገዳሚ ከከተማዋ በ 50 ሜትር ከፍታ ያህል ዙሪያውን እንደ ግድግዳ በቆመው አለታማ ቦታ ላይ የተመሰረተች ስትሆን ካለችበት አምባ ላይ ሆነው ሲመለከቱ ከተማዋ ጥርት ብላ ትታያለች፡፡ በአካባቢ የሚገኙ ቀበሌዎች ሳይቀሩ ጥርት ብለው ይታያሉ፡፡

**(የመረጃ ምንጭ፤- ከእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ ቤት በቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት ቡድን ካዘጋጀው መጽሄት የተገኘ፡፡)**

## 2.4 በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የሚገኙ ሰው ሰራሽ ቅርሶች

ቅርስ የአንድ ሀገር ባህል፣ ታሪክና ስልጣኔን የሚገልፅና ሀገሪቱ ያላትን ድንቅ የተፈጥሮ ሃብት የሚያካትት ነው፡፡ በተጨማሪም ካለፈው ትውልድ እየተወረሰ የሚተላለፍ በሳይንስ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በስነ-ጥበብና በዕደ ጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊነትና ዋጋ ያለው የዘመናት የስራ ውጤት ክምችትና የተፈጥሮ ገፀ በረከት ውጤት የሆነ ግዝፍነት ያለውና ግዝፍነት የሌለው ሀብት ነው፡፡ የቅርስን ምንነት በተመለከተ በተለያየ ጊዜ ስለቅርሶች አስተዳደር እንዲሁም  ጥናትና አጠባበቅ የወጡ አዋጆች ላይ የተሰጠውን ለአብነት እንይ፡፡

ስለጥንታዊ ቅርሶች አስተዳደር ባወጣው አዋጅ ቁጥር 229/1958 ላይ ‹‹ጥንታዊ ቅርስ›› ማለት ከ1850 በፊት የተሰራ ማንኛውም ዓይነት ሰው ሰራሽ ስራ ወይም እቃ ነው፡፡ ተብሎ ሲገለፅ ቀጥሎ ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 36/1982 ደግሞ ‹‹ቅርስ ማለት በኢትዮጵያ ቅድመ ታሪክና የታሪክ ዘመን በስነ-ጥበብ፣ በሳይንስ፣ በባህል ወይም በታሪካዊ ይዘታቸው ከፍተኛ ተፈላጊነትና ዋጋ ያላቸው የሰው ልጅ፣ የእንስሳትና የእጸዋት ቅሪት፣ ህንፃ የመታሰቢያ ቦታ ወይም ሀውልት፣ የጥንታዊ ከተማ ፍርስራሽ፣ ጥንታዊ የመቃብር ቦታ፣ የዋሻ ስዕል፣ የብራና ጽኁፍ፣ የድንጋይ ላይ ፅሁፍ፣ ከብር፣ ከነሃስ ወይም ከብረት ወይም ከእነዚህ ተከልሰው ከወጡ ንጥረ ነገሮች ወይም ከእንጨት፣ ከድንጋይ፣ ከቆዳ፣ ከዝሆን ጥርስ፣ ከቀንድ፣ ከአጥንትና ከአፈር የተሰሩ ቅርሶች፣ ስእሎችና ምስሎች፣ የፅኁፍና የግራፊክ ዶክመንት ወይም የሲኒማቶግራፊክና ፎቶግራፍ ዶክመንት፣ የድምፅ ወይም የቪዲዮ ቅጂ ዶክመንት፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሃስ፣ ወይም ከመዳብ የተሰራ ገንዘብ፣ ቤተ-ክርስቲያን፣ ገዳም፣ መስጊድ ወይም ማናቸውም የማምለኪያ ስፍራ፣ የብሔረሰቦች የመገልገያ፣ የጌጥ ወይም ማናቸውም ባህላዊ እቃ ወይምማናቸውም የሰው ስራ ፈጠራ ውጤት የሆነ ስትራክቸር ወይም እቃ ነው፡፡ በማለት ትርጉም ሲሰጥ አሁን ስራ ላይ በአለው ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 በአንቀፅ 3/4/ ላይ ቅርስ ማለት በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የስራ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚገልፅና የሚመሰክር በሳይንስ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ ስነ-ጥበብና በእደ ጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊነትና ዋጋ ያለው ማናቸውም ግዝፍነት ያለውና ግዝፍነት የሌለው ነገር ነው፡፡ በማለት ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ በእነዚህ ሦስት አዋጆች ላይ የተሰጡ የቅርስ የአተረጓጎም ጽንስ ሃሳቦች ሲጠኑ መጠነኛ ልዩነት

ከመኖራቸው በስተቀር እርስ በርስ የሚቃረኑ እንዳልሆኑና ልዩነቶችም ቢሆን ያልተካተቱትን እያካተቱ በመምጣት በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ እየሰፋ መሄዳቸውን ገላጭ ናቸው፡፡

እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የትናንት ስልጣኔ፣ የረጅም ጊዜ ታሪክና የመልካም ተፈጥሮ ገፅታ አሻራዎች ባለቤት በመሆኑ በዓይነትና በመጠን ተገልጠው የማያልቁ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ቅርሶች የሚገኙበት ነው፡፡ እነዚህን ቅርሶች በመጠበቅና በመንከባከብ ለተተኪው ትውልድ የማስተላለፍ ግዴታ ከአሁኑ ትውልድ ይጠበቃል፡፡ ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ቅርሶችን ዓይነት፣ ብዛት፣ ስርጭትና በምን ሁኔታ እንደሚገኙ ለማወቅና ለመከታተል እንዲቻል ለቅርስ ምዝገባ ትኩረት በመስጠት በተደራጀ መንገድ እየተካሄደ እንደሚገኝ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ ቤት የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

በወረዳው ተመዝግበው ለጎብኝና ለአጥኝዎች ክፍት ከሆኑ ቅርሶች ውስጥ ከሰማኒያ በላይ የሚሆኑ ጥንታዊ ገዳማትና ቤተ ክርስቲያናት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ገዳማትና ቤተ ክርስቲያናት በወረዳው በሚገኙ በተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙና ከ18ኛው ክፍለ ዘመን በፊት እንደተመሰረቱ ይነገራል፡፡ ሙሉ መረጃውንም በአባሪ ስምንት በሰንጠረዥ መልክ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 2.3.5 የርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ታሪካዊ አመሰራረት

"በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም"[1]ማቴ. 5፣14 ተብሎ በህያው ቃል እንደተነገረ ሁሉ በሀገራችን በኢትዮጵያ ከአክሱም ፅዮን ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የምትገኝ፣ በሀገረ ስብከት ለጎጃም የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን የሆነችውን የርዕሰ

---

[1]በሀገራችን የሚገኙ የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ክርስቲያናት በአብዛኛው በከፍታ ቦታ ላይ የተሰሩ እና ዙሪያቸውን ሀገር በቀል በሆኑ አጸዶች የተከበቡ ናቸው፡፡ አማኙ ማህበረሰብ ይህን የሚያደርግበትም ሃይማኖታዊ መሰረት አለው፡፡
በከፍታ ቦታ ላይ መገንባታቸው ሙሴ እራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ ባወጣ ጊዜ ‹‹ከግብጽ ሲወጡ የኤርትራን ባህር ተሻገሩ፣ ወደ ሲና ተራራም ደረሱ፣እዚያም እግዚያብሄር ‹‹ብሉይ›› የተባለውን ኪዳን ሰጣቸው ዘጸ. (13-14)፡፡ እግዚያብሄር ከህዝቡ ጋር ሊገናኝ በመካከላቸውም ሊኖር ስለወደደ ማደሪያ የሚሆን መቅደስ እንዲሰራለት፣ በማደሪያውም በክህነት ያገለግሉ ዘንድ አሮንና ልጆቹ እንዲቀድሱ የክብር ልብስም እንዲሰፋላቸው አዘዘ፣ ዘዳ.25-31፡፡ የሚለውን መጽሃፍ ቅዱሳዊ ተረክ መሰረት በማድረግ ሲሆን በአጸዶች መከበባቸው ደግሞ መላእክት ቤ ክርስቲያንን ዙሪያዋን ከበው እንደሚጠብቋት ለማሳየት ተፈልጎ እንደሆነ ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያምን ገዳም ታሪካዊ አመሰራረት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡፡

የመርጡለ ማሪያም ታሪካዊ አመሰራረት የአባይን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ በገቡት የኩሽ ልጆች ወይም ነገዶች እንደሆነ በአካባቢው በሚገኙ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና በመረጃ አቀባዮች በጥብቅ እንደሚታመን የታሪክ መጽሀፍትንና ከጥንታውያን አባቶች በቅብብሎሽ የመጣውን ዋቢ በማድረግ ነግረውኛል፡፡

በየካቲት፣16፣2011ዓ.ም፣ ከአባ ኃይለ ኢየሱስ ጋር ባረኩት ቃለ መጠየቅ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሁለት ሺህ ስምንት መቶ ዓመተ አለም ነገደ ካም ወይም የኩሽ ልጆች ኑሯቸውን የሚገፉት ታሪክ እንደሚያስረዳው በታላላቅ ወንዞች አካባቢ በመሆኑ የአባይን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ይነገራል፡፡ እነዚህ ነገዶች ግዮንን /አባይን/ ተከትለው በመምጣት የአካባቢውን የአየር ንብረት ግራና ቀኝ ሲፈትሹ መርጡለ ማርያም በወይና አደጋ የአየር ንብረት ውስጥ ያለችና በቆላና በደጋማ የአየር ንብረት የምትዋሰን ለኑሯቸውም ተስማሚ ሆና ስላገኟትና አንባዋ ደልዳላ ሁና ከባህር መካከል እንዳለች ደሴት ሞሰበ ወርቅ መስላ ስላገኟት ከልምላሜዋም የተነሳ እጅግ እያደነቁ ይህች ሀገር በአባይ ወንዝ የተከበበች፣ከልምላሜዋ ጋር አቀማመጧ የሚያምር፣ የእግዚያብሄር ሀገር ናት ብለው መጠሪያ ስሟን "ሀገረ እግዚያብሄር" ብለው ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሰየሟት ነግረውኛል፡፡

የዚህን ሀሳብ እውነትነት የሚያጠነክር የነገደ ካም ወይም የኩሽ ልጆች በዚህ ቦታ ላይ ደስ ብሏቸው ለብዙ ዘመናት በህገ ልቦና እንደአባታቸው አዳም እግዚያብሄርን እያመለኩና እያመሰገኑ እንደኖሩ እነዚህ ነገዶችም በህገ ልቦና ከ4,500 ዓመተ አለም እስከ 2,800 ዓመተ ዓለም በአጠቃላይ ለ1,700 ዓመት ሙሉ እንደአባታቸው አዳም መሰዋዕት እየሰው የኖሩባት የረጅም ታሪክ ባለቤት እንደሆነች (አባ ኃይለ ኢየሱስ፣2011፣8) ተገልጾ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል የዚች ጥንታዊትና ታሪካዊት ገዳም ከንግስተ ሳባ /ማክዳ/[2] እና ከልጇ ሚኒልክ ቀዳማዊ ጋር የተያያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ንግስተ ሳባ የነገሰቸው በአክሱም አቅራቢያ በጥንቱ አጠራር ሳባ በምትባለው ከተማ እንደነበርና በአባቷ በአቦጋስ /ተዋስያ/ እግር ተተክታ ኢትዮጵያን መግዛትና ማስተዳደር የጀመረችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ 1013-982 ዓመተ ዓለም ለ31 ዓመት እንደሆነ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ በወቅቱም ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጋር የጠበቀ የንግድ ግንኙነት ነበራት እየሩሳሌምንም ጨምሮ፡፡ በጊዜው በእየሩሳሌም ነገሶ የነበረውም የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነበር፡፡ ከኢትዮጵያ ወደ እየሩሳሌም ከእየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ የሚነግድ ታምሪን የተባለ ነጋዴ ጥሩ ጥሩ ዕቃዎችን ከኢትዮጵያ ገዝቶ ለሰሎሞን ካስረከበ በኋላ፣ ሲመለስ የለሎሞንን የቤተ መንግስት ስነ ስረዓትና ጥበቡንም፣ ክብሩንም ሁሉ ለንግስተ ሳባ እንደነገራትና በዚህ ነጋዴ የተጀመረው የንጉሱና የንግስቲቱ ግንኙነት አድጎ በጀሮዋ የሰማችውን በአይኗ ለማረጋገጥ ወደ እየሩሳሌም እንደተጓዘችና[3] ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳ[4] ወደ ሀገሯ እየተመለሰች ሳለ ከቤተ መንግስቷ ሳትደርስ የኤርትራን ባህር ተሻግራ በሀማሴን አውራጃ ማይበላ (አንዳንዶቹ ደግሞ ማዕበል ይላሉ) ከተባለው ቦታ ስትደርስ ሚኒልክ ቀዳማዊን እንደወለደች (ፍስሀ፣ 2003፣100) ገልጿል፡፡

ሚኒልክ ቀዳማዊም የ22 ዓመት ወጣት ሲሆን ወደ አባቱ ሀገር ወደ ሰሎሞን መልሳ ላከችው፤ ሰሎሞንም ልጁ መሆኑን ለእስራኤል አሳወቀ፤ እስራኤላውያንም ልጁ መሆኑን ካወቁ በኋላ ለሁለት ንጉስ መገዛት አይቻለንምና በእናቱ ሀገር አንግሰህ ስደደው አሉት፡፡ እርሱም የብዕር ልጀን ስደድ ካላችሁኝ እናንተም የብዕር ልጆቻችሁን አምጡ አላቸው፡፡ እነርሱም አምጥተው ሰጡት፡፡ ከዚህ በኋላ ቀዳማዊ ሚኒሊክን የእብራይስጥን ቋንቋ የኦሪትን ህግና ስርዓት ለ3 ዓመታት አስተምሮ ስረዓተ መንግስት አድርሶ፣ ሚኒልክን

---

[2]ንግስተ ሳባ የሚለው ስሟ ሳይሆን የሳባውያን ንግስት ማለት እንደሆነ፤ መጠሪያ ስሟም በክብረ ነገስት ማክዳ፣በመጸሀፈ ነገስት በቀዳማዊና ካልዕ፣ በዜና መዋዕል ንግስተ ሳባ፣ በወንጌል ንግስተ አዜብ እንደምትባል (አባ ኃይለ ማሪያም፣መጋቢት 30፣2011ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

[3] ተጉዛበታለች ተብለው ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ውስጥ፡- የመጀመሪያው የንጉስ ሰለሞንን የቤተ መንግስት ስነስረዓትና ጥበቡን በማድነቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በታሪከ ነገስትና ክብረ ነገስት ላይ የሚገኘው እግሯ ላይ ሸሆና እንደነበርና እየሩሳሌም ስትደርስ እንደወለቀላት የሚያትት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ አምልኮተ እግዚያብሄርን ለማወቅ እየሩሳሌም ሄደች ወዘተ የሚሉት እንደሆኑ በቃልና (ፍስሀ፣2003) ያገኒኋቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

[4] የንግስተ ሳባን አፀናነስ በተመለከተ አንደኛው ወደ ተዘጋጀላት ስፍራ ሳትሄድ በመምሸቱ ምክንያት ከዚያው አድራ ፀነሰች ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ለመፀነሷ ምክንያት ጨው የበዛበት ምግብ አብልቶ በውሃ ጥም ወደ እሱ መኝታ ውሃ ፍለጋ እንደሄደችና ያኔ እንደተገናኛት (ፍስሀ፣2003 ዓ.ም፣100)

አንግሶ ከሄኖክ እስከ ንጉሱ ሰሎሞን እስከ ጻፋቸው ያሉትን መጽሀፍት ሰብስቦ ከ12ቱ ነገደ እስራኤል 12ሺ ህዝብ ማለት 3ሺ ሌዋውያን ካህናት(መንፈሳዊ አገልጋይ)፣ 3ሺህ ጠበብተ ኪራሞስ(ጥበበኛ ሰዎች)፣ 3ሺህ ከበኩረ ዕስራኤል (በአስተዳድርነት የሚያገለግሉ)፣እንዲሁም ከእስራኤል ፈረሰኞች (ለሰራዊትነት የሚያገለግሉ) 3ሺህ ጨምሮ ከታቦተ ፅዮን ጋር ወደ ኢትዮጵያ ላከው፡፡ ሲሉ (አባ ኃይለ ኢየሱስ (ቆሞስ)፣ 9-10፣2010 ዓ.ም) ያብራራሉ፡፡

ቀዳማዊ ሚኒሊክም ኢትዮጵያ እንደደረሰ መንግስትን ከእናቱ ማክዳ ተቀብሎ 982-957 ለሃያ አምስት ዓመታት በኢትዮጵያ ነገሰ፡፡ አብረውት የመጡን ነገደ እስራኤላውያንም በየሙያቸው እየደለደለ በየክፍለ ሀገሩ እንደተላኩና በዋናነት እየተመደቡ ከተላኩባቸው ቦታዎች ውስጥ ጥንት መስዋዕተ ኦሪት ይሰዋባቸው ከነበሩት በስመጥሮቹ በአራቱ መናብርተ ጽዮን በጊዜ ቅደም ተከተል አክሱም ጽዮን፣ መርጡለ ማሪያም፣ ተድባበ ማሪያምና ጣና ቂርቆስ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ጎጃምን እንዲያስተዳድር የተላከው እስራኤላዊው አለቃ ኤፍሬም እንደነበርና እርሱም ከሰሜን ኢትዮጵያ አክሱም ተነስቶ ጎጃም ምድር እንደገባ ርዕሰ ከተማውንም በፊት ነገደ ካም ወይም የኩሽ ልጆች ይኖሩባት ከነበረው መርጡለ ማሪያም ገዳም ላይ እንዳደረገ፣ አብረውት የመጡትን አለቆችን በመላው እየመደበ እንደላካቸው፣ ከዚያም ጠበብተ እስራኤልና ሌዋውያን ካህናትን ደግሞ የኦሪትን ህግና ስረዓት ጠብቀው በሀገረ እግዚያብሄር መርጡለ ማሪያም ቤተ ምኩራብ እንዲሰሩ እንዳደረገ እና ከዚህ ዘመን ጀምሮም በዚች ታሪካዊት ገዳም ህገ ኦሪት ሙሉ በሙሉ እየተከናወነ የእግዚያብሄርን ስም እያመሰገኑና መሰዋት እየሰው ለህዝቡ ስርየት በማሰጠት እስከ ዘመነ ሀዲስ ማለትም የሀዲስ ኪዳን አብሳሪዎች አብረሐና አጽብሃ ዘመነ መንግስት ድረስ በመርጡለ ማሪያም ገዳም መስዋዕተ ኦሪት ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመባት (አባ ኃይለ ኢየሱስ(ቆሞስ) መጋቢት፣16፣2011ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

በኦርቶዶክስ ክርስትና የዘመነ ሀዲስ አብሳሪዎች በመባል የሚታወቁት ሁለቱ ምንትያ ወንድማማቾች አብርሃ ወ አጽበሐ (ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት ኢዛናና ሳይዛና በመባል ይታወቃሉ) እነዚህ ሁለቱ ወንድማማቾች ሲነሱ ከዚች ጥንታዊት ገዳም ጋር ስማቸው አብሮ የሚነሳው በሀገራችን የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ የሆኑት አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬ ምናጦስ) ናቸው፡፡

እነዚህ ሁለቱ ቅዱሳን ነገስታት እና ሊቀ ጳጳሱ ከሳቴ ብርሃን ዘመነ ክህነታቸውን በሙሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን በማስፋፋትና አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽ ይታወቃሉ፡፡ ካሳነጿቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ተጠቃሽ ነች፡፡

በዚህ ላይ የፍቁራን አሐው አብረሃ ወ አጽበሐ እና አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬ ምናጦስ)[5] ከአክሱም ጽዮን ተነስተው በወሎ ክፍለ ሀገር አቋርጠው ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር ወሎ መካነ ሰላም ላይ ሆነው የጎጃምን ህዝብ አባይ ወርዶ እንዲቀበላቸው መልዕክት እንደላኩ ፤የጎጃምም ህዝብ ሄዶ እንደተቀበላቸው እና ከአባይ ጀምረው መርጡለ ማሪያም እስከ ደረሱ ድርስ ገቢራተ ታምራትን እንደሰሩ፤(የሰሯቸውን ገቢራተ ታምራትና የተናገሯቸውን ትንቢት ነክ ተረኮች ወደ ፊት በተረክ ክፍል የምናየው ሆኖ) በሰባተኛው ቀን ጽርኃ አርያም ማለትም ወደ ዛሬዋ መርጡለ ማሪያም እንደደረሱ፣ የቦታዋን አቀማመጥና የኦሪቱን ምኩራብ ቤተ ፀሎት አይተው አድንቀው ቤተ ፀሎቱ ታሪኩን እንደያዘ ይቀጥል፤ እኛም የቡሉይ ኪዳንን ቤተ ፀሎት ከሀዲስ ኪዳን ቤተ ፀሎት ጋር አናጠጋጋም በአንጻሩ ይታያዩ እንጅ ብለው ተስማሙ፡፡

በዚህ ጊዜም ቦታው ደስ ስላላቸውና ምንም ችግር ሳይገጥማቸው ከዚህ ቦታ ስለደረሱ ለሁለተኛ ጊዜ መጠሪያ ስሟን ‹‹ሀገረ ሰላም›› ብለው ሰየሙ (አባ ኃይለ ኢየሱስ (ቆሞስ)፣ መጋቢት፣17፣2011ዓ.ም) ብለው ነግረውኛል፡፡

ይህን የሀዲስ ኪዳን ጸሎትም በስተምስራቅ በኩል ባለው ተራራ ለመስራት ጀምረው ሳለ መሬቱ እንደእሳት ትንታግ ያለ ቦግ እያለ ስላስቸገራቸውና በግንበኞች ላይም የጤና ችግር ከማስከተሉም በላይ ቀን ሰርተውት የዋሉት ግንብ አድረው ሲያዩት እየፈራረሰ ስላስቸገራቸው፣ አባ ሰላማ ‹‹ወደ ዚህ ቦታ ስንመጣ አንድም ችግር ሳይገጥመን ህዝቡም በሰላም ተቀብሎን ደስ ብሎን ሳለ የእግዚያብሄርን መመስገኛ ቤት እንስራ ባልን ጊዜ ይህ ፈተና የገጠመን እግዚያብሄር ጥበቡ አይመረመርም እና የእግዚያብሄርን ፈቃድ በሱባኤ

---


[5]አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬ ምናጦስ) ሀገራቸው ግሪካዊ ሲሆኑ ኢዛናና ሳይዛናን በሃማሴን አውራጃ በማጥመቅ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት እዲቀበሉ በማድረግ ስማቸውንም አብረሃ እና አጽብሐ እንዲባል ያደረጉ አባት ናቸው (ፍስሃ፣ 2003፣154፡፡)
አባ ስላማ ማለት ከነበራቸው ግብር የተነሳ ‹‹የሰላም አባት››፣ ከሳቴ ብርሃን ደግሞ ‹‹ብርሃን ገላጭ›› የሚል ትርጉም ያለው እንደሆነ ዳኛቸው ካሳሁን /መላከ ሰላም/፣ (1999፣145) ይገልጻሉ፡፡

እንጠይቅ›› ሲሉ ሀሳብ አቀረቡ፡፡ በዚህም ተስማምተው ንጉስ አብረሃ መሰረቱ ከተጣለበት ከአብርሂ ተራራ (ግንበ ወሬ)፣ ንጉስ አጽበሐ ዜነዎ ከሚባለው ቦታ፣ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬ ምናጦስ) ሰላምጌ፣ የኦሪቱ ሊቀ ካህን ሚናስ ቢታኒያ፣ የሀዲስ ኪዳኑ ሊቀ ካህን ደግሞ ሀዲስጌ ከተባሉ ቦታዎች ላይ ሆነው ቤተክርስቲያኑ የሚሰራበትን ቦታ እግዚያብሄር እንዲመራቸው በጽሎት ሱባኤ ገቡ ሲሉ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቹና የጽሁፍ ሰነዶችም ጭምር ያስረዳሉ፡፡

ሱባኤ በገቡ በሶስተኛው ቀን ሁሉም አንድ አይነት ራዕይ አዩ፡፡ እሱም ህንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ሊሰሩ ከፈለጉበት ቦታ ግንብ በወሬ፣ /በወሬ የቀረ ግንብ ለማለት ነው/ አስራ ሁለት በር ያለው የብርሃን ድንኳን ተዘርግቶ ከውስጡ መልከ መልካም ጎልማሳ ተቀምጦ መላእክት መሰል ሰዎች ከድንኳኑ ውስጥ ካለው ሰው ላይ ሲደርሱ ሰግደው ሲወጡ ሲገቡ አያዩ ያ ባለአስራ ሁለት በር የብርሃን ድንኳን ተነስቶ ቀደም ሲል የሀዲስ ኪዳን ቤተ ፀሎት ከብሉይ ኪዳን ቤተ ፀሎት (ምኩራብ) አናጠጋጋም ወደ ተባለበት ቦታ ሄዶ ሲያርፍ ድንኳኑ ሜዳውን ሞልቶ ወደ ላይም ሰማይ ገጭቶ ሳለ እኒያ መላእክት መሰል ሰዎች እጅግ በዝተውና ሜዳውን ሞልተው ሰው በሰው እየሆኑ ከድንኳኑ ውስጥ ካለው ሰው ላይ ሰግደው ሲወጡ ሲገቡ እንዳዩ እና በማግስቱ ሲነጋ ሱባያቸውን ጨርሰው ከቦታው ሲገናኙ በአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬ ምናጦስ) አማካኝነት መጀመሪያ ያየውን ራዕይ እንዲናገር የተጠየቀው ንጉስ አጽበሐ ነው፡፡ ራዕይም ተመሳሳይ ሰለነበረ ከላይ የተባለውን ቃል በቃል ተናገረ፡፡ ወንድሙ አብረሃም ሆነ ሌሎች በተራ ሲጠየቁ ፊት ከተነገረው ጋር ተመሳሳይ እንደሆነና በዚህም ምክንያት ያንን ቦታ ትተው ‹‹እግዚያብሄር ወደ መራን ቦታ እንሂድ›› በማለት ወንዙን ተሻግረው ከአምባው ሲደርሱ ተራራ አህሎ ይታይ የነበረው ቤተ ምኩራብ ከነሙሉ ዕቃው ተሰውሮ ለምለም ሳር በቅሎበት አገኙት በዚህ ጊዜም እጅግ በጣም ደስ ስላላቸው ለሶስተኛ ጊዜ ስሚን ‹‹ጽረሃ አርያም[6]›› ብለው ሰይመዋታል፡፡ በማለት ገድለ አብረሃ ወ አጽበሐን ጥንታዊ የብራና መጽሀፍ ዋቢ አድርገው (አባ ኃይለ ማሪያም፣ መጋቢት፣18፣ 2011 ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

---

[6]ጽርሃ አርያም ማለት ስማየ ሰማያት፣ ከሰማያት ሁሉ በላይ ያለች ሰማይ ማለት ነው፡፡




---

[7] ‹‹ዜነወ›› ማለት ነገረ፣ ተናገረ ወይም ተነጋገረ ማለት እንደሆነ አባቶች ይናገራሉ፡፡
‹‹ሰላምጌ›› ደግሞ ፍሬ ምናጦስ በሱባኤ እንዳሉ እመቤታችን ተገልጻ በታየቻቸው ጊዜ ‹‹ሰላም ለኪ ኦ ቅድስት ድንግል›› (ፀጋን የተሞልሽ ቅድስት ድንግል ሆይ ለአንች ሰላምታ ይገባል) ብለው አመስግነው ስለነበር እንደ መነሻ ሆኖ እስካሁን ‹‹ሰላምጌ›› እየተባለ ይጠራል ሲሉ አባቶች ይናገራሉ፡፡

ደ

የኦሪቱ ሊቀ ካህን ሚናስ ሱባኤ የገባበት ቦታ ቢታኒያ[8]

**ምስል፡-2 ሱባኤ የያዙበት ቦታዎችንና አቅጣጫን የሚጠቁም ስእላዊ መግለጫ፡፡**

ሰለዚህ ለዚህ ነገር ንጉስ አብረሃ እና አጽበሐ ያስገነቡት ቤተ መቅደስ እየተባለ የሚጠራው ባለአስራ ሁለት ቤተ መቅደስ ቀሪ ፍርስራሽ ማረጋገጫ ነው፡፡

ሌላው የዚህ ቤተ ክርስቲያን ለአራተኛ ጊዜ አሁን ወደምትጠራበት ስም የተቀየረው ፊት ላይ በራዕይ ተገልጾላቸው የነበረውን ቤተ መቅደስ በእግዚያብሄር እረዳትነት በፍጥነትና በጥራት ከጨረሱ በኋላ ጥር 21 ቀን 333 ዓ.ም እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ ላይ በየካቲት 30፣ 2011ዓ.ም ከፋሲካው ደጀን (መ/ር) ጋር ባደረኩት ቃለ መጠየቅ የሚከተለውን ነግሮኛል፡፡

ቤተ መቅደሱ በሚሰራበት ወቅት ሲሰሩ የዋሉት በሶስት እጥፍ አድጎ ያገኙት ስለነበር በአጭር ጊዜ ጥር 21 ቀን 333 ዓ.ም ተጠናቆ አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን (ፍሬ ምናጦስ) ቤተ መቅደሱን ባርከው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማሪያምን የቃል ኪዳን ታቦት ደናግል መነኮሳት ይዘው፣ ምዕመናን በዕልልታ፣ ካህናት በዝማሬ ዙረው ወደ ቤተ መቅደሱ ሲገቡ አብረሃና አጽበሐ እንዲሁም አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን ሌሎችም እግዚያብሄር የገለጠላቸው ቅዱሳን ሰዎች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ከታቦተ ህጉ ፊት ወደ ቤተ መቅደሱ ከልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስትገባ በግልጽ ስለታየቻቸው ፊት ጸርሃ አርያም ይባል የነበረውን ጽርህን ወደ መርጡል፣ አርያምን ወደ ማርያም በመቀየር ለአራተኛ ጊዜ ‹‹መርጡለ ማሪያም›› ብለው ሰየሟት፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የገዳሚም ሆነ የአካባቢው መጠሪያ መርጡለ ማሪያም ተባለ ሲል ያስረዳል፡፡

በመቀጠል ለመጀመሪያ ጊዜ የኦሪቱን ሊቀ ካህን ሚናስን የርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም በወቅቱ በአክሱም ጽዮን ይፈጸም እንደነበረው ስረዓት የወርቅ

---

[8] ቢታኒያ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ የሚገኝ መንደር፤ ዮሐ. 1፣28፡፡

ዘውድ አስደፍተው የገዳሚ ኤጲስ ቆጶስ በማድረግ ርዕሰ ርዑሳን[9] አድርገው መሾማቸውን መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# 3.ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት ክፍሎች የሚኖሩ ሲሆን የመጀመሪያው ለጥናቱ እንደመንደርደሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሚቃኙበት የንድፍ ሀሳብ ክፍል ሲሆን በሁለተኛ ደረጃነት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም የተጠኝ አካባቢና የማህበረሰቡ ዳራዊ ገለጻ እንዲሁም የገዳሚን ታሪካዊ አመሰራረት እንመለከታለን፡፡

## 3.1 ንድፍ ሀሳባዊ ቅኝቶች

ለጥናቱ መሳካት በዋናነት ትኩረት የምንሰጣቸው የሀይማኖት ምንነት፣ የገዳም ምንነት፣ ተረኮች ፣ ተረክን የማጥናት አስፈላጊነት እና የአጠናን ስልት ናቸው፡፡ በዚህ ዙሪያ ምሁራን የሰነዘሯቸውን ሀሳቦች አጥኝው ይጠቅሳል፡፡

### 3.1.1 የሃይማኖት ምንነት

ሃይማኖትን በተመለከተ አንድ ወጥ የሆነና ሁሉንም ሊያግባባ የሚችል ብያኔ መስጠት ከባድና አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም የሃይማኖት ዓይነቶች መብዛትና የአስተምህሮ ልዩነት መኖር የመጀመሪያው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ እምነቱ በራሱ ይዞት የሚነሳው የሰው ልጅና የተፈጥሮ ጉዳይ መሆኑ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ሲሰነዝሩ ይታያል፡፡ ለዚህም ከዚህ በታች ያሉት ገለጻዎች ማሳዎች ናቸው፡፡

---

[9]በወቅቱ የቤተ ክርስቲያኑ የአስተዳደር ወሰን ከቆማ እስከ ሶማ፣ ከእናውጋ እስከ ሰንጓጓ ነበር፡፡ ይህ ማለት ቆማ ደቡብ ጎንደር ቆማ ፋሲለደስ ሲሆን፣ ሶማ ደግሞ ምስራቅ ጎጃም እናርጅ እናውጋ (ደብረ ወርቅ) ወረዳ ነው፤ ስንጓጓ ደግሞ ደቡብ ወሎ በአጠቃላይ ጎጃም በሙሉ እንደነበር አባቶች ይናገራሉ፡፡

የደብሯም /የገዳምነቷም/ መጠሪያ ‹‹ርዕሰ ርዑሳን›› ሲሆን፣ የአስተዳዳሪው ማዕረግ ደግሞ ‹‹ርዕሰ ርዑሳን›› እንደሆነ ሐመር መጽሄር፣ ህዳር፣ 2005 ዓ.ም ያስረዳል፡፡ ርዕሰ ርዑሳን ማለትም ‹‹የአለቆች ሁሉ አለቃ›› ማለት ነው፡፡

Tylor (ዓመተ ምህረትና ገጽ ያልተጠቀሰ) ‹‹ሃይማኖት በመንፈሳዊ ነገሮች ማመን ነው፡፡›› በማለት በአጭሩ ሲገልፀው፣ Frazer, (ዓመተ ምህረትና ገጽ ያልተጠቀሰ) ደግሞ የሰው ልጅን እና ይህችን ዓለም ከፈጠረና ከሚቆጣጠር መለኮታዊ ኃይል ጋር መለማመን፣ ይቅርታ መጠየቅ፣ መታረቅ፣ ስምምነት መፍጠር እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የእነዚህ የሁለቱ ምሁራን ሃሳብ በተለያየ መንገድ የተገለፀ ቢሆንም ዋናው ጭብጥ ግን ሃይማኖት ማለት በምድር እንዳለንም ሆነ ከሞትን በኋላ የተሻለ ነገር እንዲገጥመን ማድረጊያ መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡

በመቀጠል ደግሞ የDurkeim (1995) ገለጻ ሲሆን ሀይማኖት ማለት ከተቀደሱ ነገሮች ጋር በተየያዘ የሚፈፀም የእምነቶች ስረዓት ነው፡፡ አማኙ ማህበረሰብ ማድረግ የሚገባውን በእምነቱ ህግ ተለይቶ የተቀመጠ፣ በቤተ እምነታቸው አማካኝነት እንዲያውቁት የሚደረግ፣ ማህበረሰቡ በሚትና በክበራ መልክ የራሱን ማንነት የሚያፀናበት መሆኑን ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ ሃይማኖት መንፈሳዊ ነገር የሆነና ለሰው ልጅ ወደዚህ ምድር መምጣትና ተመልሶ መሄድ (በህላዌና በሞት ጊዜ) ለሚሆነው ነገር መልስ የሚሰጥ እንደሆነ፤ ለምንኖርባት ቁሳዊ ዓለምም አፈጣጠርና ፍጻሜ እንደየ እምነቱ ዓይነትና ቀኖና /dogma/ የራሱ መልስ ያለው መሆኑን፤ ሌላው ደግሞ አማኙን ማህበረሰብ ማድረግ የሚገባቸውን ግብረገባዊ የሆኑ ነገሮችን በሚትና በስረዓተ ከበራ መልክ እንደሚያስተምሩና እንደሚያንጹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 3.1.2 የገዳም ምንነት

ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቴ በፊት ለመንደርደር ይመቸኝ ዘንድ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮችን ላንሳ፤ የመጀመሪያው የጥናቱ መነሻ ማዕከል የሆነው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ሲሆን ይህ እምነት ወደ ሀገራችን የገባው በኢዛና ዘመነ መንግስት እንደሆነና ጊዜውም በአራተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ መሆኑ ተደጋግሞ የተባለ ጉዳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ቀኖና /dogma/ ነው፡፡ በዚህ እምነት ውስጥ በርካታ ሃይማኖታዊ የቅኖና ህጎች ሲኖሩ የገዳም ቅኖና አንዱ ነው፡፡ በገዳም ውስጥ የሚኖሩ መነኩሳትና መነኩሳይት የሚያከናውኑትን መንፈሳዊም ሆነ ማህበራዊ ተግባራት መኖራቸው የታወቀ ሲሆን ተግባራቱ የሚከወኑት በዘልማድ ሳይሆን መጽሃፈ መነኮሳት የሚባለውን መጽሃፍ መሰረት

ተደርጎ እንደሆነ ዳኛቸው (1991፣178) ይገልጻል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡ ስለገዳም ምንነት የሚያወሱ ሀሳቦችን እንመለከታለን፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት (1962፣238) ላይ ገዳም፤የመናኞች፡ ባህታውያንና፡ መነኮሳት፡ መኖሪያ፤ ዓለማዊ፡ የሌለበት፡ ስፍራ፤ በማለት ያብራሩታል፡፡

አዲሱ ዓለም አቀፍ ‹‹ዌብስተር››አጠቃላይ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት (ገጽ፣821) ‹‹ገዳም ሀይማኖታዊ ቃልኪዳንን/መሀላን/ መሰረት አድርጎ በጠበቀ ሁኔታ፣በታወቁ ሰዎች የተያዘ የመኖሪያ ቦታ ሲሆን በተለይ መነኩሴዎች/መናኞች/ እና በመሰል አይነት ሁኔታ የሚኖሩ ሰዎች መኖሪያ ቦታ ነው፡፡›› ይለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናት እና ምርምር ማእከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣507) ደግሞ፣ ‹‹ገዳም ማለት መነኮሳት ከአለማዊ ኑሮ ተገልለው በሀይማኖት ስርዓት እና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተክርስቲያን ያለበት ቦታ፡፡››በማለት ይገልጸዋል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ገዳም ገባ ሲባል አለማዊ ኑሮውን በመተው መንፈሳዊ ኑሮውን ለመኖር ጀመረ ማለት ነው፡፡

Cantale & etal የገዳማት ዓላማ በመጀመሪያ ራስን ከምቾት በማራቅ፣ የገዳማትን ገዳማዊ ህግና ደንብን በመከተል በቡራኬ በመናኝነት እና በብቸኝነት የህይወት ዘዬ የመነኮሳት መኖሪያ ቦታ ነው (29 Jun 2018)፡፡ ሲሉት፡፡

Blazewicz (1999, 32) ገዳማዊነት የሚለው ቃል “Monos” ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም “ነጠላ” ማለት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይህ ማለት ገዳም ከምንም ዓለማዊ ኑሮ ተገልሎ በመንፈሳዊ ኑሮ የሚኖርበትን ስፍራ ጠቋሚ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የምንረዳው ገዳም ማለት ሀይማኖታዊ ህግና ደንብ በማክበር ከዓለማዊ ኑሮ ተገልለው በንፅህና በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን እየለመኑ የሚኖሩበት የተቀደሰ ቦታ ነው፡፡

### 3.1.3 የገዳማዊ ህይወት አጀማመር በኢትዮጵያ

የገዳማዊ ህይወት አጀማመርን በተመለከተ በአንድ በኩል በሰሜናዊው የሀገራችን ክፍል በአምስተኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ አካባቢ በዘጠኙ ቁዱሳን እንደሆነ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዚያ በፊት በአብረሃና ወ አጽበሐ /ኢዛናና ሳይዛና/ በተባሉ የአክሱም ነገስታት ዘመነ መንግስት ጊዜ በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬ ምናጦስ) እንደሆነ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በነዚህ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ላይ ከተባሉት ውስጥ የመላከ ሰላም ዳኛቸው ካሳሁንንና  ምትኩ ደምሌን (መ/ር) ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም) (1999፣ 172) ገዳማዊ ህይወት በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል በትግራይ ዋና ከተማ አክሱም አካባቢ የተወሰነ ነበር የመጀመሪያው የገዳማውያን ማህበረሰብ በአምስተኛው ምዕተ አመት ዘግየት ብሎ ከሚዲትራኒያን ባህር አካባቢ /ምናልባትም ከሶሪያና ከግብጽ/ በመጡ ጥቂት /ዘጠኝ/ መነኮሳት እንደተመሰረተ ይነገራል፡፡ ከዚሁ የተቀደሰ ተልዕኳቸውና መንፈሳዊ ህይወታቸው የተነሳ ተሰዐቱ ቅዱሳን ተብለዋል፡፡ በነዚህ ቅዱሳን ከተመሰረቱት ገዳማት በጣም ታዋቂ የሆነው ደብረ ዳሞ የተቋቋመው ከተሰዐቱ ቅዱሳን መካከል ስማቸው ጎልቶ በሚታወቀው ቀድሞ ዘ-ሚካኤል በኋላ አቡነ አረጋዊ በሚባሉት ቅዱስ ነው፡፡ ይላል

ሌላው ደግሞ ከመቀሌ ከተማ 40 ኪሎ ሜትር በመኪና ከተጓዙና ሀገረሰላም የምትባል ከተማ ከደረሱ በኋላ የአራት ሰዓት የእግር መንገድ በመሄድ የሚገኘው ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ሀገራችን ከመግባታቸው በፊት በአብረሃና አጽበሐ /ኢዛናና ሳይዛና/ በተባሉ የአክሱም ነገስታት ዘመነ መንግስት ጊዜ በራሱ በጻድቁ በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሀን የተገደመው ገዳም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ገዳም እንደሆነ  ምትኩ ደምሌ (መ/ር) 1995፣2) ያስረዳሉ፡፡ በሀገራችን በብዙ ታሪካዊ ጉዳዮች ላይ ካለው ትክክለኛና ታማኝ ጽሁፋዊ ማስረጃዎች ማነስ የተነሳ የሀሳብ ልዩነቶች፣ ክርክርና ውዝግብ መኖር የተለመደ የሚመስል ቢሆንም ከተጠቀሰው ጊዜ አንጻር የሁለተኛው ገዳም የቀዳሚነትን ደረጃ ይይዛል፡፡ ስለሆነም በሀገራችን የመጀመሪያው ገዳም የተገደመው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በትግራይ መሆኑ ነው፡፡  (ዳኛቸው ካሳሁን /መላከ ሰላም/፣ 1999፣133-34) ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በታች የሚገኙ ሌሎች ተጨማሪ የዳኛቸው፣ የሉሌን እና የያረጋል አበጋዝ ዝርዝር ሀሳቦች እንመልከት ‹‹ጻድቃን›› በመባል የሚታወቅ የመነኮሳት ማህበር በሰነአፌ ደቡብ

/በአሁኑ ጊዜ ደቡብ ምስራቅ ኤርትራ/ መጠራ፣ ባረክነሃ አካባቢና በደቡባዊ ሽመዛና ወንጌልን ይሰብኩ እንደነበር (ያረጋል፣1993፣18) ያስረዳሉ፡፡

ሌላው የተወሰኑ ገዳማት በሁለቱ ነገሥታት በአብርሀ እና አጽበሃ /በ4ኛው ምእተ ዓመት/ እንደተመሠረቱ ይገለጻል፡፡ ከዚያ ዘግየት ብሎ በገዳማት ምሥረታ የታወቁ ሌሎች ነገሥታት መኖራቸው ይነገራል (ዳኛቸው 1999፣172)

በመቀጠልም በከፍተኛ ደረጃ የታወቁት አበው እስከተነሡበት እስከ 13ኛው ምእት ዓመት ድረስ ስለገዳማዊ ህይወት የሚያስረዱ ሰነዶች ብዙ እንዳልነበሩ እና የደብረ ዳሞው የአቡነ ዮሐኒ መንፈሳዊ ልጅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ በ1287 እንዳረፉ፣ የመነኮሳት እስከ ዛሬም የገዳማዊነት ማእከል በሆነው በደብረ ዳሞ መሆኑን፣ አቡነ ኢየሱስ ሞአ በ1248 ወደ ቤተ አምሃራ፣ ማለትም የእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ወደሚገኝበት ወደ ሃይቅ ተጉዘው የደብረ ሀይቅ እስጢፋኖስን ገዳም መንፈሳዊ ት/ቤት እንዳቋቋሙ፡፡ ገዳሙ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ (13ኛው ምእት ዓመት) ጋራ የቀረበ ግንኙነት እንደነበረው፣ የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ደቀ መዝሙርና በጣና ሀይቅ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መሥራች እንደነበሩት እንደ አቡነ ኂሩተ አምላክ ያሉት ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶች ከገዳሙ የተገኙ ወይም በገዳሙ መንሳዊ ህይወት እየተሳቡ ከሌላ ቦታ የመጡ ናቸው ሲሉ (ሉሌ፣1997፣60-61) ይገልጻሉ፡፡

በጣና ሀይቅ ደሴቶች ዙሪያ የገዳማዊ ህይወት ምሥረታ የተጀመረው ቢያንስ በ14ኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመን ነው፡፡ በጣም ታዋቂ ከሆኑት የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ተክለ ሃይማኖት ናቸው፡፡ (ዳኛቸው፣1999፣173)፡፡ ተክለ ሃይማኖት ወደ ምዕራቡ የሀገሪቱ ክፍል በመሄድ በ13ኛው ምእተ ዓመት መጨረሻ በሸዋ ውስጥ የደብረ አስቦን (ኋላ በ1445 ደብረ ሊባኖስ የተባለውን) ገዳም አደራጅተው አቋቁመዋል፡፡ ብዙ ገዳማትን በመመሥረት እጅግ ታዋቂና ተደማጭነት የነበራቸው ሌላው መነኩሴ በትግራይ ገረአልታ ውስጥ የነበሩት የታላቁ መናኝ የአቡነ ዳንኤል የእኅት ልጅ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ናቸው (ዳኛቸው፣1999፣133-134)፡፡

### 3.1.4 የተረክ ምንነት

“ Oral Narrative” የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በሀገራችን የስነጽሁፍና የፎክሎር ምሁራን የተለያየ መጠሪያ ሲኖረው ይስተዋላል ፈቃደ (1991፣52) “ተረት” ዘሪሁን (2005፣28) “ተረት”፣ ሰሎሞን (2007፣83) “ቃለ ትረካ”፣ ቴዎድሮስ (2001፣259-260)”ተረክ” በሚል ይገልጹታል፡፡ ከተዘረዘሩት ስያሜዎች በጥናቱ ውስጥ ተረክ የሚለውን ቃል የሚጠቀም ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ይህ ቃል ከሌሎች በጽንስ ሀሳብ ደረጃ በዝርውና በግጥም መልክ፣ ቃላዊና ጽሁፋዊ የተረክ ዓይነቶችን እንዲሁም ትወናዊ፣ቁሳዊ ወዘተ ነገሮችን ጠቅልሎ የመያዝ አቅም ያለው ቃል በመሆኑ ነው፡፡

ተረክን የተለያዩ ባለሙያዎች የተለያየ ስያሜ መስጠታቸው ብቻ ሳይሆን በብያኔው ላይም ልዩነቶች መኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተረክን ቃል ትረካ ብለው የሚጠሩት የተረኮቹ መተላለፊያ መንገድ ‹‹አፋዊ›› መሆኑን ያምናሉ፡፡ለምሳሌ፡-ሰሎሞን (2007፣83) ቃል ትረካ (Oral Narrative) አንዱ የስነቃል ዘርፍ ሲሆን፣ የሰዎችን የማስታዎስ ችሎታ መሰረት በማድረግ በቃል ለብዙ ዘመናት ሲተላለፍ የኖረና ለዛሬው ትውልድ የደረሰ ነው፡፡ቃል ትረካ በዝርው የትረካ (prose narrative) ስልት የሚቀርብ ሲሆን፣ ስለሚነገረው ሁነት (event) ሰፋ ያለ ማብራሪያ ወይም መግለጫ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ ጥበብ የሰው ልጅ ከልደት እስከ ሞት የሚጓዝበትን ሕይወት የሚገልጽበት በመሆኑ በማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡

ተረክ የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ባህል፣ ልማድ፣ ገጠመኝ፣ እምነት ወዘተ ማስተላለፊያ መሳሪያ መሆኑን፣ ምንም እንኳ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የሚመጣ ሀብት ቢሆንም እንደጊዜውና እንደወቅቱ አብሮ ሊለወጥ የሚችል መሆኑና ማህበረሰቡን የማስተማር፣ የማዝናናት፣ መልዕክት የማስተላለፍ ዓላማ ይዞ እንደሚቀርብ ቀጣዩ ሀሳብ ዋቢ ነው፡፡

ተረክ ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶች፣ ሁነቶች እና ክስተቶች የሚፈጸምበት፣ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታና ጊዜ የሚያሳይ፣ የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ልማድ፣ ባህልና እምነት የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ፈጠራውና ተስተላልፎቱ ቃላዊ የሆነ፣ ከአንድ ትውልድ በላይ የሚዘልቅ፣ ከሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ እንደየ ዘመኑ ማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታ እራሱን በመቀያየር የሚኖርና የሚተረክ ነው፡፡ ተረክ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል በማሳየት በማህበረሰቡ የዕለት ከዕለት የህይወት መስተጋብር

ወይም በልዩ ማህበራዊ ገጠመኞች ላይ አድማጮችን የማዝናናት፣ የማስተማርና፣ መልዕክት የማስተላለፍ ዓላማን ይዞ እንደሚቀርብ ያትታል(Oring፣1986፣122)፡፡

ተረክ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ወይም በጽሁፍ፣ በግጥም ወይም በዝርው መልክ ሊተላለፍ እንደሚችልና ታሪኩን፣ተረካውን፣የታሪኩን አውድ በሙሉ ጠቅልሎ የሚይዝ ዕሳቤ መሆኑን ምሁራን ይስማማሉ፡፡

በዚህ ላይ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፣259-60) ተረክ (Narrative)፡ ታሪኩን፣ ታሪኩ የሚቀርብበትን ሁኔታና መንገድ ሁሉ ጠቅልሎ የሚይዝ ጽንስ ሀሳብ ነው፡፡ በሰፊ አገባቡ ተረክ በቃል አልያም በጽሁፍ ሊቀርብ፣ በግጥም ወይም በዝርው ሊተረክ ይችላል፡፡ ከዚህም አልፎ ሊዘፈን፣ ሊተወን፣ ሊደነስ፣ ሊሳል ፣ሊቀረጽ፣በተለያዩ መንገዶች ሊከወን የሚችልም ቅርጽ ነው ሲል ያብራራል፡፡

### 3.1.4.1 የተረክ ዓይነቶች

ስለተረክ አይነቶች ሁሉን ሊያስማማ የሚችል ወጥ የሆነ ምደባ እስካሁን አልተገኘም፡፡ ብዙ የዘርፉ ባለሙያዎች በሚከተሏቸው የመመደቢያ መስፈርት መለያየት ምክንያት በርካታ የሆኑ የተለያዩ የምደባ አይነቶች አሉ፡፡ ከመመደቢያ መስፈርቶች መካከል ገጸባህሪያትን መሰረት ያደረገ፣ ይዘትን፣ ታሪክን፣ ከየትመጣነትን፣ አውድን ወዘተ መሰረት ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ኦሪንግ (1986) ዋና ዋና የተረክ ዓይነቶች በማለት ምሁራን ይስማሙባቸዋል ያላቸውን ሶስቱን የተረክ “Oral Narrative” አይነቶች ላይ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ምሁራን የሰጡትን ብያኔ እናያለን፡፡

#### 3.1.4.1.1 ተረት

ተረት ለተራቹ ማህበረሰብ የሚሰጠው ጠቀሜታ በጣም ብዙ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ፈቃደ (1991፣52-53) በጥንቱ ዘመን ሰዎች ተረት በመተረት ጊዜ ያሳልፋሉ፣ይዝናኑ፣ ይደሰቱ፣ ይማሩ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በተመስጦ ያነቧቸዋል፣ያዳምጧቸዋልም፡፡ስለ አማልክትም፣ ስለ ቅዱሳንም፣ ስለነብያትም ወዘተ. እንዲሁም በተመስጦ ያነባሉ፣ ያዳምጣሉ፣ ከነዚህ ክንዋኔዎች ደስታን፣ ትምህርትን፣ ምግባርን ወዘተ. ይቀስማሉ፡፡

እንደየሁኔታው፣ የህይወትን ምስጢራዊነት፣ የደፋር ገጸባህሪያትን ጀግንነት፣ የፈሪዎችን ቡርቂነት፣ የሰላዲዎችን ከንቱነት፣ የቅኖችን የዋህነት ፣የአታላዮችን መሰሪነት፣ ወዘተ ይመለከታሉ፡፡ ከነዚህ ተረቶች የሚገኘውንም እውቀት ቄሱ በስብከቱ፣ ካድሬው በዲስኩሩ፣ አበውና እናቶች በወግ በጫዋታና በምክራቸው ይገለገሉበታል፡፡ ስለዚህ ተረት ንቁ ህይወታዊ ክንዋኔ ነበር፣ አሁንም እንደዚህ የሆነበት ቦታ ጥቂት አይደለም፡፡ ጾታን፣ እድሜን፣ መደብን ብዙም ሳይለይ ሰዎችን ሁሉ ይስባል፡፡ ጥሩው ተራችም እንደ የማህበረሰቡ ቋንቋና ፈሊጥ ይደነቃል፣"እገሌ ጨዋታ ያውቃል!" እገሌ ሰያሚ ነው!" የመሳሰሉት አባባሎች የአማርኛ ተናጋሪዎች የአድናቆት እና የአክብሮት መገለጫዎች ናቸው በማለት ተረትን የማህበረሰብ አጠቃላይ ርዕዮት መገንቢያ አድርጎ ያስቀምጠዋል፡፡

አንዳንዶቹ ደግሞ ተረትን ዋና ዋና ከሚባሉት የተረክ አይነቶች ውስጥ በሶስተኛ ደረጃነት እንደሚቀመጥና በተረቱ የሚባሉ ዝርው ተረኮች እውነት ናቸው ተብለው የማይታመኑ ነገር ግን ለተለያየ አላማ እንደሚያገለግሉ ይገልጻሉ፡፡ የሚከተለውም ብያኔ ይህን ያሳያል፡፡

Finnegan (1992፣156) ‹‹ለሚት እና ሌጀንድ እንደማሟያ ሆኖ በብዙ ምደባዎች ላይ እንደ ሶስተኛ ክፍል ይቀመጣል›› በማለት ከገለጸች በኋላ ‹ተረቶች በዝርው የሚቀርቡና እንደ ፈጠራ/ልቦለድ/ ይታያሉ፡፡ነገሮች ተፈጠሩም አልተፈጠሩም እንደ ህግም ሆነ ታሪክ አይቆጠሩም ለመዝናኛ ወይም መደሰቻነት ይባላሉ እንጅ› ›› በማለት የBascom (1992፣ 156) አገላለጽ ቃል በቃል አስቀምጣለች፡፡

የተረት ገጸባህርያትን በተመለከተ ምሁራን ከሰው ባሻገር ሌሎች እንስሳትና አሉ ተብለው የሚታመንባቸው ቅዱስም ሆነ እርኩስ መናፍስት ሊሆኑ እንደሚችሉ፡-

ቴዎድሮስ (2001፣259) ተረት፡ መቼት የሚያደርገው ጊዜና ስፍራ በውል አይታወቅም፡፡ ገጸ ባህሪያቱ ሰዎች፣ እንስሳት፣ መናፍስትና ሌሎችም ፍጥረታት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተረት ከሚትና ከአፈታሪክ በተለየ በሚተርከው ማህበረሰብ ዘንድ ጭምር በልብ ወለድነት፣ በፈጠራነት የሚፈረጅ አገረሰባዊ ተረክ በመሆኑ ማህበራዊ ፋይዳው ባመዛኙ ከዚሁ ባህሪው ይመነጫል፡፡ የተረት አላማ በአንድ በኩል ኪነጥበባዊ ደስታና እርካታን ማስገኘት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ትውልድን በምግባር ማነጽ የማህበሩ እሴት ተጠብቆ

ይኖር ዘንድ ማስቻል ነው፡፡ ሁለንተናዊ በሆነ በዚህ ቃል ተረክ አማካኝነት የሰውልጅ ዛሬም ድረስ የገዛ ህይወቱን ይመረምራል፤ መንፈሳዊ ገጽታውን ይረዳል፤ከራሱ ጋር እርቅ እያወረደ የኑሮ ፈለጉን ያስተካክላል፤ያሸነፈውን ዓለም ጭምር መልሶ ድል ማድረጊያው ነው ተረት፡፡

ሰሎሞን ፣ ዘሪሁን እና Bascom ስለተረት ድርጊቶች እውነትነት፣ የሚሳሉ የገጸ ባህሪያትን ምንነት፣ ተረት ከሰው ልጅ ጋር ያለው ቁርኝት እስከምን ድረስ እንደሆነ፣የተረት ተግባራትን እና ባስኮም ንዑስ የተረት አይነቶች የሚላቸውን እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

ተረት በሳይንሳዊ መንገድ ሊረጋገጡ የማይችሉና በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ተዓማኒነት የሌላቸው ፈጠራዊ ድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ ፍሰታቸውን ጠብቀው የሚቀርቡበት የቃል ትረካ አይነት ነው፡፡ ተረት በሴራ ያልተወሳሰቡ ግልጽና ቀጥተኛ የሆኑ ታሪኮችን፣አለም አቀፋዊ ባህርይ ያላቸውን ታሪኮች የሚገልጽና በውስጡም የሚገኙትን ገጸባህሪያት፣ አጋጣሚዎች፣ ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦችና የድርጊቱ ገጽታዎች እንደዋና መሰረታዊ ጭብጥ የሚወስድ ነው (ሰሎሞን፣2007፣86)

ዘሪሁን (2005፣28) “ተረት” መተረት ከተጀመረ ዘመን የለውም፡፡ተረት የማውራት ውስጣዊ ስሜትና ተረት የማደመጥ ፍላጎት ትረካን በስልጣኔ ታሪክ ውስጥ የሰው ልጅ የተፈጥሮ እኩያ እንዲሆን አድርገውታል፡፡” ተረት መተረት የሰው ልጅ በቡድን መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ነበረ የሚባለውም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

Bascom (1965፣4) ተረቶች በዝርው የሚቀርቡና እንደ ፈጠራ/ልቦለድ/ ይታያሉ፡፡ ነገሮች ተፈጠሩም አልተፈጠሩም እንደ ህግም ሆነ ታሪክ አይቆጠሩም፡፡ ለመዝናኛ ወይም መደሰቻነት ይባላሉ እንጂ፡፡ Bascom ተረቶችን የሰው ተረቶች፣ የእንስሳት ተረቶች፣ የማታለያ ተረቶች፣ ረጅም ተረቶች፣ ግራ አጋቢ ተረቶች፣ ቀመራዊ ተረቶች፣ የሞራል ተረቶች ወይም ፋቡላ ብሎ በተለያየ ንዑስ ዓይነቶች መመደብ እንደሚቻል ገልጿ፡፡

McKENDRY /ዓመተ ምህረትና ገጽ ያልተጠቀሰ፡፡/ ለ ተረት ተናጋሪ፣ሚት እና ሌጀንድ እንደ መግቢያ በሚለው ስራው ተረት የሚለውን ቃል የሚገልጸው ከአንድ ሰው ወደ ሌላ እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ ቃላዊ በሆነ መንገድ የሚተላለፉትን የተለያዩ

ተረኮችን ሲያጠቃልል እንደሆነና ዋናዎቹ የተረት አይነቶች ሚትና አፈ ታሪክ ናቸው ካለ በኋላ ፡፡ “The Aarne-Thompson” ዓለም አቀፍ የተረቶች ምደባ ወደ አምስት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚመድባቸው እነሱም፡- የእንስሳት ተረቶች፣ ተራ ተረቶች፣ ቀልድና ተረቶች፣ ቀመራዊ ተረቶችና ያልተመደቡ ተረቶች በሚል ይገልጻል፤ ይመድባል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የምንረዳው ተረት ማለት በዝረው መልክ የሚቀርብ፣ እጅግ በጣም ረጅም እድሜ ያለው፣ የሰው ልጅን የህይወት ገጽታ ማሳያ መሳሪያ የሆነ፣ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ፣ ለመዝናኛ፣ ለቁምነገር ማስጨበጫ፣ ለመደሰቻ፣ ለጊዜ ማሳለፊያ ወዘተ. የሚያገለ ግልና የትረካው ሁነት ተቀባይነት ግን ዝቅ ያለ የተረክ አንዱ ክፍል መሆኑን ነው፡፡

### 3.1.4.1.2 አፈ ታሪክ

አፈ ታሪክ ሁለተኛው የተረክ ዓይነት ሲሆን ባለሙያዎች በሚተረከው ተረክ የጊዜ እርዝማኔ ላይ እና በንዑስ አፈታሪክ  ምደባ ላይ ግልጽ የሆና የቁጥር መስማሚያ የላቸውም፡፡

ፈቃደ (1991፣56-57) የኦክፔውሁ አገላለጽ መሰረት በማድረግ አፈ ታሪክን ሲያብራሩ ይህንን ቃል፣ታዋቂ ግለሰቦችን እና ታዋቂ ድርጊቶችን [ሁኔታዎችን/(evenets)] በሚመለከት ተደጋግመው ለሚተረኩ ተረቶች ብቻ መጠሪያ እንዳደረገው፣ ድርጊቶቹ የተፈጸሙባቸው ጊዜያትም ከዛሬ ጠዋት፣ ከአንድ ሰዓት በፊት ጀምሮ እስከ ጥንት ሊሆኑ ይችላሉ ይላል፡፡ይህንን የጊዜ አመጣጠን በመጠቀምም አፈ ታሪክን በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ሲከፍለው ይገኛል፡፡ አንደኛው <u>ታሪካዊ ሌጀንድ</u>(historical legened) ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ማህበረሰቡ በቀላሉ ሊያስታውሳቸው የሚችላቸውን ድርጊቶችና ግለሰቦችን አስመልክቶ የሚተርታቸውን ይመድባል፡፡...ሁለተኛው <u>ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ ሌጀንድ</u> (romantic or mythic legened) ነው፡፡ ይሄኛው ለተራቹ ምናብ ሰፊ ነጻነት ይሰጣል፡፡ ድርጊቶቹም ሆኑ ግለሰቦቹ የጥንት የሚባሉ ስለሆኑ ተራቹን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ጥያቄ የሚደቅንበትም ሰው ብዙ አይገኝም፡፡

የአፈታሪክን የታሪክ እውነትነት በተመለከተ ብዙ ጸሀፍት በማህበረሰቡ ዘንድ ከእውነት የተቀጠረ እንደሆነና ታሪክ ፈጻሚዎችም በአብዛኛው ሰዎች እንደሆኑ ይስማማሉ፤ በዚህ ላይ ቴዎድሮስ እና ዘሪሁን የሚከተለውን ብለዋል፡፡

ቴዎድሮስ (2001፣262) አፈ ታሪክ(Legend)፡ ባለቤቱ በሆነው ማህበር ዘንድ ከእውነት ተቆጥሮ የሚነገር ቃላዊ ተረክ ነው፡፡ በአፈ ታሪክ ውስጥ ከሚሳሉ ገጸ ባህሪያት መሀል ዋና ዋናዎቹ ባብዛኛው ታሪክ (history) የሚያውቃቸው፣ ተረኩ መቸት ባደረገው ዘመንና ስፍራ በእውን የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ሰዎቹ በታሪክ የተሳተፉባቸው ታላላቅ ሁነቶችና በሁነቶቹ ውስጥ የፈጸሚቸው ተጋድሎዎች (እንደተረኩ ዓይነት፡መንፈሳዊና ዓለማዊ ተጋድሎዎች) በአብዛኛው በተረኩ ውስጥ ስፍራ ያገኛሉ፡፡ አፈ ታሪክ በከፊል ታሪካዊ በከፊል ደግሞ ፈጠራዊ (ምናባዊ) በመሆኑ ቃል ከዋኙ በታሪኩና በፈጠራው መካከል ሚዛን፣ምጣኔና ህብር ይኖር ዘንድ በእጅጉ ይደክማል፡፡አፈ ታሪክ፣ ታሪክ የሚደግፋቸውን ጥቃቅን የሚመስሉ፣ ዳሩ ግን በሰው ልጅነት ውስጥ መሰረታዊ የሆኑ ስሜታዊና ግለሰባዊ ጣጣዎችን ጉዳዬ ይላል፡፡

ዘሪሁን (2005፣31-32) አፈታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገጽታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡ የአፈታሪክ አላማ አንዳንድ አሳሳቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ በታሪክ የነበረው ሰው ያከናወናቸውን ተግባራት መልካምነት ወይም መጥፎነት ለማረጋገጥ ይነገራል፡፡ በታሪክ የተፈጸመ አንድ ድርጊት እንዴት ሊፈጸም ቻለ? ለምን ተፈጸመ? የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ በአፈታሪክ መልስ ይሰጣል፡፡

አፈታሪክ ከትውልድ ትውልድ ከሚተላለፍበት መንገድ አንጻር አንዳንዶቹ ቃላዊ በሆነ መልኩ ሲል ሌሎቹ ደግሞ በቃላዊም በጽሁፋዊ መንገድም ይተላለፋል ይላሉ፡፡ ለአስረጅነት ሀሳብ እንይ፡፡

ሰሎሞን (2007፣93-94) አፈታሪክ (legend) በአንድ አካባቢ ተከስቷል ተብሎ በሚታመን ያለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚነገር ወይም በጽሁፍ የሚተላለፍ የቃል ትረካ አይነት ነው፡፡ ይህ ቃል ትረካም ታሪኩ የተፈጸመበት ቦታ፣ ታሪኩ ተፈጸመ ተብሎ የሚነገርበት ወቅት፣ የተፈጸመው ድርጊት፣ የፈጻሚው ሰው ስም ወዘተ.በአካባቢው ተጨባጭና እውነተኛ ታሪክ ውስጥ ያለና የሚታወቅ ነው፡፡ይህ በመሆኑም አፈታሪክ ማህበረሰቡ እውነት ነው በሚል የሚቀበለው ነው፡፡

ከዚህ በታች ደግሞ ስለአፈ ታሪክ ስረወ ቃላዊ አመጣጥ፣ በድጋሚ ስለተረኩ እውነትነት በውጭ ጸሀፍት እይታ ምን እንደሚመስል፣ የጭብጡ መንፈሳዊነትና ዓለማዊነትን

በተመለከተ፣ የተረኩ የጊዜ እርዝማኔን በተመለከተ፣ ከምደባ ዓይነቶች ውስጥ ለአብነት የተጠቀሱትን፣የተረኩ ፈጻሚ ባለቤቶችም ሰዎች እንደሆኑና ሌሎች ጉዳዮችም ከሚከተለው የ McKENDRY ፣ የ Finnigan እና Bascom ስራዎችን እናያልን፡፡

McKENDRY /ዓመተ ምህረት ያልተጠቀሰ፣ p.2፡፡/ ለተረት ተናጋሪ፣ሚት እና ሌጀንድ እንደ መግቢያ በሚለው ስራው፡-ሌጀንድ የሚለው “legenda” ከሚለው የላቲን ቃል የተገኘ ሲሆን “things to be read” መነበብ ያለበት ነገር ማለት ነው፡፡ በዋናነት የሚያመለክተው ግን በገዳም የሚኖሩ ቅዱሳን የተውጣጣ ምንባቡን ወይም ክስተቶችን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ ታዳሚዎችን የሚያነቃቁበት ነው፡፡ የሚተረከውም  የቅርብ ጊዜ ወይም የሩቅ ታሪክ ሊሆን ሲችል በተራኪውም ሆነ በአድማጭ ሁነቱ እውነት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ታሪካዊ አፈ ታሪክ፣ የግል አፈ ታሪክ፣ አካባቢያዊ አፈ ታሪክ፣ ሀይማኖታዊ አፈ ታሪክ፣ መለኮታዊ አፈ ታሪክ በማለት በአምስት ይከፍለዋል፡፡

አፈ ታሪክ ስላለፈ ነገር የሚያነሳ ከሚትና ከተረት በራሱ የተለየ እንደሆነ፣ ባስኮም እንደገለጸው አፈ ታሪክ ባብዛኛው የሚያነሳው ከቅዱሳን ይልቅ ዓለማዊ ጉዳይ እንደሆነ እና በተረኩ የሚነሱ ገጸ ባህሪያትም ሰዎች እንደሆኑ Bascom 1965a፡4-5 ይገልጻል፡፡

አፈ ታሪክ ዝርው ትረካ ሲሆን ልክ እንደሚት በተራኪውና በአድማጪ፡ እውነት ነው ተብሎ የሚታመን፣ ነገር ግን አፈ ታሪክ ከሚት አንጻር ጊዜው የቅርብ ነው፡፡ አፈ ታሪክ በአብዛኛው የሚያነሳው ከቅዱሳን ይልቅ ዓለማዊ ጉዳይ እንደሆነ እና በተረኩ የሚነሱ ገጸባህሪያትም ሰዎች ናቸው (Bascom 1965፣5) በማለት ይገልጻል፡፡

ለማጠቃለል አፈታሪክ ከቅርብ ክስትተ እስከ ጥንት ያሉ ሰባዊና ተፈጥሯዊ ጉዳዮች ቃላዊ ወይም ጽሁፋዊ በሆነ መንገድ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ፣ እየተላለፈም ያለ፣ ወደፊትም የሰው ልጅ እስካለ ድረስ የሚቀጥል፣ የታሪኩ እውነትነት ተቀባይነት ያለው፤ በስው አዕምሮ ውስጥ መልስ አጥተው ለሚጉላሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች (አብዛኛውን ጊዜ ዓለማዊ) ምላሽ የሚሰጥ የዝርው ትረካ ዓይነት ነው፡፡

### 3.1.4.1.3 ሚት

ሚት ከተረክ አይነቶች ውስጥ ከሰው ልጅ ጋር አብሮ እየተነገረ በመቆየት በእድሜ አንጋፋው እንደሆነ የብዙዎች እምነት ነው፡፡ ይህ ሊሆን የቻለበትንም ምክንያት ባለሙያዎች እንደሚሉት የሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ በአብዛኛው ሀይማኖታዊ ይዘት ያለው በመሆኑና ሰው ወደዚች ምድር ከመጣ ጊዜ ጀምሮ በሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ መልስ ለማግኘት የሚላቸው ብዙዎቹ ከሚታዊ ተረኮች ጋር ስለሚያያዝ እንደሆነ የብዙዎች ስራ ምስክር ነው፡፡ የሚከተለው የBascom እና የFinnigan ማብራሪያም መመልከት ይቻላል፡፡

ሚት በዝርው ትረካ የሚቀርብ፣ በተናጋሪው ማህበረሰብ እምነት እውነት ነው ተብሎ የሚታመን በጥንት ጊዜ የሆነ ሁነት ነው፡፡የሚያነሳውም ጉዳይ በአብዛኛው ሀይማኖታዊ ሲሆን ከስነመለኮትና ከበራ ጋር ይያያዛል (Bascom 1965፣4) ይላሉ፡፡

Finnigan (1992፣138) ሚት በማህበረሰቡ ዘንድ ከረጅም ዓመታት በፊት የተከሰቱና እውነት ናቸው ተብለው የሚታመኑ ድርጊቶች የሚነገሩበት የቃል ትረካ አይነት እንደሆነ ትገልጻለች፡፡

ሚት እንደሚጠቀመው ማህበረሰብ የንቃተ ህሌና ጋር ቀጥታ የሚያያዝ ነው፡፡ የዓለም ህዝብ ከተፈጠረ ጀምሮ በርካታ ለውጦችን አስተናግዷል፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ ወቅቱና ጊዜው በሚጠይቀው ልክ ንቃተ ህሌናዊ እና ርዕዮት ዓለማዊ ማሻሻል አሳይቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ሚት በምንነቱ፣ በሚሰጠው ብያኔ፣ በንድፍ ሀሳባዊ ጥናት ወዘተ. እንደ ጊዜውና ወቅቱ እንደሚጠይቀው ሲሻሻልና ሲለወጥ ይስተዋላል፡፡ በዚህም የተነሳ የጥንት የጠዋቱን ‹‹ነባር›› ከዘመናዊ ዓለም ጀምሮ የሚባሉትን ደግሞ ‹‹አዲስ›› በማለት ከፍሎ ማየት እንሚቻል ቴዎድሮስ (2001) ይገልጻል፡፡

ቴዎድሮስ (2001፣256) ሚት (Myth): እጅጉን ተለጣጭ (flexible) ተረክ ነው፡፡ ሚት ተለጣጭ ነው ስንል አንድም፣ ባህሪያቱ እንደጊዜውና እንደ ሁኔታው ይለዋወጣሉ፤የባህሪያቱ ለውጥ ደግሞ የተረኩን ተግባር ወይም ሙያ ይቀይራል፤ ይሄንም ተከትሎ የጥበቡን ምንነት የምንገልጽበት ብያኔ፣ የምንመረምርበት ንድፈ ሀሳብ በአንድ አይረጋም ማለታችን ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚቶችን ‹‹ነባር›› እና ‹‹አዲስ›› ወይም ‹‹ብሉይ›› እና ‹‹ሀዲስ››በሚሉ በሁለት ልማዶች ወግነን መመልከት እንችላለን በማለት ሲበይነው፡፡

ሚት ለሰው ልጅ የህሌና እረፍት አግኝቶ ለመኖር ወሳኝ ነገሮች ናቸው፡፡ ሰው በተፈጥሮው ጠያቂ፣ ነገሮችን ለማወቅና ምላሽ ለመስጠት ካለው ልዩ ፍላጎት የተነሳ ካለሚት ማሰብ ይከብዳል፡፡ ሚቶቹ ሁለ ነገሩ ናቸው፡፡

ሰሎሞን (2007፣98-99) ሚት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እውነተኛ ድርጊት እንደሆነ የሚታመን ታሪክ የሚገለጽበት የትረካ አይነት ነው፡፡ በሚት ውስጥ የሚነገሩ ድርጊቶች አንድ ማህበረሰብ በራሱ ፍልስፍና፣ ባህል፣ ሀይማኖት፣ ዓለማዊ ዕይታ ወዘተ. ተነስቶ እውነተኛ ታሪክ እንደሆኑ የተቀበላቸው ናቸው፡፡እነዚህ ድርጊቶች ለሀይማኖቱ፣ ለማንነቱ፣ ለባህሉና ለማህበራዊ የህይወት መዋቅሩ ዋና መሰረቶች ናቸው፡፡

አንዳንዶቹ ሚትን ከሀተታ ተፈጥሮ ጋር በማቆራኘት ብያኔ ሲሰጡት ይስተዋላሉ፡፡ ለዚህም ዘሪሁን (2005፣33) ሀተታ ተፈጥሮ ሰዎች የሰውነታቸውን ሚስጢር፣ በአለም ለመኖር የቻሉበትን ምክንያት ለማወቅ ይሻሉ፡፡ አካባቢያቸውንም በመመልከት የተፈጥሮ ልዩ ልዩ ገጽታዎችንና መልክአ ምድራዊ ቅርጾችን አፈጣጠር ለመረዳት ይጓጓሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ እንደየባህላቸውና እንደየእምነታቸው ለተፈጥሮ ትርጓሜ ይሰጣሉ፡፡ ለመኖር ሲሉ ከተፈጥሮ ጋር ትግል ሲያደርጉ ብዙ አስደንጋጭ፣ አስፈሪና ፈታኝ ሁኔታዎች ይገጥሟቸዋል፡፡ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ለምን እንደመጡም ያሳስቧቸዋል፡፡ ለነዚህ እንደ እምነታቸውና አመለካከታቸው መልስ ይሰጣሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ የምንገነዘበው ሚት በተለያዩ ባለሙያዎች የሚሰጠው ብያኔ እንደባለሙያው ዝንባሌ የተለያየ ሊሆን እንደሚችልና በዋናነት ግን በሰው ልጅ ውስጥ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው፣ በዝርው ትረካ የሚቀርብ፣ ለህይወት እንቆቅልሾች መልስ የሚሰጥ (በአብዛኛው መንፈሳዊ)፣ እውነት ነው ተብሎ የታመነበት መሆኑን ነው፡፡

### 3.1.5 ተረክን የማጥናት አስፈላጊነት እና የአጠናን ስልት

ከላይ እንደተመለከትነው ተረክ ማለት የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን እና ግለሰብ አመለካከት፣ ባህል፣ እምነት፣ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ማንነት ማወቅ የሚያስችል፤ ሁነቶችንና ድርጊቶችን የሚያሳይ፤ ዓረፍተ ነገሮች በስረዓት ተዋቅረው የሚያደረጁት፣ ታሪክ ያለው፣ ታሪኩን የሚያስኬድ ገጸ ባህሪያት ያለበት የሀሳብ ማስተላለፊያ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም ተረክን ማጥናት ደግሞ የተራኪውን ማኅበረሰብ ማንነት፣ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ወዘተ. ለመረዳት ያስችላል፡፡ ይህንንም በማስመልከት Sims (2005: 168)

“ተረኮች የተራኪውን ማኅበረሰብ አመለካከት የያዙና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ተረኮች በማጤን የማኅበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል፣ ርዕዮት ዓለማዊ ፍልስፍና፣ ወዘተ. ማወቅ ይቻላል” ይላል፡፡ ተረክ ሲጠና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የተለያዩ ነጥቦች እንዳሉ ተመራማሪዎች ሀሳቦችን ሰንዝረዋል፡፡

“በተረኮች ላይ ትንታኔ ለመስጠት ስንነሳ ከግንዛቤ ማስገባት ያለብን የተረኩን ሚና ማወቅ፣ ትልሙን መለየት፣ የተረኩን የአደረጃጀት ቅደም ተከተል መለየትና ድምጸቱን መገንዘብ፣ የትረካውን የትኩረት አቅጣጫ መለየት እና የተረኩን፣ የተራኪውን እና የአድማጩን ተዛምድ መለየት ናቸው” በማለት (Finnegan, 1992: 37-38) ይገልጻሉ፡፡

እንደ Degh (1972: 54) ገለጻ ደግሞ ተረክን ለማጥናት የሚነሳ ሰው ትኩረት ሰጥቶ ሊመልሳቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነሱም የተረኩ መልዕክት ምንድነው? ለተረኩ መፈጠር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምንድን ነው? እና ተረኮቹን ተራኪዎቻቸው እና አድማጮቻቸው እንዴት ይመለከቷቸዋል? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው::

ከእነዚህ በተጨማሪ Oring (1986: 135-142) ተረክን ለማጥናትና ለመፈከር የሚነሳ ሰው አራት አውዶችን መረዳት እንዳለበት ይጠቁማል፡፡ እነሱም ባህላዊ አውድ፣ ማህበራዊ አውድ፣ ግላዊ አውድ እና ንጽጽራዊ አውድ ናቸው፡፡ እነዚህን አውዶች መረዳትና ከግንዛቤ ማስገባት ተረኮቹ ለማህበረሰቡ ምን እንደሆኑና ሚናቸውን ለማወቅ ያስችላል ፡፡

ስለዚህ ተረክ ሲጠና ተረኩን ብቻ ወስዶ ትንታኔ ከመስጠት ይልቅ የተረኩ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ ለተረኩ ያለውን አመለካከት፣ ባህል፣ የመከወኛ ቦታና የመከወኛ ጊዜ ማወቅ በተረኩ ውስጥ ያሉትን ትዕምርቶችና ሀሳቦች ለመረዳት ያስችላል፡፡

### 3.2 የተዛማጅ ጥናት ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ተዳስሰዋል፡፡ምንም እንኳን በስነጽሁፍና ፎክሎር በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ እንዲሁም በሶስተኛ ዲግሪ በዚህ ቦታ /መርጡለ ማሪያም ገዳም/ የተሰራ ጥናት ባይኖርም በቀን 16/05/2011 ዓ.ም/ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል በተጻፈልኝ የትብብር ደብዳቤ አማካኝነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጽሃፍት ውስጥ ባደረኩት ዳሰሳ ከኔ የጥናት ርዕስ ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የሆኑ ስራዎች

(ጥናቶች) ተገኝተዋል፡፡ ጥናቶችም ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት እንዲሁም በጥናቶቹ ውስጥ የታዩኝን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለማሳየት ሞክሪያለሁ፡፡ የጥናቶችም ዓይነትና ብዛት በታሪክ ትምህርት በመጀመሪያ ዲግሪ አንድ፣ በስነጽሁፍና ፎክሎር በሁለተኛ ዲግሪ ሰባት በአጠቃላይ ስምንት ጥናቶች እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

የመጀመሪያው ጥናት የሀብታሙ መንግስቴ (1998) “A History of Monastory of Mertulamariam (c1500-1974)”በሚል በእኔ ርዕስ የጥናት ቦታ ላይ የተሰራ ጥናት ተገኝቷል፡፡ ይህ ጥናት ቤተክርስቲያኗ ከመመስረቷ በፊት የነበረው አካባቢያዊ ሁኔታ፣ ቤተክርስቲያኗ የተመሰረተችበትን ዘመን እና ወደ ገዳምነት ያደገችበትን ሂደት በጥናቱ ላይ በሰፊው ተብራርቶ ይገኛል፡፡ የጥናት ቦታችን አንድ በመሆኑ የሚያመሳስለው ሲሆን ነገር ግን ሀብታሙ ስለቤተክርስቲያኗ ታሪካዊ አመሰራረት ከማንሳቱ በተጨማሪ በግራኝ አህመድ የደረሰባትን ውድመት በሰፊው አስቀምጧል እንጅ ከቤተክርስቲያኗ ታሪክ ጋር ተያይዞ ስለሚነገሩ ተረኮች ያለው ነገር የለም፡፡ በዚህ ከኔ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

ሀብታሙ ገዳሚ ከመመስረቷ በፊት የነበረውን አካባቢያዊ ሁኔታ፣ ቤተ ክርስቲያኗ የተመሰረተችበትን ዘመን እና ወደ ገዳምነት ያደገችበትን ሂደት በጥናቱ ላይ በሰፊው መገለጹ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው፡፡ ነገር ግን የጥናቱ ድክመት ገዳሚ በግራኝ አህመድ ውድመት እንደደረሰባት የተገለጸው ነገር ስህተት መሆኑ ነው፡፡ በአጥኝው ጥናት ውስጥ ስለ ግራኝ አህመድ የክብር ልብስ ተረክ በሰበሰብኩበት ወቅት ማረጋገጥ እንደቻለው ግራኝ አህመድ ከገዳሚ ቀርቶ የጎጃም ምድርን እንዳልረገጠ በተረክ ክፍሉ ላይ የተገኘው መረጃ ዋቢ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በፍፁም ኩራባቸው (2006)‹‹የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት››በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በዝዋይ ደሰያት አድባራት መመስረት የተገኙ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን ምሳሌ፣ ዘይቤና ትዕምርታዊ አንድምታ መርምሮ ማብራራት፣ እንዲሁም ተምሳሌታዊ ፍቻቸውን በመፈከር የተረኮቹንና ቁሳዊ ባህሎቹን ፋይዳ ማብራራት የሚል ነው፡፡ ፍፁም ዓላመውን ከዳር ለማድረስ ምልከታ፣ ቃለ መጠየቅና የቡድን ውይይት የመረጃ መስብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ መረጃውን በማሟላት የጥናቱን ዓላማ ከግብ አድርሷል፡፡ በመጨረሻም መረጃዎችን በገላጭ የምርምር ስልት ተንትኖ አቅርቧል፡፡

የፍፁም ጥናት በገዳም ላይ ተመስርቶ ተረኮቹን ማጥናቱም ሆነ የመተንተኛ ስልቱ ከአጥኚው ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን የሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አለመጠቀሙ፣ ቁሳዊ ባህልን ማጥናቱ፣ የአጥኚው ጥናት ደግሞ የተመሰረተበት ገዳም የተለየ መሆኑ እና ተረክ ላይ ብቻ ማተኮሩ ከእርሱ ጥናት ይለያል፡፡

ፍጹም የተግባራዊ ንድፍ ሀሳብን፣ የተረክን ንድፍ ሀሳብ እንዲሁም የቁሳዊ ባህልን ፅንስ ሀሳብ በአግባቡና በስረዓት በመጠቀሙ የጥናቱም ዓላማ አሳክቷል፡፡ ቃላዊ ተረኮችን ተንትኗል፡፡ ቁሳዊ ባህሎችን መርምሯል፡፡ ያላቸውን ተምሳሌትም ማሳየት ችሏል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱን በተሳካ ሁኔታ በጥልቀት መርምሮ በስፋትና በምልዓት መተንተኑ ጠንካራ ጎኑ ነው፡፡

መሪማ መሐመድ (2009) ‹‹የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት›› በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ መሪማ የጥናቷ ዋና አላማ እንደሚጠቁመው ተረኮቹ እና ቁሳዊ ባህሎቹ በገዳማውያኑና በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ያላቸው ፋይዳ በመመርመር እና ተምሳሌታቸውን ማሳዬት በሚለው መሰረት መረጃዎቹን በቃለ መጠየቅና በምልከታ በመሰብሰብ እንዲሁም ሌሎች አጋዥ መሳሪያዎችን ተጠቅማ የተገኙ ቃላዊ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን በተረክ ንድፍ ሀሳብ፣ በቁሳዊ ባህል ጽንስ ሀሳብ ሞዴሎችንና ተረክንም ሆነ ቁሳዊ ባህልን ለመፈከር በሚያስችለው በተግባራዊ ንድፍ ሀሳብ (functional theory) በመተንተን በገለጻና ትንተና ስልት አብራርታ ገልጻለች፡፡ ይህ ጥናት ከአጥኚው የጥናት ርዕስ ጋር የሚመሳሰለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠየቅና ምልከታ መጠቀሟ፣ የገዳማውያንን ህይወት መዳሰሷና ተረክን ማጥናቷ ነው፡፡ ልዩነቱ የአጥኚው ጥናት ቡድን ተኮር ውይይት (focus grouping discustion) እና የጽሁፍ ሰነድ ፍተሻን ጨምሮ መጠቀሙ፣ የመረጃ መተንተኛ ንድፍ ሀሳብ፣ የጥናቱ የሀሳብ ቅደም ተከተል (format)ና ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ /ገዳም/ ልዩነታችን ነው፡፡

መሪማ የጥናቷን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀመቻው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ መሳሪያዎችና የመረጃ መተንተኛዋ አግባብነት ጥሩ ነው፡፡ በጥናቷ የተጠቀመቻው ንድፍ ሀሳባዊ ዳራ (የገዳም ምንነት፣ የገዳም ህይወት አጀማመር በኢትዮጵያ፣ የገዳም ህይወት አኗኗር ስረዓት /ደንብ/) እና ሌሎች ተረካዊ ንድፍ ሀሳቦች በጥናቱ በበቂ ሁኔታ መዘርዘራቸው በጎ ጎን ነው፡፡

መሪማ የተጠቀመቻቸው የተዛማጅ ጥናቶች ከቅድስት ስላሴ የስነ መለኮት ኮሌጅ፣ ከታሪክ ትምህርት ክፍል በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ የተሰሩ እንዲሁም በሁለተኛ ዲግሪ በኢትዮጵያ የስነጽሁፍና ፎክሎር ናቸው፡፡ የተዛማጅ ጥናቱ ቁጥር ብዙ መሆንና ጥናቷን ከተለያየ ‹‹ዲሲፕሊን›› አንጻር ለማየት መሞከሯ የጥናቱ ጥሩ ጎን ነው፡፡ ይሁን እንጅ መሪማ በዚህ ጥናት ሰፊ የሆነ ትንታኔ የሰጠችው በሁለተኛ ዲግሪ የስነጽሁፍና ፎክሎር ጥናቶች ላይ ብቻ ነው፡፡

የቁሳዊ ባህሎችን በተነተነችበት ክፍል በገዳሚ /በእንጦጦ ሐመረ ኖህ ኪዳነ ምህረት ገዳም/ በረካታ የሆኑ ቁሳዊ ባህሎች እንደሚገኙ ገልጻለች፡፡ ነገር ግን ትንታኔ የተሰጠባቸው ቁሶች ጥቂት ናቸው፡፡ ለነዚህ መመረጥና ለሌሎች አለመመረጥ /አለመተንተን/ የተሰጠ ምክንያት የለም፡፡ እነዚህ የጥናቱ ደካማ ጎኖች ናቸው፡፡

በአቤል አሰፋ (2008 ዓ.ም) ‹‹የጣራ አቡነ ኤዎስጣቴዎሰ ገዳም፣ ዋሻ እንዲሪያስ እና ዋሻ ተክለሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናትና በዙሪያው የሚነገሩ ተረኮች›› የተሰራ ሲሆን፣ አጥኝው በነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችን አገልግሎት ለማሳየት ጥረት አድርጓል፡፡ መረጃዎችንም ተያያዥነት ካላቸው የጽሁፍ ሰነዶችና በቃለ መጠየቅ ሰብስቧል፡፡ የተጠቀመው የምርምር ዘዴም ገላጭ ነው፡፡

አቤል የጥናቱ ትኩረት ባደረገባቸው ቤተ ክርስቲያናትና ገዳም የሚነገሩ ተረኮችን ብቻ ማጥናቱ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው የጽሁፍ የሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠየቅ መሆናቸው እንዲሁም አጥኝው ለመረጃ ትንተና ገላጭ የምርምር ዘዴን መጠቀሙ ከአጥኝው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን ነገር ግን በዚህ ጥናት ውስጥ አንድ ገዳምና ሁለት አብያተ ክርስቲያናት በጥናቱ ተተኳሪነት መካተታቸው ዋና ልዩነታቸው ነው፡፡

አቤል የሚያነሳቸውን የማብራሪያ ሀሳቦች በምሁራን ሀሳብ ለማስደገፍ ያደረገው ሙከራ በጥሩ ጎን የሚታይ ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተከተለው የንድፍ ሀሳብ አካሄድ ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ክፍተቶች አሉበት፡፡ የአቤል ጥናት በአብያተ ክርስቲያናትና በገዳም ተረኮች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

ነገር ግን በተዛማጅ ጥናት ቅኝት ላይ የተዳሰሱ ጥናቶች ከሁለቱ በአማርኛ ስነጽሁፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች በስተቀር ሌሎቹ ስለገዳማት ታሪካዊ አመሰራረት የሚያትቱ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ ስለገዳማዊ ህይወት፣ ስለሚያከናውኗቸው

ፎክሎራዊ ገጽታዎች፣ የሚያወሩ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ሁለት ጥናቶች ደግሞ በስነቃልና አፈ ታሪክ ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህን ጥናቶች በተዛማጅነት እዚህ አምጥቶ መጠቀሙ ለምን እንዳስፈለገ ግልጽ አይደለም፡፡ ሌሎች ከነዚህ የተሻሉ ተዛማጅ ጥናቶችን ማቅረብ ይቻል ስለነበር፡፡ እንደ አጠቃላይ የሁሉንም ተዛማጅ ጥናቶች ያለባቸውን ክፍተት ወይም ጠንካራ ጎን፣ ከእሱ ጥናት ጋር የሚዛመዱበትንም ሆነ የሚለያዩበትን አመክኖ አልገለጸም፡፡

ሌላው በተዛማጅ ጥናቱ ውስጥ ስለ ሉሌ መላኩ መጽሃፍ አንስቶ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ይህን ጉዳይ ከዚህ ማስገባቱና ያን ያህል ሰፊ ሀተታ ማስቀመጥ ትክክል አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ድክመት ሆኖ ታይቶኛል፡፡

ቴዎድሮስ ይበልጣል (2005) ‹‹የደብረወርቅ ማሪያም ገዳም አመሰራረትና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና››በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ ከደብረ ወርቅ ገዳም ማሪያም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች በገዳማውያኑና በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡

ቴዎድሮስ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃውን በቃለ መጠየቅና በምልከታ ዘዴ ሰብስቦ በገላጭ የምርምር ዘዴ ተንትኗል፡፡ በንድፍ ሀሳባዊ ዳራ አጥኚው ስለተረክ ምንነት፣ ዓይነቶችና ስለተግባራዊ ንድፍ ሀሳብ በጥናቱ በቂ ማብራሪያ አቅረቧል፡፡

አጥኚው የገዳሚን አመሰራረት ስያሜ፣ ጥንታዊነት፣ ቅድስና፣ ተዓምረ ሰሪነትና የቅዱሳን መፍለቂያ መሆኗን የሚያሳዩ ተረኮችን ሰብስቧል፡፡ በዚህም ተረኮቹ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት እንዳሏቸው ለማሳየት ሞክሯል፡፡ የሰበሰባቸውን ተረኮችም እንደየሚያነሱት ጉዳይ በይዘት ለመመደብ እና ለመተንተን ችሏል፡፡

ቴዎድሮስ በዚህ ጥናቱ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበረሰቡ ወይም የእምነቱ ተከታይ እምነቱን ፀንቶ እንዲቆይ የማስተማር፣ የመግታትና የመቆጣጠር ተግባር እንዲሁም ለገዳሚ ክብር ይሰጥ ዘንድ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

የቴዎድሮስ ጥናት ገዳም ላይ መመስረቱና ተረክን ብቻ ማንሳቱ ከአጥኚው ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት የተመሰረተበት ገዳምና የእርሱ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለያ ነው፡፡

በመጨረሻም ቴዎድሮስ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመረጃ መሰብሰቢያው አግባብነትና የመረጃ አተናተኑን በገላጭ የምርምር ዘዴ ተጠቅሞ መረጃ የተነተነበት ሂደት ጥሩ የሚባል ነው፡፡ አጥኚው በንድፍ ሀሳባዊ ዳራው ስለተረክ ምንነት፣ ዓይነቶችና ስለተግባራዊ ንድፍ ሀሳብ ለጥናቱ በበቂ ሁኔታ አብራርቶ ማቅረቡ ጠንካራ ጎኑ ነው፡፡ ነገር ግን ስለገላጭ ዘዴ ምንነትና ለምን ሊመርጠው እንደቻለ ማብራሪያ አለመስጠቱ የጥናቱ ድክመት ነው፡፡

ወንድወሰን ሞላ (2007) ‹‹በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት››በሚል የተጠና ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት በገዳሙ የሚነገሩ ተረኮችን በመመርመርና በመተንተን ለገዳማውያኑ ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ አጥኚው የተሟላና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ያስችለው ዘንድ የቤተ መጽሀፍትን መረጃዎችን፣ በቃለ መጠየቅና በምልከታ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በተግባራዊ ንድፍ ሀሳብና በተረክ ንድፍ ሀሳብ ላይ በመመስረት ለመተንተን ሞክሯል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ተረኮች ተሰብስበው መመርመርና መተንተናቸው፣ የተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጽሁፍ መረጃዎች፣ ቃለመጠየቅና ምልከታን መጠቀሙ የሚያመሳስለው ሲሆን ነገር ግን የተሰበሰቡ መረጃዎችን በተግባራዊ ንድፍ ሀሳብ ታግዞ መረጃዎችን መተንተኑ፣ መረጃ ከማግኘት ዘዴዎች ውስጥም ቡድን ተኮር ውይይትን አለመጠቀሙ ከአጥኚው ጥናት የሚለየው ነው፡፡

የወንድወሰን ጥናት በጥናቱ የሰበሰባቸውን መረጃዎች አስተማማኝነታቸውን የተሻለ እንዲሆን መረጃዎችን እንደአመላቸው ከጽሁፋዊ ሰነዶች የሚገኙትን ከጽሁፋዊ ሰነዶች፣ ጥናቱ ሰለሚካሄድበት አካባቢና በገዳሙ ውስጥ ስለሚተረኩ ተረኮች ደግሞ በቃለ መጠየቅና በምልከታ መሰብሰቡ፣ የሚያነሳቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በምሁራን ሀሳብ እያስረገጠ ማቅረቡ፣ የተጠቀማቸው ንድፍ ሀሳቦች አግባብነትና ከበቂ ማብራሪያ ጋር መቅረባቸው፣ የተዛማጅ ጥናቶችን ከእሱ ጥናት ጋር ያላቸውን ዝምድና፣ ልዩነት፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ከበቂ ማብራሪያ ጋር ማቅረቡ፣ በጥናቱ መጨረሻ ላይ የተረክ፣

የምስል፣ የመረጃ አቀባዮች እና የተለያዩ ደብዳቤዎችን በአባሪነት ማስቀመጡ የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡

ሞገስ ጀንበሬ (2003) ‹‹ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና በገዳሙ ውስጥ አምልኳዊ ስርዓቶች›› በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዓላማም ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮችና በገዳሙ ውስጥ በሚፈጸሙ አምልኳዊ ስርዓቶች የገዳማውያኑ እምነት ምን እንደሚመስል መመርመርና ይህም እምነት ለገዳማውያኑ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡

ተረኮችን በዓይነት በዓይነታቸው ከለየ በኋላ እነዚህ ተረኮች ገዳማዊ ህይወትን የማጠናከርና የመትከል ተግባር እንዳላቸው ገልጿል፡፡ የአምልኳዊ ስርዓቶችም ለገዳማውያኑ መንፈሳዊ ድባብን ከማስረጽ በተጨማሪ ገዳማዊ ህይወትን የማጽናት ተግባር እንዳላቸው አስረድቷል፡፡

ይህ ጥናት ከአጥኚው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ምልከታና ቃለ መጠየቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት መጠቀሙ እንዲሁም በገዳም ላይ መመስረቱ እና ተረክን ማጥናቱ ነው፡፡ ነገር ግን አምልኳዊ ስርዓቶችን ማካተቱ፣ የመረጃ መተንተኛ ስልቱ፣ ቡድን ተኮር ውይይትና ሰነድ ፍተሻ አለመጠቀሙ የጥናቱ ተተኳሪ ቦታ /ገዳማቱ/የተለያየ መሆኑና የመረጃ መተንተኛ ስልቱ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡

ሞገስ የገዳማዊ ህይወት አጀማመርን ከጣና ሃይቅ ደስያት ገዳማት ጋር በተያያዘ ያቀረበው መረጃ፣ በጥናቱ የመጨረሻ ክፍል የአባሪ ፎቶዎችንና ለቃለ መጠየቁ የቀረቡ ጥያቄዎችን ጨምሮ በአባሪነት ማካተቱ የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡

ነገር ግን ጥናቱ ክፍተቶችም አሉበት፡፡ ስለተገለገለባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ስለምንነታቸውና ለጥናቱ ያላቸውን አስፈላጊነት የሰጠው ማብራሪያ የለም፡፡ የተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት ያደረገበት ሁኔታም የቃኛቸውን ጥናቶች ከዓላማቸው ጀምሮ ይዘታቸውን በአጭር በአጭሩ ያስቀምጣል እንጅ ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን፣ የጥናቶቹ ግብ ምን እንደሚመስል ያለው ነገር የለም፡፡

ምህረት ተስፋዬ (2003) ‹‹ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት›› በሚል ርዕስ የተሰራው ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ በገዳማውያኑ ዘንድ እምነትን በመትከልና በማጠናከር ረገድ ያላቸውን ሚና ማሳየት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የገዳማዊ ህይወት አጀማመር በሰፊው ተተንትኗል፡፡ ቁሳዊ ባህሎችንም ቢሆን እያንዳንዱን በፎቶ በማስደገፍ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ መስተጋብራዊ ንድፍ ሃሳብ በመጠቀም ጥናቱን ለማስኬድ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም የገዳማውያኑን አመጋገብ፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች ከነስረዓቱ ለማሳት ተችሏል፡፡

የምህረት ጥናት ከአጥኚው ጥናት የሚያመሳስለው ተረኮችን ማጥናቱ ነው፡፡ ነገር ግን የጥናቱ ቦታ /ገዳሙ/፣ ቁሳዊ ባህሎችን ማጥናቱና የተጠቀመው ንድፍ ሀሳብ ደግሞ ልዩነቱ ነው፡፡

የምህረት ጥናት የገዳምውያን ህይወት አጀማመር ለማሳየት በቂ ማብራሪያ መስጠቱ፤ ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን የሄደበት ስልት፣ እያንዳንዱን ቁስ በፎቶ አስደግፎ ማቅረቡ እና ሌሎች ዓላማውን ለማሳካት አገልግሎት ላይ የዋሉ መረጃዎች የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡

ነገር ግን አሁንም ጥናቱ ክፍተት አልታጣበትም፡፡ በመጀመሪያ ጥናቱ ዳራ የለውም፡፡ መግቢያ ከዚያ ቀጥታ አነሳሽ ምክንያት ላይ ይጀምራል፡፡ የምልከታንና የቃለ መጠየቅን ዘዴዎች የመረጠበትን ምክንያት አይገልጽም፤ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉም የሚለው ነገር የለም፡፡ በተዛማጅ ጥናቶች ውስጥ የተዳሰሱ ጥናቶች ከጥናቱ ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት፣ ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የተሰጠ ማብራሪያ የለም፡፡ አገልግሎት ላይ ስለዋለው ንድፍ ሃሳብ ምንነትም ሆነ አስፈላጊነት የተገለጸ ነገር አለመኖሩ የጥናቱ ደካማ ጎኖች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.የአጠናን ዘዴ

የጥናቱ ዓይነት ዓይነታዊ ሲሆን ጥናቱ በገዳሟ የሚነገሩ ተረኮችን ይዘት ተንትኖ መመርመር በመሆኑ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠየቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይት እንዲሁም ከጽሁፋዊ ሰነዶች ከሰበሰብኩ በኋላ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስና የጥናቴን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተረክን ንድፍ ሃሳብ መታገጊያ በማድረግ በገላጭ የምርምር ዘዴ መረጃዎችን ተንትኛለሁ፡፡

### 4.1 የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት የተካሄደው በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ በመርጡለ ማሪያም ከተማ በምትገኘው በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማርያም ገዳም በሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና ላይ ያተኮረ ነው፡፡

### 4.2 የቦታ ናሙና አመራረጥ

የተመረጠው ክልል አማራ ሲሆን ክልሉ የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የተገኘበት ክልል በመሆኑ በአመቺ ናሙና ስልት ተመርጧል፡፡ የተመረጠው ዞን ምስራቅ ጎጃም ሲሆን የተመረጠበት ምክንያት ያጥኚው ልምድ የተገኘበትና የጥናት ስራውንም ለመስራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በድጋሚ በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡ የተመረጠው ወረዳ እነብሴ ሳር ምድር ነው፤ የተመረጠበት ምክንያት የአጥኚው አነሳሽ ምክንያት በጥናቱ የሚፈለገው መረጃ የሚገኝበት ቦታ በመሆኑ አሁንም በአመቺ የናሙና ስልት ተመርጧል፡፡

### 4.3 የመረጃ ሰጪ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በጥናቱ ርዕስ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን ባህሪ ከግምት በማስገባት አጥኝው አስተማማኝ እና ትክክለኛ መረጃ ያገኝ ዘንድ የመረጃ አቀባዮች ምርጫ የወሳኝ ናሙና አይነት የሆኑትን ኢላማዊ (targetd sampling) እና ምቹታዊ (convenience sampling) የናሙና አመራረጥ ስልት ተግባራዊ አድርጓል፡፡

ምክንያቱም አጥኝው የመረጃ ሰጪ ናሙናዎችን የወሰደው በአካባቢው ተወልደው ያደጉ /ለብዙ ጊዜ የኖሩ/ መሆናቸውን አረጋግጦ፣ ስለሚጠናው ርዕስ በቂ እውቀት እንዳላቸው ፈትሾ፣ ቅን /የተዛባ መረጃ የማይሰጡ/ መሆናቸውን ተማምኖ፣ የሚያውቁትን ነገር በደንብ መግለጽ የሚችሉትን ግለሰቦች ካረጋገጠ በኋላ በአካላዊ፣ በቦታም ሆነ በሌላ ምክንያት ከዚህ በፊት ባያውቃቸውም የመረጃውን ደህንነት ከግምት በማስገባት ብቻ መረጃ አቀባዮችን የመረጠበት ሁኔታ በመኖሩ ኢላማዊ (targetd sampling) የናሙና አወሳሰድን ሊጠቀም ችሏል፡፡

ነገር ግን ሁሉንም ናሙናዎች በዚህ መልክ ብቻ አልሰበሰባቸውም ይልቁንስ በጓደኝነት፣ በጉርብትና ወይም በሌላ ምክንያት አጥኝው የሚቀራረባቸው ግለሰቦችን ከላይ የተጠቀሱ የመረጃውን ደህንነት የሚያስጠብቁ ጉዳዮችን ሳይዘነጋ ትክክለኛ መረጃ ይሰጡኛል ብሎ ያመነባቸውን ሰዎች ናሙና ያደረገበት ሁኔታም ስላለ ምቹታዊ ናሙና ሊጠቀም ችሏል፡፡

### 4.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡ ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች መጽሃፎች፣ መጽሄቶችና ሌሎች በራሪ ወረቀቶች እንደ አስፈላጊነታቸው ተመርጠው ተወስደዋል፡፡ ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ ምልከታ፣ ቃለ መጠየቅ እና የቡድን ተኮር ውይይት ተመርጠዋል፡፡

እነዚህ ዘዴዎች መረጃዎችን ከመስክ ለመሰብሰብ በዋናነት ተመራጭ ሲሆኑ፣ ዘዴዎችን እንደ አስፈላጊነታቸውና አመቺነታቸው እያፈራረቁ መጠቀም ለመረጃው ግብዓትና ጥራት አስተዋጽኦ እና ጠቀሜታ እንዳላቸው የመስኩ ምሁራን ገልጸዋል

(Goldstein፣1964፣77-104) ‹‹በአንድ አጋጣሚ ላይ ቢያንስ ሁለት ዓይነት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም መረጃዎች እንዳይረሱና እንዳይጠፉ ያደርጋል፡፡ የተለያየ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መጠቀም የተሟላ መረጃ እንድናገኝ ከማድረጉም በተጨማሪ የመረጃዎቹን ትክክለኛ መልዕክት ሳንረዳ እንዳንቀር ያደርጋል፡፡›› ይላሉ በመሆኑም ይህን ጥናት ምልዑ ለማድረግ በዚህ ጥናት እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እያደጋገፍኩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በመቀጠልም ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ፤ ካልዓይ የመረጃ ምንጭ እንዲሁም ሶስቱን ቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የካልዓይ የሰነድ ፍተሻን በአጭር በአጭሩ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**ሀ.ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ፡-** ይህ ማለት ናሙና ከሆነው ግለሰብ ወይም ቡድን ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት የምንፈልገውን መረጃ በቃለ መጠየቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይት ወዘተ መረጃ የምናገኝበት ነው፡፡ ከጥናቱ ርዕሰ ባለቤት ከሆነው ማህበረሰብ ቀጥታ የሚያገናኝና መረጃ አቀባይ ጋር ፊት ለፊት የሚያነጋግር፣ የሚያወያይ፣ የሚያስተያይ የመረጃ መገኛ በመሆኑ ተመራጭነቱም ሆነ የመረጃው ታማኝነት ከፍ ያለ ነው፡፡

**ለ.ካልዓይ የመረጃ ምንጭ፡-** ይሄ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ከመረጃ አቀባይ ግለሰብ ወይም ቡድን ጋር የሚደረግ የፊት ለፊት ግንኙነት ሳይሆን ስለሚጠናው ጉዳይ የተጻፉ መጽሃፎችን፣ መጽሄቶችን፣ ጋዜጣዎችን፣ በራሪ ወረቀቶችን ወይም መሰል የመረጃ ማግኛ ስልቶችን ተጠቅመን መረጃ የምናገኝበት ነው፡፡ የዚህ የመረጃ ምንጭ ደካማ ጎኑ ከጉዳዩ ባለቤት ጋር የቀጥታ ግንኙነት ሳናደርግ በተጻፉ ሰነዶች ላይ ብቻ በመመስረት የምንሰበስበው በመሆኑ ተመራጭነቱንና የመረጃው ጤነኝነት ዝቅ ማድረጉ ሲሆን፣ ነገር ግን ጉዳዩን ለማጥናት ያለው አማራጭ በዚህ ብቻ የተወሰነ ከሆነ በቀጥታ የማይገኙ መረጃዎችን በማስገኘትና ጥናት እንድንሰራ ማስቻሉ በጎ ጎኑ ነው፡፡

**1.ምልከታ፡-**ምልከታ በዓይናችን የተመለከትናቸውን ብቻ ሳይሆን በአፍንጫችን ያሸተትናቸውን፣ በዕዝነ አዕምሯችን የተመለከትናቸው፣ በምላሳችን የቀመስናቸውና በመዳፎቻችን የዳሰስናቸው ነገሮችን እንደሚያካትት (Goldstein, 1964፣79) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ከቁስ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች ሙሉ መረጃ ለማግኘትና ለማሳየት

ምልከታ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ በዚህ ጥናት ከምልከታ ዓይነቶች ውስጥም ተገቢና አስፈላጊ የሆነው ተሳትፏዊ ምልከታ ተተግብሯል፡፡

የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱም፣ በምልከታ እና በቃለ መጠየቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች በቪዲዮና ፎቶ ካሜራ እንዲሁም መቅረጸ ድምጽን በመሳሰሉ አጋዥ መሳሪያዎች መታገዝ አለባቸው (Goldstenin, 1964, 97-99)፡፡ እንዳሉት ጥናት ወደሚደረግበት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጎጃም ዞን እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ በመሄድ በመርጡለ ማሪያም ከተማ የምትገኘውን ርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም በመገኘት ወደ ገዳሚ በመመላለስ መረጃ ሰብስቢያለሁ፡፡ በገዳሚ ባደረኩት ቆይታ፣ ሱባኤ የተያዘባቸውን አምስት ቦታዎች፣ በዳግማዊ ሚኒልክ የተጻፈውን ደብዳቤ፣ በሙሴና ኢያሱ ከእፀ ህይወት ስር ያመጧቸው የሚባሉ ትክል ድንጋዮችን፣ በእቃ ቤቱ የሚገኘውን የግራኝ አህመድ የክብር ልብስ፣ ዲያቆን ነዋ በግኡ ፀሎት ያደርግበት የነበረው በኋላም በአፀደ ስጋ የተሰወረበትን ጥንታዊ የፅድ ዛፍ፣ መምህር ዘውዱን ያነጋገረችው ስዕለ ማሪያምን፣ በገዳሚ አጠገብ የሚገኘውን የጠበል ቦታ፣ ‹‹ግንድ አጥም ማሪያም›› በሚል ቅፅል ስም የሚጠራውን ፅድ፣ ታሪካዊ የሆኑ ሁለቱ የገበታ የብራና መጽሃፍትን፣ በቅጽር ገቢው ውስጥ የሚገኙ የጥንታዊው የአብረሃ ወ አጽበሐ ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ፍርስራሽ፣ በአንበሳ ውድም የተገነባውና አሁን በማገልገል ላይ የሚገኘውን የቅድስት ድንግል ማሪያም ቤተ ክርስቲያን፣ በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት እንደተሰራ የሚታወቀውን የስላሴ ቤተ ክርስቲያን እና ሌሎች ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎችንና ቁሶችን ለመመልከትና የፎቶ ማስረጃዎችን ለመያዝ ችያለሁ፡፡

በመቀጠልም ከገዳሚ አጠገብ ወደሚገኘው የጠበል ስፍራ በመሄድና ፈውስ ካገኙ ጠበልተኞች ጋር በአካል በመገናኘት፣ መረጃዎችን በቃለ መጠየቅ፣ በድምጽና በቪዲዮ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ጠበሉም ብዙ ህሙማን የሚጠመቁበት፣ የተለያዩ የፈውስ ተዓምራት የተፈፀመበት ቅዱስ የጠበል ስፍራ መሆኑን መረጃ አግኝቻለሁ፡፡ በዓይኔም ተመልክቻለሁ፡፡ ተጨማሪ መረጃዎችንም በፎቶ መልክ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

2.ቃለ መጠየቅ፡-የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀምኩት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠየቅ ነው (Goldstein, 1964, 77-78) ‹‹ይህ ዘዴ ለጥናት የሚረዱኝን መረጃዎች ስለሚጠናው ጉዳይ እውቀት ካላቸው ሰዎች በመጠየቅ መረጃዎችን የሚሰበስቡበት ዘዴ መሆኑን›› ይግልጻል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ቃለ መጠየቅ ተጠያቂዎቹ ከሚሰጡት ምላሽ በተጨማሪ ከሰውነት እንቅስቃሴያቸውም መረጃ ማስገኘት ያስችላል፡፡ ስለሆነም በምልከታ ያልተሟሉ መረጃዎችን በቃለ መጠየቅ አማካኝነት ለማሟላት ሲባል ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

ይህንንም ዘዴ በመጠቀም በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች በተመለከተ ከሀይማኖት አባቶች እና ከመምህራን ስለገዳሚ አመሰራረትና ተረኮች መረጃ ማግኘት ተችሏል፡፡

መረጃዎቹ በአጠቃላይ የተሰበሰቡት በገዳሚ ውስጥ እና በገዳሚ ዙሪያ ከሚኖሩ በዕድሜ ከገፉ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን ቃለ መጠየቅ በማድረግ ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮቹ አብዛኞቹ ከሰላሳ አምስት ዓመት በላይ በገዳሚ እና በአካባቢው የኖሩ የተለያዩ የስልጣን ደረጃዎች የነበሯቸውና ያሏቸው ናቸው፡፡ ከነዚህም አካላት መረጃ ለመሰብሰብ መደበኛና ኢ-መደበኛ ቃለ መጠየቅ ተጠቅሚያለሁ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መረጃ ሰጪዎቹ መረጃውን በነጻነት ስሜት እንዲሰጡኝ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

በዚህ መንገድ የተሰበሰቡ መረጃዎች ወደ ጽሁፍ ሲቀየሩ በተቻለ መጠን ከዋናው መሰረተ ሀሳብ እንዳያፈነግጡ በጥንቃቄ ለመጻፍ ተምክሯል፡፡ በቃለ መጠየቅ ወቅት መደበኛና ኢ-መደበኛ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንድ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር አብረው የማይሄዱ እና የተደጋገሙ ጉዳዮች ወደ ጽሁፍ ሳይቀየሩ ቀርተዋል፡፡

3.ቡድን ተኮር ውይይት፡- ቡድን ተኮር ውይይት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ ተመራጭ ዘዴ እንደሆነና የቡድን አባላቱም ቁጥር ከ7-12 ሊደርስ እንደሚችል (Mike and Cook፡ 2007) ይገልጻሉ፡፡ ሂደቱም በተመራማሪውና ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል በሚደረግ ምልልስ የሚከወን ነው፡፡ የቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የተመረጠበት ምክንያትም ያልተሟሉ መረጃዎችን ማሟላት ከማስቻሉም በተጨማሪ ያልተዳሰሱ ጉዳዮች እንዲታወሱ ይረዳል፡፡ የመረጃዎችን ሀቀኝነት ለማረጋገጥና አዲስ መረጃን ስለሚያስገኝ ነው፡፡

በምልከታና በቃለ መጠየቅ ያልተሟሉና የተዘነጉ መረጃዎችን ለማሟላት እና የተለያየ ሀሳብ የሚሰጥባቸውን ነገሮች ለይቶ ትክክለኛውን መረጃ ለማቅረብ ይቻል ዘንድ ሁለት የቡድን ተኮር ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ እነዚህም ውይይቶች በእያንዳንዱ ቡድን በአራት የሃይማኖት አባቶች የተደረጉ ናቸው፡፡

በቡድን ተኮር ውይይቱ፣ በግል ተካሆዶ በነበረው ቃለ መጠየቅ ልዩነት ታይቶባቸው የነበሩ ሀሳቦች በጥያቄነት ተነስተው አራቱም የቡድን አባላት እንዲወያዩ በማድረግ ወደ አንድ መግባቢያ ሀሳብ መጥተው ትክክለኛ ነው የሚባለውን የጋራ ሀሳብ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አጥኝው በገዳሚ በነበረው ቆይታ በመቅረጸ ድምጽ መረጃ ከመሰብሰብ በተጨማሪ አባቶችን ከስራና ከፀሎት ሰዓት ውጪ ስለገዳሚ የሚያውቁትን ተረኮች እንዲነግሩት በመጠየቅ እና ማስታዎሻ በመያዝ እንዲሁም አንዳንድ ከንዋያተ ቅድሳትና ልዩ ልዩ ቁሶች ጋር የሚነገሩ ተረኮችን በፎቶ ግራፍ በማንሳት መረጃ ለመሰብሰብ ምክሯል፡፡

ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ቡድን ተኮር ውይይት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ከቡድን ተኮር ውይይት በፊት በሁለት ዙር የሰበሰባቸው መረጃዎች ከማስታዎሻ፣ ከቪዲዮና ከፎቶግራፍ መረጃዎችን በመምረጥና በስረዓት በመሰደር አደራጅቷል፡፡ የቡድን ውይይቱ ያወዛገቡና በቃለ መጠየቅ ያልተመለሱ /እርግጠኝነታቸው የሚመሳከር/ ጥያቄዎች የቀረቡበት ሲሆን ከሶስት እስከ አራት የሚደርሱ  ሰዎች ያሳተፉ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡

4.የሰነድ ፍተሻ፡-ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀመው ሁሉንም መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠየቅ ወይም በቡድን ተኮር ውይይት ብቻ በመጠቀም የተሟላ ስራ መስራት አይቻልም ብሎ በማሰቡ ነው፡፡ ምክንያቱም ወደ ዚህ ጥናት በተግባር በገባበት ጊዜ ጽሁፋዊ ሰነዶች ብቻ በማገላበጥ የሚገኙ መረጃዎች ሊኖሩ መቻላቸውን በማረጋገጡ ሲሆን፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ከላይ በምልከታ፣ በቃለ መጠየቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰጡ መረጃዎችን ከጽሁፋዊ መረጃዎች ጋር /ያላቸውን/ በማመሳከር የተዛባ መረጃ እንዳይጽፍ ያግዛል ብሎ በማመኑ ነው፡፡ ስለሆነም ስለገዳሚ አመሰራረት እና ስለመሰረቷት አባቶች ውስን ቢሆኑም የታተመውን መጽሄት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ የተጻፉ መጽሀፎችን በሚገባ ፈትሸዋል፡፡

### 4.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

በመስክ ቆይታየ ወቅት እያንዳንዱን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የአንደኛውን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ክፍተት በሌላኛው በማሟላት የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት

አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደመረጃው ባህሪና ተገቢነት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ለመጠቀም ምክሯል፡፡ ስለሆነም በምልከታ፣ በቃለ መጠየቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይት እና ከሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡትን መረጃዎች የተተነተኑት በገላጭ የምርምር ዘዴ ስልት ሲሆን የተሰበሰቡትን ተረኮች ለመመርመር ይችል ዘንድ የተረክ ንድፍ ሀሳብን ተጠቅሟል፡፡

በመቀጠልም በቀዳማይም ሆነ በካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ይዘትን መሰረት አድርጎ በመልክ በመልክ በመመደብ ጥናቱን ከግብ በሚያደርስ መልኩ በማደራጀት ተንትኜ አቅርቧል፡፡

መረጃዎቹ በሚሰበሰቡበት ወቅትም ሆነ ከተሰበሰቡ በኋላ የእያንዳንዱን ተረክ ትርጉምም ሆነ ትዕምርት ከተጠኚው ማህበረሰብ እምነት፣ ባህል፣ አስተሳሰብና ፍልስፍና ጋር አገናኝቶ ለመተንተን ምክሯል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5.የመረጃ ትንተና

## 5.1 ከርዕሰ አድባራት ወገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም የተሰበሰቡ ተረኮች ትንተና

በምዕራፍ ሁለት በንድፍ ሀሳባ ክፍል ላይ ሰለተረክ አይነቶች  ሁሉን ሊያስማማ የሚችል ወጥ የሆነ ምደባ እስካሁን አለመገኘቱ ተገልጿ፡፡ ለአብነትም ተረክን በተመለከተ ዓለም አቀፋዊ የሆነ ክፍፍል እንደሌለና ከአካባቢ አካባቢ የተለያየ ክፍፍሎች እንደሚኖሩ (Bascom, 1965:5) የገለጸው ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ የዘርፉ ባለሙያዎች በሚከተሏቸው የመመደቢያ መስፈርት መለያየት ምክንያት በርካታ የሆኑ የተለያዩ የምደባ አይነቶች እንዳሉና የመመደቢያ መስፈርቶች ከሚባሉት መካከል ገጸባህሪያትን መሰረት ያደረገ፣ ይዘትን መሰረት ያደረገ፣ ታሪክን መሰረት ያደረገ፣ ከየትመጣነትን መሰረት ያደረገ፣ አውድን መሰረት ያደረገ እየተባለ ሰለሚመደብ  ለመለያየቱ እንደመንስኤ ይጠቀሳል፡፡

ምንም እንኳን ከላይ እንተባለው ምደባው ወጥ የሆነ ነገር ባይኖርም ነገር ግን ለሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ የተሻለ የሚመስለውን መርጦ መጠቀም ግድ ስለሆነ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከገዳሚ ጋር በተለያየ ምክንያት ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን በይዘት መስፈርት በመከፋፈል ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከዚች ገዳም የተሰበሰቡ ተረኮች ይሄ ሚት ነው፣ ይሄ ደግሞ አፈ ታሪክ ነው፣ ይሄኛው ደግሞ ተረት ነው ብሎ ቁርጥ ያለ ምደባ ለመስጠት ቢያስቸግርም ነገር ግን ከላይ ከተዘረዘሩት የመመደቢያ ስልቶች ውስጥ ይዘትን መሰረት ያደረገ ምደባ በማካሄድ በገለጻ የምርምር ዘዴ በመጠቀም ለመተንትን ተምክሯል፡፡

ተረኮቹን ለመተንተን ከላይ ተረክን የማጥናት አስፈላጊነትና የአጠናን ስልት በሚለው ክፍል ውስጥ እንደ ተረኩ ዓይነትና ባህሪ የFinneganን፣ የDegahንና የOringን አራት አውዶች እንደአስፈላጊነታቸው በመጠቀም ተረኮችን ለመተንተን አገልግለዋል፡፡ የሚጠናው ሃይማኖታዊ ተረክ እንደመሆኑ እንደ አስፈላጊነቱ የመጽሃፍ ቅዱስን ታሪኮች ለተረኮች ትንተና ማንጸሪያነትና ማስኬጃነት ተጠቅሜባቸዋለሁ፡፡ ለዚህ የመነሻ ሃሳቤ ደግሞ (Oring፣1986፣135-42) ተረክን ከንጽጽራዊ አውድ አንጻር ትንታኔ ለመስጠት


የመጽሃፍ ቅዱስን ታሪኮች ማንሳት አንዱ እንደሆነ የገለጹትን መታገጊያ በማድረግ ነው፡፡

### 5.1.1 የገዳሚን ጥንታዊነት የሚዘክሩ ተረኮች

ከዚህ በመቀጠል በገዳሚ ጥንታዊነት ላይ የሚያጠነጥኑ ተረኮችን እንመለከታለን፡፡

በአንድ ወቅት በእነማይ (ቢቸና) ወረዳ የሚገኘው ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በምስረታ ከመርጡለ ማሪያም ይቀድማል የሚል ውዝግብ በዳግማዊ ሚኒልክ ዘመነ መንግስት ተፈጥሮ እንደነበር አባቶች ይናገራሉ፡፡ ይህንን ምክንያት በማድረግ ከቁልፍ መረጃ አቀባየና ከጽሁፍ ማስረጃዎች ያገኘሁት መረጃ፡፡

> በነበረው ክርክር መርጡለ ማሪያምን ወክለው ሲከራከሩ የነበሩት ፊታውራሪ እንድሬ ዲማ ከመርጡለ ማሪያም ይቀድማል መባሉ እንኳንስ መብለጡ መስተካከሉስ አለን? የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በረከቱ ይድረሰንና ዲማ በትክል መርጡለ ማሪያምን እንኳን ሊቀድም መርጡለ ማሪያም ስትተከል የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አባት ዞሮንቶስ አልተወለደም፡፡ በማለት የገዳሚን ጥንታዊነት ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከዲማ ጊዮርጊስ የምትቀድም ስለመሆኑ በዳግማዊ ምኒልክ ቀደምትነቷ የተረጋገጠበት ፊርማቸው ያለበት ደብዳቤ በዕቃ ቤቱ ውስጥ ይገኛል፡፡
>
> (ቃለ መጠየቅ፣ አባ ኃይለ ማሪያም፣መጋቢት 20 2011፣ መርጡለ ማሪያም ገዳም)



**ምስል3፡-ርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጠለ ማሪያም ገዳም ከዲማ ጊዮርጊስ የምትቀድም**

**መሆኗን የሚያረጋግጥ በዳግማዊ ሚኒልክ የተጻፈ ደብዳቤ፡፡**

ቀደም ሲል በገዳሚ ታሪካዊ አመሰራረት እንደተጠቀሰው ቅድመ ልደተ ክርስቶስ 2800 ዓ.ዓ ገደማ የካም ወይም የኩሽ ልጆች በአካባቢው መኖር ጀምረው ሀገሯንም ሀገረ እግዚያብሄር ካሉበት ጀምሮ (ከህግ ልቦና) እስከ ዘመነ ሀዲስ ያለው ታሪክ ለጥንታዊነቷ ትልቁ ማሳያ ሲሆን ይህ ደግሞ ተጨማሪ ማሳያ ነው፡፡

በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ቅጽር ግቢ ውስጥ ከስላሴ ቤተ ክርስቲያን በስተ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ ሁለት ትክል ድንጋዮች ሲገኙ አንደኛው ከላዩ ላይ ከድንጋይ የተሰራ የመስቀል ቅርጽ ተደርጎበት ይገኛሉ፡፡ ስለነዚህ ትክል ድንጋዮች የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ሀሳብ ሲሰነዝሩ ይደመጣል፡፡ እሱም፡- ግራኝ አህመድ የወረወረው ድንጋይ ነው፤ ገላውዲዎስ ግራኝ አህመድን ካሸነፈ በኋላ ለድል አድራጊነቱ መታሰቢያ ያቆመው ነው፤ የጥንት ነገስታት ሲሞቱ ለክብራቸው መገለጫ የሚቆምላቸው

ሀውልት ነው፤ አብረሐ እና አጽበሃ ጥንታዊ ቤተ መቅደሱን ሲሰሩ ያቆሙት ነው፤ የጥንት ሰዎች የስረዓተ ዓምልኮ መፈጸሚያ የነበረ ነው በማለት ይነገርለታል፡፡ ነገር ግን (መጋቢት 21፣2011 ዓ.ም ከ አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ አባ ኃይለ ማሪያም፣ አባ ቃለ ጽድቅ እና ፋሲካው ደጀን (መ/ር) ጋር ባደረኩት የቡድን ተኮር ውይይት እውነት ነው ተብሎ ስለሚታመንበት ተረክ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

> ሙሴና ኢያሱ ኑሯቸው እግዚያብሄርን በማመስገን በንጽህና እና በቅድስና ስለነበር ከእግዚያብሄር ጋር ባላቸው ቀረቤታ አራቱ አፍላጋት[10] ከመነጩበት ከእጸ ህይወት ስር ጠጠሮችን ይዘው በሚንቀሳቀሱበት ቦታ የእግዚያብሄር ቃል ኪዳን ያለባቸውን የሐዲስ ኪዳን መነገሪያ ቦታዎች ላይ ሲደርሱ እነዚህ ጠጠሮች በሚለመልሙ ጊዜ ምልክት አድርገው ሀውልት እንዲያቆሟቸው እግዚያብሄር በገባላቸው ቃል ኪዳን መሰረት ከዚህ ቦታ ሲደርሱ ይዘውት የነበረው ጠጠር ለምልሞ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ3740 ዓ.ዓ በፊት ይህች ቦታ የሀዲስ ኪዳን መንገሪያና የቃል ኪዳን ቦታ መሆኗን በትንቢት በሙሴና በኢያሱ አማካኝነት የቆመ ባለ ስድስት ገጽ ድንጋዮች ናቸው፡፡ ብለዋል፡፡

እንደ አጠቃላይ ከላይ የተባሉ ተረኮችን ጠቅለል አድርገን ገዳሚ በትዕንቢት ቃል ኪዳን የተመሰረተች ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ከታሪካዊ አመሰራረቷ ስንነሳ ሙሴና ኢያሱ በአምላክ ትዕዛዝ በዚያ በጥንት ጊዜ ጠጠሮችን አስቀመጡ፣ የካም ወይም የኩሽ ነገዶች ቦታው መጥተው በመስፈር እና ለቦታዋም የመጀመሪያውን ስያሜ በመስጠት ደስ ብሏቸው መስዕዋት እየሰው አምልካቸውን እያመሰገኑ ኖሩ፤ ክርሰቶስ ተወለደ፤ ወደ ቦታዋም የክርስቶስ (ሀዲስ ኪዳን አብሳሪዎች) በትዕንቢቱ መሰረት አብረሃ ወ አጽበሐ እና አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን መጡ፤ እንደተባለው የኦሪቱን ምኩራብ (ቤተ ፀሎት ለታረክ መዘክር ትተው) ከሌላ ቦታ (ግንብ በወሬ) ላይ ለመስራት ሞከሩ ያች ቃል ኪዳን አለችና

---

[10]አራቱ አፍላጋት (ወንዞች) ግዮን (አባይ)፣ ኤፌሶን፣ ጤግሮስ እና ኤፍራጠስ ናቸው፡፡የግራኝ አህመድ ቀሚስ መርጡለ ማሪያም ገዳም ቢገኝም እሱ ግን ከዚያ ቦታ አልመጣም ሲሉ አባቶች አጫሠውተውኛል፡፡
ከላይ የተጠቀሱት ሀውልቶች እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ቆም እንደነበርና በ842 በዩዲት ጉዲት የአብረሃ ወ አጽበሐ ቤተ መቅደስን ካፈረሰች በኂላ ሰባብራ እንደጣለችውና ለብዙ ዘመን ወድቆ ከቆየ በኂላ በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በ1933 በግሪካውያን (ሙሴ ኤልያስና ዩሐንስ ሉኪስታስ) አሁን ባለበት ሁኔታ ሊተከል ችሏል፡፡*

ከተባለው ቦታ ሳይሆን ከትንቢቱ ቦታ የጥንቱ ቤተ መቅደስ በራዕይ ተሰራ ከዚያም ሌሎች ቤተ ክርስቲያናት ተሰሩ፡፡

በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ ለቦታው የሚሰጠው ክብርና ዝና ከፍ ያለ ነው፡፡ ወደ እውነተኛው ተረክ ስንመጣ ደግሞ ማህበረሰቡ የኔነው የሚለውን ሀይማኖታዊ ጉዳይ እንዲከበርለትና ትልቅ ቦታ እንዲሰጠው ይፈልጋል፡፡ ከክብር ማስገኛ መንገዶች ውስጥ አንዱ ረጅም ዕድሜ ነው፡፡ በመሆኑም ክርሰቶስ ከመወለዱ በፊት ከ3740 ዓመት በፊት ይህች ቦታ እንደዚህ እንደምትሆን ተነገረ መባሉ ከሌላው ደብርና ገዳም በተለየ ክብርና የዕድሜ ባለጸግነትን እንድትይዝ ተፈልጎ ሊሆን ይችላል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ምናልባትም ማህበረሰቡ ድንጋይ (አሞጽ 5፣11) ለድንበር መለያ፣(ኢያሱ 4፣20) ለመታሰቢያነት፣ (ሕዝ. 11፣19፡20) ወይም መሰረት ያለውን ቋሚ ነገር ሊያመለክት ይችላል፡፡ የሚለውን ሃይማኖታዊ ትርጓሜ በማሰብ ተረኩ ተብሎ ይሆናል፡፡

ሌላው ከዚሁ ጋር አብሮ የሚታየው የትክል ድንጋዮች ቁጥር ሁለት መሆን፣ በአንደኛው አናት ላይ መስቀል ሲኖረው በሁለተኛው ላይ አለመኖሩና ስድስት ገጽ መኖሩ ሲሆን፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ስንል የሚከተለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ተፈልጎ ይመስላል፡፡ ሁለት ቁጥር፣ ይህች ጥንታዊትና ታሪካዊት ገዳም የኦሪትንና የሀዲስ ኪዳኑን (ክርስቶስ ከመወለዱ በፊትና ከተወለደ በኋላ ያለውን) ዘመን አጣምራ የያዘች የእድሜ ባለፀጋ መሆኗን ለማመላከት የቆሙ ናቸው ልንል እንችላለን፡፡ መስቀል በአንዱ ላይ መኖርና በሌላው ላይ አለመኖሩ ደግሞ፣ በብሉይ ኪዳን መስቀል የመከራ ተምሳሌት ሲሆን በሀዲስ ኪዳን ደግሞ ‹‹መስቀል የማስታረቅ ቃል ነው፡፡ በሰዎች መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ አፍርሷልና፤ ኤፌ. 2፣ 14-16፡፡›› ተብሎ በመጽሃፍ ቅዱስ ተጽፏልና፡፡ ይህም በመሆኑ መስቀል ያለው የሀዲስ ኪዳኑን ዘመን ጠቋሚ ሲሆን የሌለው ደግሞ የብሉይን ዘመን ወካይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሌላው ድንጋዮቹ ስድስት ገጽ እንዴት ሊኖራቸው ቻለ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ላይ ምናልባትም እግዚያብሄር በሙሴ አማካኝነት በደብረ ሲና የሰጣቸውን የኪዳን ትዕዛዝ የሚባሉት አስርቱ ትዕዛዛት ጊዜ የነበረው በሀዲስ ኪዳን ጊዜ ወደ ስድስት ህግጋተ ወንጌል መጠቃለሉን የሚጠቁም ነው፡፡



ምስል4፡-በሙሴና ኢያሱ ከእፀ ህይወት ስር የመጡ ጠጠሮች፡፡

### 5.1.2 ለገዳሚ የተገባላት የቃል ኪዳን ተረኮች

ቃል ኪዳን በአንድ ነገር ላይ ልባዊ ሆነን ስንስማማ የመንፈጽመው ወይም የምንገባው የጉዳዩ ማጽኛ /መተማመኛ/ ነገር ነው፡፡ ይህ ተግባር በሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ጀማሪውና አስተማሪው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሆኑ ቅዱሳን አባቶች፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ መላእክትና እራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ወይም ሰዋዊ ላልሆኑ ነገሮች ቃል ኪዳን ሲገቡ ይስተዋላል (የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር፣1980፣93)፡፡

በዚህም ምክንያት በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም በቅዱሳን ነገስታት፣ በቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት፣ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያምና ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ለገዳሚ የገቡላትን የቃል ኪዳን ተረኮች እንመለከታለን

አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን  መርጡለ ማሪያም ገዳምን ባርከወና ቀድሰው በመርጡለ ማሪያም ገዳም ክልል ውስጥ እባብ ሰውን ነድፎ እንዳይጎዳና ረሃብ ቸነፈር እንዳይኖር አባታዊ ቃል እንዳሳደሩ ቀጥሎ ያለው ተረክ ይነግረናል፡፡

በመርጡለ ማሪያም ገዳም ክልል ውስጥ ዛሬውኑ ሰውን እባብ ቢነድፍ በገዳሚ ቃል ኪዳን ሰለሚያምን ወደ ህክምና አይሄድም፤ በዚህ በሰጡት አባታዊ ቃል መሰረት የጋማና የቀንድ ከብቶች እንዲሁም ሳር ነጭተው ቅጠል ቀንጥሰው የሚኖሩ በግና ፍየሎች ሁሉ በውጭ ሲያድሩ የለሊት አውሬ ጅብን ጨምሮ ሳይበላቸው በሜዳ አድረው ይገኛሉ፡፡ በረዶ፣ አንበጣ፣ ቸነፈር መቸም ቢሆን በገዳሚ ክልል ውስጥ ጉዳት አድርሶ አያውቅም፡፡ ያጣ የነጣ በደጇ ሰላም ደጅ እየጠና የሚኖር ፈላሲ /ከሌላ ቦታ የመጣ/ የገዳሚ ቃል ኪዳን ስለሚጠብቀው በረሃብ አይሞትም በረድኤተ እግዚያብሄር ጠግቦ ያድራልና፡፡

(ቃለ መጠየቅ፣ አባ ኃይለ ማሪያም፣ መጋቢት19፣ 2011 ዓ.ም፣መርጡለ ማሪያም ገዳም) በማለት ገልጸዋል፡፡

ቃል ኪዳን በማህበረሰባችን ዘንድ ከፍተኛ ቦታ አለው፤ ይህ የሆነበት ምክንያትም መሰረቱና ምንጩ ህይማኖት ስለሆነ ነው፡፡ የእግዚያብሄር ቃል ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ለአዳምና ሄዋን ነው፡፡ (ዘፍ. 2፣8-17 እና ሆሴዕ 6፣7) በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ይህንን ህይማኖታዊ ጉዳይ ስለሚረዳ የተገባውን ቃል ኪዳን ይቀበለዋል፤ ያምንበታል፡፡

በመቀጠል በጥር 21 ቀን 333 ዓ.ም የኪዳን ጽላቱ ወደ ቤተ መቅደሱ በገባበት ዕለት ቅድስት ድንግል ማሪያም በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ በመርጡለ ማሪያም ገዳም የተገባላት የቃል ኪዳን ተረክ እንዳለ የሚነገር በቃለ መጠየቅ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

እናቴ ሆይ በዓለ እረፍትሽን አስቦ ዝክርሽን የዘከረ፣ በአንች ስም ስሙን የሰየመ፣ ለተቸገረ የሰጠ፣ በዓለ እረፍትሽን ለማክበር ከሩቅም ከቅርብም ተሰብስቦ ከዚህ ቦታ መጥቶ ስጋየን የበላውን፣ ደሜን የጠጣውን፣ በስምሽ ተማጽኖና ባንች ታምኖ ጸበል የጠጣውን፣ በዚህ ዕለት ከደጅሽ ተገኝቶ የተማጸነውን ሁሉ ምሬልሻለሁ፡፡ እናቴ ሆይ የጎደለኝን ሙላልኝ ኑሮየን አስተካክልልኝ ብሎ በአንች ስም በሱባኤ የጠየቀኝን ሁሉ ልመናውን አሰምርለታለሁ፡፡ ይህም ቦታ ላንች የድንግልናሽ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በንጽህና በድንግልና የፀኑ ደናግል መነኮሳት ያገልግሉሽ ሲል ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ሰጥቷታል፡፡

(ቃለ መጠየቅ፣ መርጌታ ዲበኩሉ፣መጋቢት30 ፣2011 ዓ.ም፣ ከወረዳው ሰበካ ጉባኤ ቢሮ)

ሌላው ከዚሁ ጋር የሚመሳሰል የቃል ኪዳን ተረክ አለ፡፡ የሚከተለውንም ይመስላል፡፡

አባ ተጠምቀ መድህን የተባሉ መነኩሴ በዚህች ገዳም እያገለገሉ ይኖሩ ነበር፡፡ እኒህ መነኩሴ ከፍጽምነታቸው የተነሳ ከእግዚያብሄር ጋር ቃል በቃል እንደተነጋገሩና ስምህን የጠራ፣ ዝክርህን የዘከረ፣ በዓልህን ያከበረ፣ ገድልህን የጻፈ ያጻፈ ሁሉ ለመንግስተ ሰማያት የበቃ ይሆናል የሚል የክርስቶስን የማይታበል ቃል ኪዳን ተቀብለው ያረፉ አባት እንደሆኑ

(በቃለ መጠየቅ፣አባ ኃይለ ማሪያም፣ መጋቢት 29፣2011 ዓ.ም፣መርጡለ ማሪያም ገዳም) ነግረውኛል፡፡

የቃል ኪዳን ተረኮች ተፈጽመዋል ተብለው ከሚነገሩ ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ላሉ የገቢራተ ተዓምራት፣ የፈውስ /ድህነት/፣ የቦታ ልዕልና፣ የቦታዋን ክብር ወዘተ ተረኮች መገኛ ናቸው፡፡ በመሆኑም በነዚህና መሰል ምክንያቶች ሳይሆን አይቀርም ጥር 21 ቀን በሚከበረው የበዓለ ዕረፍቷ መታሰቢያ በሀገራችን ውስጥ ከሚገኙ ጥንታዊ አድባራትና ገዳማት በተለየ ከሀገራችን ከአራቱም አቅጣጫ ህዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን ለማክበርና በዚያን ዕለት የተገባላቸውን እመቤታችንና የአባቶችን ቃለ በረከት ለመካፈል የሚመጣው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን እነዚህ ተረኮች ማህበረሰቡን በእምነቱና በማህበራዊ ጉዳዩ ለማጽናት /ለመትከል/፣ ለመቆጣጠርና ለመግታት፣ ግብረ ገብነትን፣ ለጋስነትን ከማስተማር አንጻር የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም፡፡

### 5.1.3 የገዳሟን ቅድስና እና ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተረኮች ደግሞ የቦታዋን ክብርና ቅድስና በማጉላት ማህበረሰቡ ገዳሟን በማክበር እንዲንከባከብ፣ አካባቢውን እንዲወድ፣ እምነቱን አጥብቆ እንዲይዝና እንዲመካበት፣ በመንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ኑሮው ተስፈኛ እንዲሆን የሚያደርጉ ተረኮች ናቸው፡፡

መርጡለ ማሪያም ‹‹የግራኝ እመቤት›› የሚል ቅፅል ስም አላት፡፡ ምክንያቱም በ1519 ዓ.ም ግራኝ አህመድ ወደ ስልጣን በመምጣት የክርስትናን እምነት

በማዳከም የእስልመና እምነትን ለማስፋፋት በነበረው ህልም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን፣ ብዙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያናትን እና ህዝበ ክርስቲያንን ጨምሮ ሲያቃጥል፣ ሲገድልና ሲያስገድል እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሆኖም በወቅቱ የነበሩት ንጉስ አፄ ልብና ድንግል ሲሆኑ የግራኝን ጦርነት መቋቋም አቅቷቸው ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ገቡ፡፡ ልጃቸው ገላውዲዎስም በእግራቸው ተተክቶ ወደ መንበረ ስልጣናቸው መጡ፡፡ ይህን የክርስቲያን መቅሰፍት የሆነውን ግራኝ አህመድንም ለመፋለም፣ አንዳንዶቹ ራሱ ገላውዲዎስ ሲሉ ፣ ሌሎቹ ደግሞ እናቱ የልብነ ድንግል ሚስት ንግስተ ሰብለ ወንጌል ሲሉ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ሁለቱም ይላሉ፡፡ ነገር ግን እኔ ቡድን ተኮር ውይይት አወያይቸ ትክክለኛ ነው ተብሎ የሚታመነው አፄ ገላውዲዮስ ጥር 21 ቀን 1535 ዓ.ም በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም የዕረፍት በዓል መታሰቢያ ንግስ በዓል ዕለት ከቦታው ድረስ መጥቶ ‹‹ ተዋግቸ ግራኝ አህመድን[11] ድል ብነሳው (ባሸንፈው) የኔን የክብር ልብስ፣ የግራኝ አህመድን የወግ ዕቃ፣ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ እቃዎችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ገቢ አደርጋለሁ፡፡›› በማለት ብፅዓት ገብቶ (ተስሎ) እንደሄደና በየካቲት 27 ቀን 1535 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት ግራኝ በጥይት ተመትቶ እንደሞተ፣ ገላውዲዮስም አሸንፎ በብፅዓቱ መሰረት ገቢ እንዳደረገ እና አሁንም በዕቃ ቤቱ እንደሚገኝ (ቡድን ተኮር ውይይት፣ መጋቢት 19፣2011 ዓ.ም ከ አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ አባ ኃይለ ማሪያም፣ አባ ቃለ ጽድቅ እና ፋሲካው ደጀን /መ/ር/፣ ርዕሰ ርዑሳኑ ቤት) ገልጸውልኛል፡፡




ምስል5፡- በዕቃ ቤቱ የሚገኘው የግራኝ አህመድ የክብር ልብስ፡፡

[11]የግራኝ አህመድ የክብር ልብስ በገዳሟ የሚገኘው ከላይ በተባለው ተረክ አማካኝነት እንጅ መርጡለ ማሪያም እንዳልመጣ የጽሁፍና የአባቶች ቃል ምስክር ነው። አንዳንዶችስ እንደውም ጎጃምን አልረገጠም ይላሉ። ይህም ግራኝ አህመድ የወረወረው ድንጋይ ለሚለው ተረክ ከወሬ ያለፈ አለመሆኑን ተጨማሪ ማሳያ ነው።

እዚህ ጋ አንድ ትልቅ ጉዳይ አለ እሱም ስለት /ብፅዓት/ ነው፡፡ ስለት /ብፅዓትን/ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ መንፈሳዊ እና ዓለማዊ፡፡

ሀ/መንፈሳዊ ስእለት፡- የሚባለው የስእለት አይነት ማህበረሰባችን የዚህ ምድሩን ሳይሆን የሰማዩን ህይወት በማሰብ፣ ዓለማዊውን ሳይሆን መንፈሳዊውን በማሰብ የቢሆንልኝ‹ የቢሳካልኝ እሳቤ ሲሆን፣

ለ/ ዓለማዊ ስእለት፡- ደግሞ በተቃራኒው የሰማዩን ሳይሆን የቁሳዊውን ዓለም በተሳካ ሁኔታ በኢኮኖሚም ሆነ በሌሎች ዓለማዊ ሆነው ምድራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የቢሆንልኝ‹ የቢሳካልኝ እሳቤ ልንለው እንችላለን፡፡

ስለዚህ ይህ የስለት ተረክ የተባለበት ምክንያት ምናልባትም አማኙ ማህበረሰብ ለቃሉ ታማኝ እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር ይህ የጥናቱ ተተኳሪ ማህበረሰብ ከላይ የተባለውን የግራኝን ተረክ ከግምት በማስገባት ወይም ‹‹ሰው ለእግዚያብሄር ብሎ እራሱን ከተፈቀደ ነገር ለማራቅ እንደ ናዝራዊ ስዕለት ይሳል ይሆናል፡፡ ሆኖም ከሚሰጠው ሀላፊነት ለመሸሽ ስዕለት መሳል ኃጢያት ነው (ማር.7፣10-13)፡፡ ሰው ስዕለቱን ባይፈፅም ኃጢያት ነውና በችኮላ መሳል አይገባም (ዘዳ.23፣21-23፤ምሳ.20፣25፤መክ.5፣4-5)›› የሚለውን አምላካዊ ቃል ህዝቡን ለማስተማር በመፈለግ ነው ሊባል ይችላል፡፡

ወደ ቀጣዩ ተረክ ከመሄዴ በፊት እዚሁ ላይ ከአፄ ገላውዲዮስና ግራኝ አህመድ ጋር ተያይዞ የሚነገረውን የህልም ተረክ ልጥቀስ፡፡

> መላእክት የጌታን ፈቃድ ለሰዎች በሕልም ይናገራሉ፤ ማቴ. 1፣20፤2፣13፡19፡፡ እንደተባለው ‹‹ዓፄ ገላውዲዮስ መርጡለ ማሪያም መጥቶ ግራኝ አህመድን እንዲያሸንፍ ብጽዓት ከገባ በኋላ በህልሙ ነጭ ንብ ከመርጡለ ማሪያም ገዳም ሄዳ የግራኝን ዓይን ስትወጋው እንዳየ ከዚያም በአሸናፊነት መንፈስ ተምልቶ ወደ ጦር ሜዳ እንደሄደና በስኬት እንደተመለሰ (አባ ኃይለ ማሪያም፣ሚያዚያ 12፣2011 ዓ.ም)›› ነግረውኛል፡፡

ስለተረኩ በዝርዝር ለማውራት ይመቸኝ ዘንድ ስለ ‹‹ህልም›› ምንነት ልግለጽ፡፡ ህልም በእንቅልፍ ጊዜ የሚታይ ነገር ነው፡፡ ህልም በቀን ከታየን ወይም ከታሰበ ነገር ጋር፣ ከአድራጎትም የተነሳ ሊታለም ይችላል፡፡ በብዙ ሰዎች ዘንድ ብዙ ጊዜ ልዩ ትርጉም

ባይኖረውም አልፎ አልፎና በአንዳንድ ሰዎች ላይ ግን ጥልቅ መልዕክት ሊኖረው እንደሚችል (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣24) ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ከዚህ በላይ ያለው ተረክም ጥልቅ መልዕክት ካዘሉ ህልሞች የሚመደብ ይመስላል፡፡

ማህበረሰባችን ወደ ፊት ስለሚገጥመው ጥሩም ይሁን መጥፎ ነገር በእንቅልፍ ሰዓት በሚታየው ህልም የማወቅ የቆየ ፍልስፍና እንዳለው ይታወቃል፡፡ የህልም አፈታት ጥበብም እንዲሁ፡፡ በዚህ ተረክ ውስጥም የታየው ነገር ይኸው ነው፡፡ ዓፄ ገላውዴዎስ ከገዳሚ በመምጣት ብጽዓት ገባ ይልና ከዚያ በህልሙ ‹‹ነጭ ንብ›› የግራኝ አህመድን ዓይን ስትወጋ አየ ይላል፡፡ በሀገራችን ባህል ‹‹ነጭ ቀለም›› የደስታ፣ የስኬት፣ የጥሩ ነገር ተምሳሌት ነው፡፡ ለዚህም በአብዛኛው ማህበረሰባችን በተለያየ ሃይማኖታዊም ሆነ ዓለማዊ በዓላት የሚለብሱት ልብስ ቀለም ነጭ መሆኑ ምስክር ነው፡፡ ‹‹ንብ›› ደግሞ የታታሪነት፣ የቅድስና ተምሳሌት ነች፡፡ ለዚህም ለቅዳሴና ለተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚውለው ጧፍ የሚዘጋጀው ንብ ከምትሰራው የማር ሰፈፍ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ‹‹ነጭ ንብ›› ማለት ምንን ይወክላል? እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያምን ለመወከል ተፈልጎ የተባለ ይመስላል፡፡ በመሆኑም ለዓፄ ገላውዴዎስ ከግራኝ አህመድ ጋር ባደረገው ጦርነትና ለግራኝም መሞት ለዓፄ ገላውዴዮስም ድል የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም መንፈሳዊ ተራዳይነት ነበረው ለማለት የተነገረ ይመስላል፡፡ በዚህ አጋጣሚም ይህ ተረክ ለአማኙ ማህበረሰብ የለመኗትን ፈጥና የምታደርስ ተዓምረኛ ገዳም መሆኗን ለማሳወቅም የተባለ ነው ሊባል ይችላል፡፡

ቀጣዩ የገዳሚን ቅድስናና ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተረክ አባ ሰላማ ከሳቴ ብረሐን /ፍሬ ምናጦስ/ መርጡለ ማሪያም ገዳምና ህዝቡን ይወዱት እንደነበር የሚነገረው ነው፡፡ ሆኖም እኒህ መንፈሳዊ አባት ወደ ሌላ ቦታ ከመሄዳቸው በፊት ቦታዋን ባርከውና ቀድሰው ወደ ተፈቀደላቸው ቦታ እንደሄዱ ይነገራል፡፡ ለዚህም የሚከተለው ተረክ ዋቢ ነው፡፡

> አባ ሰላማ ምንም እንኳ ቦታዋ ተስማሚና ምቹ ብትሆንም ይህ ቦታ ለእሳቸው እንዳልተፈቀደ በአብሳሪው ቅዱስ ገብርኤል አማካኝነት ተነግሯቸው ወደ ትግራይ እንደሄዱ ይታውቃል፤ ሆኖም ከመሄዳቸው በፊት ህዝቡን ሰብስበው ‹‹ልጆቼ የእጃቹህ ስራ ይባረክ፣ ሴት ወንድ ልጆቻችሁ ህግ እግዚያብሄርን የሚያከብሩ፣ በኦርቶዶክስ ሐይማኖት የጸኑ፣ ለእናት አባታቸው ታዛዥም ይሁኑ፣ ከውጭ

የገዛችሁት፣ በጋጥ በበረት ያዋለዳችሁት ይርባላችሁ፡፡ የምህረት ዝናብም ይዝነብላችሁ፤ የመሬታችሁ ፍሬ ይብዛላችሁ፤ ፍቅርና ሰላም፣ ደስታና ሀሴት በሁላችሁም ላይ ይሁን፡፡ እኔ እናንተንና ቦታዋን በመውደዴ ምክንያት በዚህ መኖር ፈልጌ ነበር ሆኖም ወደ ትግራይ እንድሄድ የእግዚያብሄር መላክ ቅዱስ ገብርኤል ነግሮኛል፡፡›› በማለት ህዝቡን ከመከሩና ከዘከሩ በኋላ የመለያያ ቃለ እግዚያብሄርን እያስተማሩ እያለ መሸ፡፡ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃንም ፀሀይን በእግዚያብሄር ሀይል ቁሚ ብለው አቁመው ህዝቡን እያስተማሩ ሲያቆርቡ ፈቃደ እግዚያብሄርን ተከትሎ ለሚሄድ ሰው ሁሉ ይደረግለታልና ለኖህ በቀስተ ደመና፣ ለሙሴ በሐመልማልና በነበልባል መካከል ሆኖ እንዳናገራቸው ሁሉ ለአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃንም አራት ህብር መልክ ባላት ቀስተ ደመና መካከል ሆኖ ሰላማ፣ ሰላማ፣ ሰላማ ሆይ ህግጋቱን ስረዓቱን ማስተማሩን ቀጥል፤ ያንተ አካል እንደፀሀይ ያብራ፤ ፀሀይን ከስልጣንህ ማሰሪያ ፍታት፤ ወደ መግቢያዋም ትገባ ዘንድ ስደዳት በማለት እንደነገረው፣ ይህንንም ቃል ሰምተው ፀሀይን ፈቷት ፀሀይም ወደ መስኮቷ ገባች፡፡ የአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ሰውነታቸው እንደ ፀሀይ አበራ ብረሃኑም የተሰበሰቡትን ሰዎች ሁሉ ዓይን ያንጸባርቅ ነበር፡፡

(ቃለ መጠየቅ፣ አባ ኃይለ ማሪያም፣ መጋቢት 18፣2011ዓ.ም፣ መርጡለ ማሪያም ገዳም)

ይህ ተረክ የአካባቢ ማህበረሰብ ለቅዱሳን አባቶች ቃል፣ ቡራኬና ምርቃት ከፍተኛ ቦታ እንዲሰጥ ከማድረግ አንጻር ያለው ጠቀሜታ ቀላል አይደለም፡፡ ስለሆነም ገዳሟ የአባቶች ቃለ በረከት ያደረባት ቦታ ነች በማለት በአማኙ ማህበረሰብ ከፍተኛ ክብር እንዲሰጣት ያደርጋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ፀሀይ ልትጠልቅ መስኮቷን ስትፈልግ ነብየ እግዚያብሄር ኢያሱ ለእስራኤላውያን ዕርስት ሲያካፍል ሰዓት ቢመሽበት ፀሃይን አቁሞ ያካፈለበትን መጽሀፍ ቅዱሳዊ ሁተታ በማሰብ ይህች ገዳም ምን ያህል የተቀደሰች እና የተከበረች እንደሆነች ለማሳየት ተፈልጎ ይሆናል፡፡

ሌላው የቦታውን ክብር ከፍ ከፍ ከሚያደርጉ ተረኮች ውስጥ የሀዲስ ኪዳኑን ቤተ መቅደስ ለመስራት ፈቃደ እግዚያብሄር ለመጠየቅ ሱባኤ ገብተው ሁሉም አንድ አይነት ራዕይ በማየታቸው የፈጣሪን ስራ እያደነቁ ሳለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ቃል በቃል አነጋግራቸዋለች ይባላል፡፡ በዚህ ላይ የሚከተለውን ጽሁፋዊ ማስረጃ እንይ፡፡

‹‹ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ አሐድር እስመ ሐረ ይክዋ›› (ትርጉም ለዘላለም መቀመጫየ ያች ያልኳት ይህች ናት በዚህ አድር ዘንድ መርጫለሁ) ብላ ነግራቸዋለች፡፡ (ከጽሁፍ፣ አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ 20፣ 2010 ዓ.ም) በማለት ጽፈዋል፡፡

ከዚ በመቀጠል ያለውም ተረክ ከዚሁ ጋር ተቀራራቢነት ስላለው በአንድ ላይ ለማየት እንሞክር፡፡

ሌላኛው ተረክ ደግሞ በአብረሃና አጽበሐ የተሰራው ቤተ መቅደስ ተጠናቆ ታቦተ ህጉ ወደ ቤተ መቅደሱ በሚገባበት ሰዓት ቅድስት ድንግል ማሪያምና ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብረሃ ወ አጽበሐ፣ ለአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን እና ሌሎች ለበቁ አባቶች እንደተገለጹ የሚነገር ተረክ እንዳለ ቀደም ሲል ከፋሲካው ጋር በተደረገው ቃለ መጠየቅ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

> ሆኖም ጥር 21 ቀን 333 ዓ.ም ተጠናቆ አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን (ፍሬ ምናጦስ) ቤተ መቅደሱን ባርከው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማሪያምን የቃል ኪዳን ታቦት ደናግል መነኮሳት ይዘው፣ ምዕመናን በዕልልታ፣ ካህናት በዝማሬ ዙረው ወደ ቤተ መቅደሱ ሲገቡ አብረሃና አጽበሐ እንዲሁም አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃንና ሌሎችም እግዚያብሄር የገለጠላቸው ቅዱሳን ሰዎች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ከታቦተ ህጉ ፊት ወደ ቤተ መቅደሱ ከልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስትገባ በግልጽ ታይታቸዋለች፡፡
>
> (ቃለ መጠየቅ፣ ፋሲካው፣ የካቲት፣ 30 2011 ዓ.ም፣መርጡለ ማሪያም ገዳም)

ከዚህ ተረክ የምንረዳው ምርጫን ነው፡፡ ሰው ብቻ ሳይሆን ፈጣሪም ቦታን ይመርጣል፡፡ ‹‹ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት›› እንዲሉ አበው ቦታዋ ከሌሎች ሁሉ በተለየ ተመርጣለች፡፡ ስለሆነም ይህች ገዳም የተቀደሰችና የተከበረች ነች ብሎ ህዝቡ እንዲያምን ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ በአባቶች መንፈስ ቅዱስ አድሮ ከጻድቃን፣ ከሰማዕታት፣ ከመላእክት ብሎም ከፈጣሪ ጋር በራዕይ ወይም ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥና መተያየት አንዱና ዋነኛው መመዘኛ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሀይማኖታዊ ተረክ ለአማኙ ማህበረሰቡ ከማስተማር፣ ከመትከል፣ ከመቆጣጠር አንጻር የሚኖረው ፎክሎራዊ አገልግሎት ቀላል አይደለም፡፡

ከአብረሃ ወ አጽበሐ ፍርስራሽ ቤተ መቅደስ በስተ ሰሜን ምዕራብ፣ አንበሳ ውድምና ሌሎች ነገስታት ከአደፏትና በአሁን ጊዜ አገልግሎት እየሰጠ ከሚገኘው የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በስተ ሰሜን አቅጣጫ የሚገኘው ‹‹ነዋ በግኡ›› እየተባለ ስለሚጠራው እድሜ ጠገብ ፅድ የሚነገረውን ተረክ እንይ፡፡

> ከዚሁ አካባቢ የተወለደ አንድ ዲያቆን ነበር፡፡ እሱም በፀሎተኝነቱና በደግነቱ የታወቀ እንደነበር ይነገራል፡፡ በዚህም የተነሳ የሚሰወርበትም ጊዜ እንደነበር ይነገራል፡፡ በመጨረሻም ዲያቆናቱን ሰብስቦ እንግዲህ እኔ ቦታዬና ቤቴ ይህች ፅድ ነች ብሎ እየተናገረ ጓደኞችን ተሰናብቶ ከዚህ ፅድ ተሰወረ
>
> (ቃለ መጠየቅ፣ መርጌታ ዲበኩሉ፣ መጋቢት 24፣2011 ዓ.ም፣ ገዳሚ ሰበካ ጉባኤ ቢሮ)

ሰው በእግዚያብሄር መልክና ምሳሌ ለእግዚያብሄር ስለተፈጠረ ከእግዚያብሄር ጋር ለመገናኘት ይፈልጋል፡፡ መገናኛውም ፀሎት ስለሆነ ይፀልያል፡፡ ፀሎት ከእግዚያብሄር ጋር ያለን የመገናኛ ምልክትና የግንኙነት ማጽኛ መሳሪያ ነው፡፡ ስለሆነም በፀሎት ላይ ደግነት ሲታከልበት ምልዑ ይሆናልና ሰውን የእግዚያብሄር ፀጋ ይቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ቅዱሳን አባቶች የሚሰወሩት ማንም የማያየው የሚታያቸው ለዚህ ነው፡፡ የዲያቆኑም መሰወር የእግዚያብሄር ጸጋና በረከት አድሮበት የሆነ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ዲያቆናቱን ሰብስቦ ‹‹እንግዲህ እኔ ቦታዬና ቤቴ ይህች ፅድ ናት›› ሲል ጽዱ የክርሰቶስ ተምሳሌት መሆኑ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ይህ ተረክ መባሉ ማህበረሰቡን ፀሎተኛና ደግ ለማድረግ ታስቦ የተባለ ይመስላል፡፡



ምስል6፡- ዲያቆን ነዋ በግው ፀሎት ያደርግበት የነበረውና በኋላም በአፀደ ስጋ የተሰወረበት ጥንታዊ የፅድ ዛፍ፡፡

በዚች ገዳም ውስጥ የምትገኝ የገዳሚ 13ኛ ርዕሰ ርዑሳን የነበሩትን መምህር ዘውዱን አናግራለች የምትባል ስዕለ ማሪያም አሁን አገልግሎት እየሰጠ ከሚገኘው ቤተ ክርስቲያን በስተ ምስራቅ ትገኛለች፡፡

> ሰለዚች ስዕል ሲናገሩ ይህች ስዕል አባታችን ጸሎተኛና ደግ ስለነበሩ ከእለታት አንድ ቀን ጸሎት አድርገው ሲጨርሱ ቀና ብለው ወደ ስዕሏ ሲመለከቱ ‹‹አባ ዘውዱ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና ዕለተ ዕረፍትህ ደርሷልና ደስታ ይገባሃል›› ብላ አነጋግራቸዋለች፡፡ በዚህም ምክንያት ‹‹ኦሆ በሐሊት›› ማለትም ተናጋሪት የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷታል (ምልከታና ቃለ መጠየቅ፣ ዲበኩሉ /መርጌታ/የካቲት 25፣2011 ዓ.ም፣ መርጡለ ማሪያም ገዳም)፡፡ ሲሉ ነግረውኛል፡፡

የዚህ ተረክ መባል አንድም ማህበረሰቡ ለመንፈሳዊያን ስዕሎች የሚሰጠውን ክብር ከፍ በማድረግ እንዲንከባከባቸው፣ እንዲያምንባቸው፣ እንዲመካባቸው፣ እንዲማፀናቸው የማድረግ ተግባር ሲኖረው በሌላ በኩል ደግሞ የጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ‹‹ግማደ መስቀሉ›› በዓጼ ዳዊት ዘመነ መንግስት በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ቅዱስ ሉቃስ በፀዴንያ የሳላት ‹‹ኦሆ በሐሊት›› /ተናጋሪት / በመባል የታወቀችው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ስዕል አብራ ወደ ኢትዮጵያ መጥታለች፡፡ ስለሆነም ይህችን የወንጌላዊው የቅዱስ ሉቃስን ታምረኛ ስዕል ለመጠቆም ተፈልጎ የተባለ ይመስላል፡፡



ምስል7፡- መምህር ዘውዱን ያነጋገረቻቸው ስዕለ ማሪያም፡፡

አሁንም ልክ እንደመምህር ዘውዱ የክርስቶስ ፀጋና ክብር ቀርቧቸው ስለነበሩት መምህር ፈላታዎስ የሚነገረውን ተረክ እንይ፡፡

> መምህር ፈላታዎስ ይባሉ የነበሩት የርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም 23ኛው ርዕሰ ርውሳን በፀሎታቸው የበቁና ለእግዚያብሄር ቅርብ የሆኑ እንደነበሩ ይነገራል፡፡ እኒህ ደግ አባት ዕለተ እረፍታቸው በደረሰ ጊዜ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ቀናቸው የቀረበ መሆኑን በዚች ገዳም ቃል በቃል እንዳነጋገረቻቸው ይነገራል
>
> (ቃለ መጠየቅ፣ ፋሲካው፣ የካቲት30፣ 2011 ዓ.ም፣ መርጡለ ማሪያም ገዳም)፡፡

አሁንም ከዚሁ ጋር የሚመሳሰለው ሌላው ተረክ፡-

> አባ እንጦንስ የተባሉ በገዳሚ ይኖሩ የነበሩ መነኩሴ ከደግነታቸውና ከመንፈሳዊ ብቃታቸው የተነሳ በሚቀድሱበት ጊዜ መላ ሰውነታቸው ከፀሃይ ሰባት እጥፍ ያበራ እንደነበርና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ሁለት ጊዜ አንዴ ፀሎታቸው እንደሰመረና በመጨረሻም ዜና ዕረፍታቸውን ለማብሰር በአካል ተገልጣ እንዳነጋገረቻቸው
>
> (ቃለ መጠየቅ፣ አባ ቃለ ጽድቅ፣ የካቲት 28፣ 2011 ዓ.ም፣ በገዳሚ ዕቃ ቤት ውስጥ) ነግረውኛል፡፡

እዚህ ጋ ሁለት ነገሮችን ልናጤን ይገባል፡፡ አንደኛው በእየ ተረኮቹ መሃል የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ስሟ ተደጋግሞ መነሳት ነው፡፡ ሁለተኛው በገዳሚ ያገለገሉ የእምነት አባቶች በተረኮች ውስጥ ተደጋግሞ መነሳት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ይህን ተረክ ለምን ከነዚህ ሁለት ነገሮች ጋር አያይዞ ሊተርክ ቻለ? የሚለውን ስንመረምር መልሱን እናገኛለን፡፡ ምክንያቱም ሰው የኔ ነው የሚለውን ነገር ያውም እምነቱን ከፍ ከፍ ማድረግ ሰዋዊ ባህሪ በመሆኑ የቦታዋን ክብር አንድም በስሙ በታነጸው ቤተ ክርስቲያን ስም አለያም በቤተ ክርስቲያኗ በሚያገለግሉ አባቶች ስም ተረኮችን በማያያዝ እንደሚተርኩ እንገነዘባለን፡፡ ስለሆነም የእኛ ታቦት እኮ ታምረኛ ነች! የእኛ የእምነት አባቶች እኮ ከሁሉም በላይ የበቁ ናቸው! በአጠቃላይ ተረኩ የእምነቱን ትክክለኛነትና አዳኝነት ለማሳየት የተሞከረበት በሚመስል መንፈስ የተባለ ይመስላል፡፡ በመሆኑም

ማህበረሰቡ በዚህ ተረክ የተነሳ ለገዳሟም ሆነ ለእምነት አባቶች የሚሰጠው ክብርና የሚኖረው አመለካከት ልዩ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህም ነው ከተረክ ተግባራት ውስጥ አንዱ እምነትን ማፅኛ ነው የሚባለው፡፡

### 5.1.4 በገዳሟ የተፈጸሙ የፈውስ ተረኮች

ሃይማኖታዊ ፈውስ አንድ አካላዊ ወይም ስነልቦናዊ ችግር ያለበት ሰው ለአካላዊውም ሆነ ለስነልቦናዊ ችግሩ በእምነቱ የሚያገኘው ድህነት ነው ሊባል ይችላል፡፡ በመሆኑም ሰዎች በመስቀል በመታሸት፣ በአባቶች ፀሎት፣ በፀበል በመጠመቅ ወይም በመጠጣት ወዘተ ፈውስ ያገኛሉ ተብሎ የሚታመንባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተረኮችም ከዚ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ የተካተቱ በቅዱሳን ነገስታትና ቅዱሳን አባቶች የተፈጸሙትንና ከገዳሟ አጠገብ ስለሚገኘው የፀበል ቦታ የተነገረውን የፈውስ ተረኮችን የምናይ ይሆናል፡፡

‹‹ሰዎች በመድኃኒት ሲያምኑ በነፍስ ሊጠነክሩ ይችላሉ፤

ጥቅሙ ከእምነት እንጅ ከመድኃኒት አልነበረም፡፡›› እንዲሉ አበው በጥንት ጊዜ ሰዎች በእምነታቸው ይፈወሱ ነበር፡፡ የዛሬው የህክምና ሳይንስ እንዳይሰማን ድምጻችንን ዝቅ ¡

ያ ማለት ዛሬ ፈውስ በእምነት የለም ለማለት ሳይሆን እየሰራነው ያለው ስራ ከፈጣሪ ጸጋና በረከት አርቆን እንጅ፤ ቢሆንም እሱ ፈጽሞ አይተወንምና አሁንም አልፎ አልፎ የፈውስ ተዓምራትን ማየትም ሆነ መስማታችን አልቀረም፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ከአብረሃ ወ አጽበሐ እና ከአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን፣ ከዓጼ በዕደ ማሪያም፣ ስለቅዱሳን አባቶች እና ከገዳሟ አጠገብ ስለሚገኘው ፀበል የሚነገሩ ተረኮች ማሳያዎች ናቸው፡፡

አብረሃ ወ አጽበሐንና አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃንን የወሎ ህዝብ ሽኝቶ የጎጃም ህዝብ ከተቀበለ በኋላ ከአባይ ተነስተው መርጡለ ማሪያም እስከ ደረሱ ድረስ ማህበረሰቡን እየፈወሱና እያዳኑ ከቦታው እንደደረሱ (ጽሁፋዊ ማስረጃ፣ አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ 17፣ 2010ዓ.ም) ያስረዳሉ፡፡

እኒህን ቅዱሳን ነገስታትና አባ ሰላማን ለመቀበል የመጡ ዐይነ ስውራን በአባቶች መስቀልና እጅ በመታሸትና በመዳሰስ ሴቶች ዓይናቸው ስለበራላቸው ደስ ብሏቸው የእግዚያብሄር ሰዎች ናቸው ብለው ሲያደንቁ ሰምተው ‹‹ርዕያ አንስት ወ አንክራ›› ብለው ስለነበር ያቦታ ዛሬ ድርስ ‹‹ወርያ›› እየተባለ ይጠራል፡፡ ቀጥሎ ወደ ደብር መድሃኒት አምርተዋል፡፡ ከቦታው ላይ ሲደርሱ እነሱን ለመቀበል ከቤቱ ከወጣው ሰው ለምጻሞች እየነጹ፣ አንካሶች እየረቱ፣ ዐይነ ስውሮች ዓይናቸው እየበራ፣ ጎባጦች እየቀኑ፣ መስማት የተሳናቸው እየሰሙ፣ ህመምተኞች እየተፈወሱ ያዩበትን ቦታ ደብር መድሃኒት ብለው ሰይመውታል፡፡ በዚህም ምክንያት ለዚህ ቦታ መጠሪያ ስም ሆኖት ‹‹ደብረ መድሃኒት››[12] ተብሎ እየተጠራበት ይገኛል፡፡

ኢየሱስ ዐስራ ሁለቱ ሀዋሪያት ድውያንን እንዲፈውሱ ስልጣን ሰጣቸው፤ ማቴ. 10፣1 በተባለው አምላካዊ ቃል መሰረት ቅዱሳን አባቶች ከበሽታ የመፈውስ፣ የማያይን አይን የማብራት፣ ጎባጦችን የማቅናት፣ ለምጻሞችን የማንጻት፣ የሞተን የማስነሳት ወዘተ ከእግዚያብሄር የተሰጣቸው ፀጋ አለ፡፡ በመሆኑም ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እነዚህ ፈውሶች በየገዳማቱና አድባራቱ የፀበል ቦታዎች ሲከሰቱ ማየት የተለመዱ ክስተቶች ናቸው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ አንድ አካባቢ በተፈፀመበት ሰናይም ሆና እኩይ ተግባር ስያሜውን ሊያገኝ እንደሚችል ነው፡፡

ዓፄ በዕደ ማሪያም የመርጡለ ማሪያምን ገዳም ካሳደሱ ነገስታት ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡ እድሳት በሚያደርጉ ጊዜ የልጃቸውን የዓፄ ናኦድን ልጅ ዘንዶ ነክሶ እንደገደላትና ዓፄ በዕደ ማሪያም ባደረጉት የድረሱልኝ ፀሎት ኣባ ኤልያስና ኣባ ሰርፀ ጴጥሮስ ህጻኗን ከሞት እንዳስነሷት የሚነገር ተረክ አለ፡፡ ስለዚህ በጽሁፍና በቃል ያገኘሁት መረጃ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ዓፄ በዕደ ማሪያም ዩዲት ጉዲት /አስቴር/ ካቃጠለችው ቤተ ክርስቲያን በስተ ምዕራብ በኩል ባለው ፍርስራሽ ላይ የቤተ ክርስቲያኑን ስራ አስጀምረው ሳለ ከዚህ መጣ ያልተባለ ዘንዶ የልጃቸውን የዓፄ ናኦድን ልጅ ማርታን ነክሶ ገደላት፡፡

---

[12]በአሁኑ ሰዓት ‹‹ደብረ መድሃኒት›› ከስሙ በተጨማሪ (020 ቀበሌ) እየተባለ እንደሚጠራ እና ‹‹ወርያ›› ደግሞ ‹‹ወርያ መስቀል›› ወይም (032 ቀበሌ) የሚባለው እንደሆነ ልብ ሊሉ ይገባል።

ንጉሱም በእኔ ክፉ ስራ እንጅ የእሷ ሆኖ አይደለም በማለት ወደ እመቤቴ ፀሎት አደረጉ፡፡ ፀሎታቸውም ሰምሮ በእመቤታችን ትዕዛዝ አባ ኤልያስ በነፋስ ሰረገላ ከእንጦጦ ሃመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም (የቀድሞዋ አሸክላ ገዳም)፣ አባ ሰርፀ ጴጥሮስ ከደብረ ወርቅ ማሪያም (ምስራቅ ጎጃም ከምትገኘው) በቦታው በመገኘት አባ ሰርፀ ጴጥሮስ ወደ ህጻኗ ሙት አካል በመሄድ ‹‹በአምላክ እናት በድንግል ማሪያም ስም በአባ ኤልያስ ፀሎት አንች ህጻን ተነሽ›› ባሏት ጊዜ እንደ ፀሃይ የምታበር እጅ በድኗን ዳሰሰቻት፤ በድኑም ተንቀሳቀሰ፤ ‹‹መግነዙን ፍቱልኝ በአባ ኤልያስና በዚህ መነኩሴ ፀሎት ነፍሴ ወደ ስጋየ ተመልሳለች፡፡ ይህም በፊታቹህ የቆመው መነኩሴ የእመቤታችን የድንግል ማሪያም ወዳጅ ስለሆነ ስለፅርሱ ከሞት ዳንኩ›› ብላ ድምፅ አሰምታ ስትናገር መግነዟን ፈቱና በህዝብ መካከል አቆሟት፡፡

(ጽሁፋዊ ሰነድ፣ አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ 2010፣39-40፤ ዲበኩሉ /መርጌታ/) ይላል፡፡

በላይኛው ተረክ ላይ እንደተጠቀሰው ቅዱሳን አባቶች በፀሎታቸውና በግብራቸው የበቁ ከሆኑ ተዓምራትን እንደሚሰሩ ይታመናል፡፡ ከዚህ ተረክም የምንረዳው ይህንኑ ነው፡፡ ቅዱሳን አባቶች በፀሎት ይረዳዳሉ ይተሳሰባሉ፤ በጻድቃን ሰማዕታት ተራዳይነት ይታገዛሉ፤ በመላእክትና በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ስራቸውን ይሰራሉ፡፡ የዚህ ማሳያ በተረኩ ውስጥ ‹‹ልጅቷ በዘንዶ ተናክሳ እንደሞተችና እንደ ፀሃይ የምታበራ እጅ በድኗን ዳስሳት እንደዳናች›› ይነግረናል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ነገሮች እንዴት ሊባሉ ቻሉ? ብለን ስናስብ ዘንዶ በማህበረሰቡ ዘንድ አስፈሪና እርኩስ ፍጥረት ተደርጎ ከመታሰቡ በተጨማሪ ከዚሁ ጋር በሚመሳስል ሁኔታ የአስፈሪ አውሬና የሰይጣን ተምሳሌት እንደሆነ ራእ. 21፣15፣ 15፡16 በግልጽ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ በሌላ መልኩ ፀሀይ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ የጥሩ ነገር ምሳሌ እንደሆነች ይታወቃል፤ በመጽሀፍ ቅዱስም የእግዚያብሄርን ታማኝነት ያመለክታል (መ.ዝ 19፣4-6) እንዲሁም ፀሀይ የጻድቃን ተምሳሌት ነች፡፡ ስለሆነም ሙት አካሉን የዳሰሰቻት እጅ የጻዲቁ አባታችን የአባ ኤልያስ ነች ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በሰይጣን የተለከፉ ምዕመናን በጻድቃን አባቶች ጸሎትና ምህላ እንደሚድኑ ሁሉ ልጅቷም ከሰይጣኑ የመቅሰፍት ሞት በጻዲቁ አባታችን በአባ ኤልያስ የዳነች መሆኑን ከማሳየቱ በተጨማሪ ሰይጣን በቅዱሳን አባቶች ፊት ምንም ስልጣን እንደሌለው ለማሳየት የተባለ ነው ልንል እንችላለን፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ይህ ተረክ እንደዚህ መባሉ ተረኩን የሚሰማው ማህበረሰብ በጎ ስራን የሚሰራ ሰው በእርኩስ መናፍስትም ሆና ከአቅሙ በላይ የሆነ ሌላ ችግር ሲያጋጥመው ከልቡ ወደ አምላኩ ልመና ካደረገ ልመናው እንደሚሰማ ለማስተማር ተፍልጎ ነው ሊባል ይችላል፡፡

አሁን ደግሞ አባ ዝክረ ማሪያም ይባሉ የነበሩት የገዳሟ ሁለተኛው ርዕሰ ርዑሳን በሃይማኖታቸው የፀኑና ፀጋ እግዚያብሄር የቀረባቸው ከመሆኑ የተነሳ በፀሎታቸው ድውይን /ህሙማንን/ የሚፈውሱ አባት እንደነበሩ ይነገራል፡፡

> ከዕለታት አንድ ቀን ከደጀ ሰላም ሄደው ዓይኑ የጠፋ ደካማ ሰው እንዳገኙና ሊያናግሩት ቢሞክሩ ዝም እንዳላቸው፤ ጓደኞቹን ሲጠይቁ ዓይኑ ብቻ ሳይሆን ጆሮውም እንደማይሰማ ይነግሯቸዋል፡፡ ያኔ እኚህ ደግ አባት ልባቸው ተሰብሮ ለሊቱን ሙሉ በዋይታ ፀሎት ሲያደርጉ አድረው ጠዋት ላይ እምባቸውን በእፍኛቸው አምጥተው ሲረጩትና ሲዳስሱት ዓይኑም አየ፤ ጆሮውም ሰማ ብለዋል፡፡
>
> (ቃለ መጠየቅ፣ የካቲት 28፣ 2011 ዓ.ም አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ መርጡለ ማሪያም ገዳም በብህትና ቤታቸው)

ይህ ተረክ እንዴት ሊባል ቻለ? ስንል ሁለት ነገር እንድናነሳ ይጋብዘናል፡፡ የመጀመሪያው እግዚያብሄር ሊያድን ሲፈልግ በሰበብ መሆኑን ለማስተማር ተፈልጎ የተባለ ነው ልንል እንችላለን፡፡ ምክንያቱም በነዚያ ደካማ ሰው በማስመሰል አማኙን ማህበረሰብ ፈውስ በሰበብና በምክንያት ሊገኝ እንደሚችል ማስተማሪያ ሆኖ የገባ ይመስላል፡፡ የፈውስ ማግኛ መንገዶች ብዙ መሆናቸውን ማሳየቱ እንዳለ ሆኖ፡፡ ሁለተኛው አማኙን ማህበረሰብ የእምነት አባቶች ‹‹የእግዜር ታናሽ ወንድም›› መሆናቸውን ለማሳየት ተፈልጎ ነው፡፡ ይህ ሲባል ‹‹ክርስቶስ ለተከታዮቹ ስልጣንን ሰጠ፤ ማር.3፣15፤ ሉቃ.10፣19›› የሚለውን አምላካዊ ቃል አማኙ ማህበረሰብ ሁል ጊዜ መዘንጋት እንደሌለበትና ክብር ለሚገባው ክብር መሰጠት እንዳለበት ለማስተማር ነው፡፡ ይህም ተረክ በማር. 7፣31-37 የሚገኘውን ደንቆሮና ዲዳ የነበረ ሰው ፈውስ ያገኘበትን ተረክ ያስታውሰናል፡፡

### 5.1.5 በገዳሟ የተፈጸሙ የገቢራት ተአምራት ተረኮች

ተአምር ብዙን ጊዜ በዓለም ያልተለመደውንና የማይሆነውን ማድረግ ወይም ሆኖ ማየት ነው፡፡ ከዚህ በታችም ከገዳሟ ውስጥ በሚገኙ ሁለት የወይራ ዛፎች እና በደርግ ዘመነ መንግስት ተፈጥረዋል ተብለው የሚነገሩትን ተአምራት እናያለን፡፡

> ዓፄ በዕደ ማሪያም[13] አሁን በማገልግል ላይ የምትገኘውን የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን እያሳደሱ እያለ በሰሜንና በደቡብ በኩል የሚገኙ ሁለት የጥንት የወይራ ዛፎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ጣራ ለመስራት ከላይ ሆነው ስለከለከሉ ንጉሱ እንዲቆረጡ በአዘዙ ጊዜ በሚገርም ሁኔታ ጣሪያውን የያዘው የሁለቱም የወይራ ዛፎች ክፍል ለቆ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ዛፎቹ እንዲቆረጡ እመቤታችን ስላልፈቀደች ነው ብለው የሰራችውን ድንቅ ተአምር ለመግለጽ ከዚያ ወዲህ የዛፎቹን መጣመም ‹‹ግንደ አጥም ማሪያም›› ይላሉ፡፡ (አባ ኃይለ ማሪያም፣ 30፣2011 ዓ.ም)

ከዚህ ተረክ የምንገነዘበው የነገሮች ሁሉ መሆን የፈጣሪ ፈቃድ እንጅ የሰው አለመሆኑን ነው፡፡ ሰዎች የታያቸውን ሊያደርጉ አሰቡ ፈጣሪ መሆን የሚገባውን አደረገ የሚለውን፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ቀደም ሲል ‹‹የግራኝ እመቤት›› ያልንበትን የተረክ ዓይነት አስታውሶ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ገዳም በሚያደርጉት የተለያዩ ተአምራት /ተግባራት/ የተነሳ ስያሜ[14] ሊያገኙ እንደሚችሉ ይነግረናል፡፡ በመሆኑም እኒህን ግብር ገላጭ ስያሜዎች ልታገኝ ችላለች፡፡

---

[13] የጥንቱ ቤተ መቅደ ከፈረሰና አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ከተሰራ በኂላ ገዳሟን ካሳደሱ ነገስታት ውስጥ አጼ ዳዊት /3ኛ/፣ አጼ ገላውዲዮስ፣ አጼ ናዖድ፣ አጼ በእደማሪያም (ሚስቱ ንግስት እሌኒ የቤ/ ክርስቲያኑን አጥር)፣ ንጉስ ትክለ ሃይማኖት፣ እራስ ኃይሉ በዋናነት ተጠቃሾች እንደሆኑ የተገኘው ጽሁፋዊ ሰነድ ያስረዳል፡፡

[14]ቅፅል ስያሜን በተመለከተ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ከግራኝ አህመድ ጋር በሚመሳሰል የታሪክ ሁነት ‹‹የጓንጉል እመቤት እና የአስፋው ኃይሉ እመቤት›› ትባል እንደነበር የጽሁፍና የቃል ሰነዶች የሳያሉ፡፡



ምስል9፡- ሊቆረጡ ከነበሩ የወይራ ዛፎች ውስጥ የቤተ ክርስቲያኑን ጣራ ለቀው ከተገኙት ውስጥ በስተ ደቡብ ያለው፡፡

የደርግ መንግስት በነበረው ሃይማኖታዊ አቋም የተነሳ በመርጡለ ማሪያም ገዳም በተሰበሰበው ህዝበ ክርስቲያን ላይ የደርግ ጦር ሰራዊት ሊያደርሰው የነበረው ጭፍጨፋ በእመቤታችን ድንቅ ተዓምር ሳይሳካ እንደቀር በእኔ እድሜ በዓይኔ ያየሁት ነው በማለት (አባ ኃይለ ኢየሱስ መጋቢት 27፡፡2011 ዓ.ም) ያጫወቱኝ ደግሞ የሚከተለው ነው፡፡

> ጥር 10 ቀን 1968 ዓ.ም ከሌሊቱ ስድስተ ሰዓት ጀምሮ ቤተ መዘክሩን ሰብረው በመግባት ውድ የሆኑ ዕቃዎችን ወደ ካምፕ ጭነው ወሰዱ፡፡ ይህ አልበቃ ብሏቸው ለሊት ቤታቸውን እየሰበሩ ሲደበድቧቸው እያመለጡ ወደ ገዳሚ መጥተው የተጠለሉ ክርስቲያኖችን እየሰበሰቡ ከገዳሚ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኘው የስላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካስገቡ በኋላ በሶስቱም በር ባለ ሁለት እግር መትረየስ ጠምደው ክርስቲያኖችን ለመፍጀት የተመደቡ ወታደሮች ትዕዛዝ እየተጠባበቁ ሳለ ከህዝቡ ጋር የነበሩ በጸሎት ተግተው የሚኖሩ ከእኔ ጋር ሁለት የገዳሚ አገልጋይ ካህናት ማለትም ታዋቂ የቆሜ ድጓ መምህር የሆኑት መርጌታ

ምትኩ ተገኘ እና በገዳሚ ከነበሩት መደበኛ ቀዳሽ ደናግል መነኮሳት በነባርነትና በአጽንኦት በአት የሚታወቁት ፀሎተኛው አባ ዩሐንስ ታደለ መትረየስ ከተጠመደባቸው ፊት ቀመው ‹‹የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማሪያም ከዚህ ጭንቅ ታድናለች በፍጽም እምነት ድረሽልን›› እያላችሁ ወደ አምላክ እናት አልቅሱ በማለት እኚህ አባት አወጁ፡፡ ህዝቡም አዘነ፣ እነሱም ተዘባበቱ በመጨረሻም በጦር አዛዦቹ በመቶ አለቃ አበበና በመቶ አለቃ ምስጋናው ለተኳሾች ህዝቡን እንዲመቱ ትዕዛዝ ተሰጠ፡፡ በሶስቱም በር የተጠመዱ መትረየስ ተኳሾች በህዝቡ ላይ አነጣጥረው ሊመቱ ምላጭ ሲስቡ የሶስቱም ተኳሾች መሳሪያ መተኮስ አልቻለም፤ ወደ ሰማይ ሲሉት ይተኩሳል፡፡ ያኔ በንዴት መቶ አለቃ ምስጋናው ተኳሹን ልቀቅ ብሎ ገፍትሮ ካህናቱ ባሉበት በር የተጠመደውን መትረየስ ተቀብሎ ምላጭ ሲስብ በጦር እንደተወጋ ድምፅ አሰምቶ ወደ ኋላ ተፈነገለ፡፡ ያኔ የደነገጡ ሌሎች ወታደሮች አለቃቸውን ይዘው ወደ ካምፓቸው ሄዱ ሲሉ ነግረውኛል፡፡

ይህ ተረክ ሁለት ነገሮችን ያስተምራል፡፡ አንደኛው በተረኩ እንዳየነው አቅም አለኝ፣ መሳሪያ አለኝ ብሎ የመጣው ሰራዊት ባልታሰበና ባልተገመተ ተአምር አላማውን ሳያሳካ አፍሮ እንደተመለሰና ህዝቡ ደግሞ በተፈጠረው ሁነት የአሸናፊነት መንፈስ ሲላበስ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ተረክ ማህበረሰቡ ቅድስት ድንግል ማሪያምን አምኖ የተጠጋ ከጭንቅና ከመከራ እንደሚድን፣ ጥላና ከለላ እንደምትሆነው ለማሳሰብ ሲሆን ወይም ደግሞ ምዕመኗን የሚዳፈር ማንኛውም ኃይል እንደማይሳካለትና ሊያደርጉ ከሚያስቡት መጥፎ ተግባር እራሳቸውን ማራቅ እንደሚገባቸው መልዕክት ለማስተላለፍ የተፈለገ ይመስላል፡፡

ሁለተኛው ቁም ነገር ማህበረሰቡ ለሃይማኖቱ ያለው ቦታ እና አተያይ እጅግ በጣም የጠነከረ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም እምነት አዳኝ ነው፡፡ እምነት እግዚያብሄር በሰጠው የተስፋ ቃል መተማመንና መደገፍ ነው፡፡ ይህንንም በመረዳት በእምነታቸው ከገቡበት ጭንቅና መከራ ድነዋል፡፡ ለዚህም ነው ማህበረሰባችን ከማይደራደርባቸው ጉዳዮች ውስጥ ሃይማኖት ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው፡፡ እምነቱ ተስፋው ነው፤ እምነቱ የዚች አለም እንቆቅልሽ መፍቻ ቁልፉ ነው፡፡ በመሆኑም አጥብቆ ይይዘዋል ጥብቅ አድርጎ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ እግዚያብሄር በአባ እንድሪያስ አድሮ በክፉዎች ላይ አድርጓል የሚባለውን ተረክ እናያለን፡፡

አባ እንድሪያስ ይባሉ የነበረ በንጽህናና በድንግልና ተወስነው በገዳሚ ይኖሩ የነበሩ አባት ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንዱ በቅኔ ማህሌት በመገኘት ውዳሴ ማሪያም ሲያድሉ ከሚታደሉት መካከል አንዱ አንተ ውዳሴ ማሪያም ማደል አይገባህም፡፡ አንተ ኃጢያተኛ መነኩሴ ነህ እንዲያውም ልጅ ወልደሃል በማለት እንደሰደባቸውና ወደ ቤቱ ሄዶም የእሳቸውን ስም እያጠፋ እያለ የገዛ ምራቁ ትን ብሎት ይሞታል፡፡ ያኔ ቤተሰቦቹ ከመነኩሴው በዓት ሄደው ክፉኛ ይደበድቧቸዋል፡፡ የተደባደቡትም ሰዎች ሰውነታቸው አብጠ፣ ቆሰለ፣ ሁሎችም ተዝለፍልፈው ወደቁ፣ በዚህን ጊዜ ስቃዩ ስለፀናባቸው አባታችን እጅግ ደግ ሰው ተሳድቦ የእኛም እጅ ስለተላለፈ እግዚያብሄር ተቆጥቶ ነው በማለት እኚህ ጻዲቅ አባት ፀሎት እንዲያደርጉላቸው ይጠይቃሉ፡፡ መነኩሴውም ፀሎት አድርገው እግዚያብሄርን ተማጽነው ቢዳስሷቸው ሁሎችም ድነው በሰላም ወደ ቤታቸው እንደተመለሱ (አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ የካቲት 29፣ 2011 ዓ.ም) አጫውተውኛል፡፡

ከዚህ ተረክ የእምነት አባቶችን ማክበር እንደሚገባን ካልሆነ ግን አወዳደቃችን እንደሚከፋ፣ ሰዎችን ካለ ግብራቸው ስብዕናቸውን ዝቅ ማድረግ /ስማቸውን ማጥፋት/ ለመጥፎ ነገር እንደሚዳርግ በአጠቃላይ ውሸትን መጸየፍ እንደሚገባን ከማስተማር በተጨማሪ ይቅር ባይነትንም ያስተምረናል፡፡ በመሆኑም የዚህ ተረክ መተረክ ማህበረሰቡን ሃቀኛ፣ ሰው አክባሪ፣ ይቅርባይነትን ወዘተ ለማስተማር ተፈልጎ የተባለ ነው ልንል እንችላለን፡፡

### 5.1.6 ከገዳሚ መመስረት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ትንቢት ነክ ተረኮች

ትንቢት በጣም ሰፊ ጽንስ ሀሳብ የተሸከመ ቃል ቢሆንም ቀለል ባለ አገላለፅ ወደ ፊት የሚሆን ወይም የሚፈፀም አወንታዊ ወይም አሉታዊ ነገር ወይም ሁነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ይዘቱን ስናይ ‹‹እግዚያብሄር በብዙ ዓይነትና በብዙ መንገድ በነቢያት በኩል ተናገረ፣ ዕብ. 1፣1፡፡›› የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የተባለውን ተረክ የእግዚያብሄር መንፍስ በቅዱሳን ነገስታትና ቅዱሳን አባቶች አድሮ የተነገረ የትንቢት ቃል ነው ሊባል ይችላል፡፡

ወደ ተረኩ ስመለስ፣ ቀደም ሲል በገዳሚ ታሪካዊ አመሰራረት ላይ እንደገለጽኩት የፍቁራን አሐው አብረሃ ወ አጽበሐ እና አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬ ምናጦስ)

ከአክሱም ጽዮን ተነስተው በወሎ ክፍለ ሀገር አቋርጠው ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር እንደሄዱ ጠቅሰን ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የተናገሩት ትንቢት ዛሬ ቀኑ ደርሶ ተፈጽሞ ይገኛል፡፡

> እሱም፣ አብረሃ ወ አጽበሐ እና አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በወሎ ህዝብ መልካም ሽኝት ተደርጎላቸው አባይ ወንዝ ደረሱ የአባይንም ወንዝ ሙሴ ህዝበ እስራኤልን ከግብጽ ይዞ ሲሄድ የኤርትራ ባህር ምልቶ አላሻግርው ቢል በያዘው ትምህርተ መስቀል ባህሩን ሲባርከው ግራና ቀኝ እንደተከፈለለት እና ህዝቡን ይዞ ባህረ ኤርትራን በደረቅ እንደተሻገረ ሁሉ አኒህም ነገስተ ኢትዮጵያ አብረሃ ወ አጽበሐና አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን ልክ እንደ ሙሴ እግዚያብሄርን በጽሎት ጠይቀው ዓባይን በመስቀል ሲባርኩት ውሃው ለሁለት ተከፍሎላቸው እንኳን ውሃ ጭቃም ሳይነካቸው በደረቅ ምድር ላይ ተሻግረው ጎጃም ምድር እንደደረሱ የጎጃምና የወሎን ህዝብ ሰብስበው ቃለ እግዚያብሄር ካስተማሩ በኋላ ከጊዜ በኋላ የጎጃምና የወሎ ህዝብ ያለ ምንም ችግር ክረምት ከበጋ በደረቅ መገናኘት እንደሚችል ተናገረው ከጎጃም ህዝብ ጋር ጉዟቸውን ጀመሩ (መርጌታ ዲበኩሉ፣ መጋቢት፣ 21፣ 2011ዓ.ም) በማለት ነግረውኛል፡፡

እንደሚታወቀው በአሁኑ ሰዓት የጎጃምና የወሎ ህዝብ እንደድሮው መልካ /መሻገሪያ/ ፍልጎ በዋና ተሻግሮ መገናኘት ሳይሆን አስፋልት ተሰርቶለት ካለምንም ችግር በእግር ብቻ ሳይሆን በመኪናም ጭምር ቀን በቀን እየተገናኘ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የአካባቢውን ማህበረሰብ ይህን ተረክ መሰረት በማድረግ የአባቶች ቃል ምን ያህል ትክክለኛና ጠቃሚ እንደሆነ ለማስገንዘብና ማክበር እንደሚገባቸው ለማሳየት ተፈልጎ የተባለ ይመስላል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ያለው ደግሞ ከብዙ ዓመት በፊት ከጠበል መፍለቅ ጋር (ስለፈውስ ተረክ ያወራንለት የጠበል ቦታ ነው) ተያይዞ የሚነገር የትንቢት ተረክ ነው፡፡ ተረኩም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

‹‹ይህ ጠበል እንዲሁ በአጋጣሚ የፈለቀ ሳይሆን በድሮ ጊዜ እዚህ ቦታ ላይ ብዙ ሰዎችን የሚያድንና ታምራትን የሚሰራ ፀበል እንደሚፈልቅ በትንቢት ተነግሮለት እንደነበርና የትንቢቱም ቀን ደርሶ ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ጀምሮ ብዙ ፈውስን እያስገኘ ይገኛል (ፋሲካው፣ መጋቢት 3፣ 2011 ዓ.ም)›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ስለዚህ ይህ ተረክ በመነገሩ ማህበረሰቡም ሆነ ከሌላ ቦታ የሚመጣው ሰው ፀበል ለመሆኑና ላለመሆኑ ሳይጠራጠር በሙሉ እምነት እንዲመጣ የማድረግ ትልቅ አቅም አለው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በድሮ ጊዜ ትንቢት የተነገረለት መሆኑ ከሌሎች ፀበሎች የተመራጭነትና የሚሰጠው የይፈውሰኛል /ያድነኛል/ እና ያድንለኛል ግምት ከሌሎች የተሻለ የማድረግ ኃይል አለው፡፡ በመሆኑም ከተለያየ አካባቢ ወደ ዚህ ጠበል የሚመጣውን የጠበልተኛ ቁጥር እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ ይህም የሚያመለክተው አማኙ ማህበረሰብ ለጠበሉ የሚሰጠው ቅድስናና ክብር ከፍተኛ መሆን ማስቻሉን ነው፡፡

### 5.1.7 ከራዕይ ጋር በተያያዘ የሚነገረው ተረክ

የዚች ገዳም ብዙ ነገሯ ከታሪካዊ አመሰራረቷ ጋር በመያያዙ አሁንም ወደ ገዳሚ ታሪካዊ አመሰራረት እንመለስና የሀዲስ ኪዳኑን ቤተ ጸሎት ለመስራት ሙከራ ባደረጉ ጊዜ መሬቱ እሳት እየተፋ፣ ሰራተኞችም ጤናቸው እየታወከ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ያኔ ሱባኤ ገብተው ሁሉም አንድ አይነት ራዕይ አይተዋል፡፡ ሙሉ ተረኩ እንደሚከተለው ነው፡፡

> ሱባኤ በገቡ በሶስተኛው ቀን ሁሉም አንድ አይነት ራዕይ አዩ፡፡ እሱም ህንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ሊሰሩ ከፈለጉበት ቦታ ግንብ በወሬ፣ /በወሬ የቀረ ግንብ ለማለት ነው/ አስራ ሁለት በር ያለው የብርሃን ድንኳን ተዘርግቶ ከውስጡ መልከ መልካም ጎልማሳ ተቀምጦ መላእክት መሰል ሰዎች ከድንኳኑ ውስጥ ካለው ሰው ላይ ሲደርሱ ሰግደው ሲወጡ ሲገቡ እያዩ ያ ባለአስራ ሁለት በር የብርሃን ድንኳን ተነስቶ ቀደም ሲል የሀዲስ ኪዳን ቤተ ፀሎት ከብሉይ ኪዳን ቤተ ፀሎት (ምኩራብ) አናጠጋጋም ወደ ተባለበት ቦታ ሄዶ ሲያርፍ ድንኳኑ ሜዳውን ሞልቶ ወደ ላይም ሰማይ ገጭቶ ሳለ እኒያ መላእክት መሰል ሰዎች እጅግ በዝተውና ሜዳውን ሞልተው ሰው በሰው እየሆኑ ከድንኳኑ ውስጥ ካለው ሰው ላይ ሰግደው ሲወጡ ሲገቡ ያያሉ፡፡ (መረጌታ ዲበኩሉ፣ መጋቢት፣18፣ 2011 ዓ.ም) ይላል፡፡

በዚህ ተረክ ውስጥ ከሱባኤ አገባቡ በመነሳት ‹‹በሶስተኛው ቀን››፣ ‹‹አንድ አይነት ራዕይ››፣ ‹‹አስራ ሁለት በር ያለው የብርሃን ድንኳን››፣ ‹‹መልከ መልካም ጎልማሳ›› የሚሉትን መሰረታዊ የሆኑ ሀረጎች ላይ በማተኮር ተረኩ ለምን እንዲህ ሊባል እንደተፈለገ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

ከላይ በፎቶ በተደገፈው ስዕላዊ ማሳያ ለመገለጽ እንደተሞከረው የሀዲስ ኪዳኑ ሊቀ ካህን ሱባኤ የያዘበት ከሊቀ ጳጳሱ አባ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን /ፍሬ ምናጣስ/ በትይዩ ከገዳሟ በስተ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ሲሆን፣ ንጉስ አብረሃ ደግሞ ከወንድሙ በአሻጋሪ ከገዳሟ በስተ ሰሜን ምስራቅ ነው፡፡ አባ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን ደግሞ ከገዳሟ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ሲሆን፣ ንጉስ አጽበሃ ከወንድሙ በስተ ግራ ከገዳሟ በስተ ደቡብ ምዕራብ ነው፤ ሌላው የኦሪቱ ሊቀ ካህን ሚናስ ከገዳሟ በስተ ምስራቅ አቅጣጫ በመሆን እንደነበር ይነገራል፡፡ ከላይ በምስሉም ለማሳየት እንደተሞከረው የሰዎቹ ብዛት አምስት ሆኖ የሱባኤው አያያዝ መስቀለኛ ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ በተጠኝው ማህበረሰብ እምነት አምስት ቁጥርና መስቀል ቅርጽ ምን ትዕምርት ሊኖራቸው ይችላል ብለን ስንመረምር ምናልባትም የሰዎቹ ብዛት አምስት መሆናቸው በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት የአምስቱ አዕማደ ሚስጥራት ምሳሌ አድርገን ልናየው ስንችል፡፡ መስቀለኛ መሆኑ ደግሞ ‹‹መስቀል የቅድስና ቃል ነው፡፡ ይህም ከክርስቶስ መስቀል ጋር በእምነት ተባባሪ መሆን ከኃጢአት ፍርድ መዳን ብቻ ሳይሆን ከኃጢአትና ከዓለም ኃይልም መላቀቅ ነው፤ በቅድስና ለመኖር ኃይል ነው፤ገላ. 2፣20፤5፣24፤66፣14፡፡›› የሚለውን መጽሃፍ ቅዱሳዊ ሀተታ ያስታውሰናል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ሀሳብ በመንደርደር የሚከተለውን ሀሳብ መሰንዘር ይቻላል፡፡ መስቀል ቅርጽ መያዙ የተሰራው ስራ /ሱባኤ/ የተቀደሰ፣ የተባረከ፣ የተሳካ የሆነው በዚህ ቅርጽ ስለሆነ ነው የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ታስቦ የተባለ ሊሆን ሲችል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በዚህ ተረክ አማካኝነት አማኙን ማህበረሰብ ለመስቀል የሚሰጠው ክብር ከፍ ከፍ እንዲልና ምናልባትም መስቀል ኃይልና ቤዛ ነው የሚለውን ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ለማስተማር ተፈልጎ ሊሆን ይችላል፡፡

ሶስተኛ ቀን ሲነሳ ፈጣሪ ይህችን ዓለም ሲፈጥር ከሰራቸው ስራዎች ‹‹እግዚያብሄር ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርንና ቡቃያን በምድር ላይ ታብቅል አለ፣ ሆነ፣ ዘዳ. 1፣11›› የሚለውን አምላካዊ ቃል ያስታውሰናል፡፡ ሳሩንና ቡቃያውን የክርስቶስን ቃል በሚያስተምሩ ሃዋሪያት ስንመስለው፣ በሶስተኛው ቀን የታየው አንድ አይነት ራዕይ በአንዲት ሃይማኖት ሊመሰል ይችላል፡፡ ራዕዩም አስራ ሁለት በር ያለው የብርሃን ድንኳን ነው፡፡ አስራ ሁለት በር ያለው መሆኑ ከአስራ ሁለቱ ሀዋሪያት ጋር መስለን ልናየው እንችላለን፣ ብረሃኑ ‹‹እግዚያብሄር ብርሃን ነው፣1ዩሐ. 1፣5፤ 1ጢሞ. 6፣16›› ከሚለው ሃይል ቃል ጋራ አመሳስለን፣ ድንኳኑ የእግዚያብሄር ማደሪያ ምሳሌ ከሆነቸው ቤተ ክርስቲያን ጋር ወክለን

ልናየው እንችላለን፤ በብረሃን ድንኳኑ ውስጥ ያለው መልከ መልካም ጎልማሳን ተሳልመው የሚሄዱት መላእክት መሰል ሰዎች፣ አማኙን ማህበረሰብ ይወክላል፡፡ ከዚህም በመነሳት የተባለው ራዕይ እውነት ሆኖ ከታሰበበት ሳይሆን እግዚያብሄር ከፈቀደበት ቦታ ላይ ባለ አስራ ሁለት በር ያለው ቤተ መቅደስ በአብረሃና ወ አጽበሐ በወርቅና በዕንቁ ታንጾ ለብዙ አመታት የእግዚያብሄር ቃል እየተነገረበት፣ የህዝብ ክርሲቲያኑ ቁጥርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ አሁን አለበት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ የዚህ ተረክ መነገሩ በማህበረሰቡ ላይ ያለውን ፋይዳ ስናይ በእግዚያብሄር ፈቃድ የተሰራች ነች ብሎ ስለሚያምን ለቅድስናዋና ክብሯ ሲል ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ያደርጋል፤ ለእምነቱም ትልቅ አክብሮት ይኖረዋል፡፡

### 5.1.8 የገዳሟን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ ተረኮች

ከላይ በተዓምራት ተረክ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በደርግ ዘመነ መንግስት ዕቃ ቤቱን ሰብረው በመግባት ውድ የሆኑ ዕቃዎችን ወደ ወታደራዊ ካምፕ በወሰዱ ጊዜ የተፈጠረ የገዳሟን ልዕልና የሚያስጠብቅ ሁነት ተፈጥሮ እንደነበር ይነገራል፡፡ በዚህ ላይ ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አባ ኃይለ ማሪያም፣መጋቢት፣30፣2011 ዓ.ም እንደነገሩኝ ከሆነ፡፡

> ከገዳሟ ዕቃ ቤት የወርቅ ጉብጉባት ያላቸው ሁለት የብራና መጽሐፍት፣ ሶስት የራስ ቁሮች እና በርካታ ስጋጃ ምንጣፎች ሌሎችም ልዩ ልዩ ንብረቶች ወስደው ነበር፡፡ ነገር ግን ስጋጃውን እያነጠፉ በሚተኙበት ጊዜ የጤና መታወክ ችግር ሲገጥማቸው ከቤተ ክርስቲያን ያመጡት መሆኑን ስለተገነዘቡ ወደ ገዳሟ ሲመለሱ ከጤናቸው እንደተመለሱ እና የወርቅ እራስ ቁሮችንና መጽሃፍቶችን ሹሞች ለመውሰድ አስበው በሂልኮብተር ጭነው ለመሄድ ሲሞክሩ የሂልኮብተሩ ሞተር አልነሳም በማለት ያስቸግራቸዋል ከዚያ ሲያስቡ ምናልባት ፊት በስጋጃው ገጥሟቸው የነበረውን የጤና እክል በማስታወስ ሞተሩም እንቢ ያለ ከነዚህ ንብረቶች ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል ብለው በመጠርጠር ካህናቱን አስጠርተው ‹‹ይሄ በስህተት የወሰድነው የገዳሟ ቅርስ ነው ይቅር በሉን›› በማለት ሲመለሱ እንቢ ያለው የሂልኮብተሩ ሞተር በመነሳት መሄድ ወደ ፈለጉበት እንደሄዱ ገልጸውልኛል፡፡



ምስል10፡- በሂልኮብተር ሊወሰዱ የነበሩት በወርቅ ጉብጉባት የተሰሩት (ከቀኝ ወደ ግራ፣ የዩሐንስ ወንጌልና የጳውሎስ መልዕክት) ሁለት ባለ ገበታ የብራና መጽሃፍት፡፡

ሌላው ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው የሚመስል የገዳሚን ልዕልና የሚያስጠብቅ ተረክ ነው፡፡

‹‹በአንድ ወቅትየ ገዳሚን ከወርቅ የተሰራ ቃጭል ተሰርቆ እንደነበር ይነገራል፡፡ ሆኖም ግን በተደረገው ሱባኤና ፀሎት መልሰው አምጥተው ከገዳሚ በር ላይ በማስቀመጥ ተመልሶ እንደተገኘ (ገብረ ህይወት፣ መጋቢት 30፣ 2011 ዓ.ም)›› አጫውቶኛል፡፡

የዚህ ተረክ መነገር ለአማኙ ማህበረሰቡም ሆነ ለሌላው ማህበረሰብ ትልቅ ተግባር /መልዕክት/ ይኖረዋል፡፡ ከተግባራቱም ውስጥ በገዳሚ ውስጥ ወይም ውጭ የሚገኙ የእሷን ሀብትና ንብረት ለመስረቅም ሆነ ለማሰረቅ እንዲሁም በጉልበት ለመውሰድ የሚያስብ ማንኛውም ግለሰብም /ቡድን/ እንደማይሳካለትና ከዚህ እርኩስ ተግባር እራሱን እንዲያርቅ የሚያስተምርና የሚያሳስብ መሆኑ አንዱ ነው፡፡

ቀጣዩ ተረክ ደግሞ በገዳሚ ጣሪያ ላይ የተጣለባት የአውሮፕላን ቦንብ ሳይመታትና ሳያቃጥላት ስለመቅረቷ የሚያትት ነው፡፡

ዓመት ምህረቱና ቀኑ መቼ እንደሆነ በግልጽ ባይታወቅም ገዳሚን ለማቃጠልና ለማውደም ፈልጎ የነበረ ጠላት አሁን ድረስ በማገልገል ከምትገኘው ከክቧ /ቤተ ንጉሷ/ ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበረች አድርጎ ማፍረስና ማቃጠል ቀርቶ ከሰማይ የወረደው ቦንብ ጣሪያውን እንኳ ሳይነዳ እንደጠጠር ኮለል እያለ መሬት ላይ እንዳረፈ (ሹምየ፣ መጋቢት 2፣2011 ዓ.ም) ነግሮኛል፡፡

የዚህ ተረክ መነገር ዋና ዓላማ ገዳሚን ለማፍረስ፣ ለማውደም፣ ለማቃጠልም ሆነ ለሌላ እኩይ ተግባር የተሰለፈ ወይም ሊሰለፍ የሚያስብ ማንኛውም ግለሰብ /ቡድን/ አይሳካልህምና አርፈህ ተቀመጥ የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም የአውሮፕላን ቦንብን ያህል ነገር አምክና ምንም ሳትሆን የቀረች ገዳም ነች ተብሎ ሲነገር የሚሰማ ማንኛውም ጠላት የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን ምንም ያህል እንኳ አቅም ቢኖረው እንደማይሳካለትና የፈለገውን ማድረግ እንደማይችል ስነ ልቦናዊ ጫና ያድርበታል፡፡

የገዳሚን ቀጣይነት፣ ደህንነት የሚያስጨንቅውና የሚፈልገው አካል ደግሞ በዚህ ተረክ ምክንያት የበለጠ ክብርና ቅድስና እንዲሁም አድናቆት ለገዳሚ ይሰጣል፡፡ ይህ ሆነ ማለት ደግሞ አማኙና ለገዳሚ ጥብቅና የሚቆሙ ሰዎች ቁጥር ይጨምራል፡፡

ስለዚህ ከዚህ ተረክ የምንገነዘበው ነገር አንድ ማህበረሰብ በተረኮቹ አማካኝነት ማጀገን ወይም ማስፈራራት፣ ማበረታታት ወይም ተስፋ ማስቀረጥ ወዘተ እንደሚችል ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ተረክ መሳሪያነት ማህበረሰቡ ገዳሚን አስጠብቆና አስከብሮ አቆይቶበታል ወደ ፊትም ያስቀጥልበታል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች

### 6.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ይዘት እና ማህበራዊ ፋይዳ ተንትኖ ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የጽሁፍ መረጃዎችን በመመልከት ቃለ መጠየቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ተኮር ውይይት በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

መረጃዎቹ በጽሁፍ ማስታዎሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ግራፍ እና በመቅረጸ ድምጽ አማካኝነት ተቀርጸዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም እንደአስፈላጊነቱ ማጣቀሻ መጽሃፍትን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

የገዳሚ ታሪካዊ አመሰራረት የሚጀምረው የአባይን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ በገቡ የነገደ ካም ወይም የኩሽ ልጆች እንደሆነና እነዚህ ነገዶች በዚህ ቦታ ላይ ለብዙ ዘመናት በህገ ልቦና እንደአባታቸው አዳም መሰዋዕት እየሰው የኖሩባት የረጅም ታሪክ ባለቤት እንደሆነች ታይቷል፡፡

በመቀጠልም በቀዳማዊ ሚኒልክ ዘመን ጎጃምን እንዲያስተዳድር የተላከው አለቃ ኤፍሬም ከሰሜን ኢትዮጵያ አክሱም ተነስቶ ጎጃም ምድር እንደገባ ርዕሰ ከተማውንም ፊት ነገደ ካም ወይም የኩሽ ልጆች ይኖሩባት ከነበረው መርጡለ ማሪያም ገዳም ላይ እንዳደረገ፣ አብረውት የመጡትን ሌዋውያን ካህናት የኦሪትን ህግና ስረዓት ጠብቀው በሀገረ እግዚያብሄር መርጡለ ማሪያም ቤተ ምኩራብ እንዲሰሩ እንዳደረገና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመነ ሀዲስ ማለትም የሀዲስ ኪዳን አብሳሪዎች አብረሃና አጽበሐ ዘመነ መንግስት ድረስ ሙሉ በሙሉ መሰዋዕተ ኦሪት እንተደፈጸመባት ተብራርቷል፡፡

ሌላው አብረሃ ወ አጽበሐ እንዲሁም አባ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን (ፍሬ ምናጦስ) አሁንም ከአክሱም ጽዮን ተነስተው በወሎ ክፍለ ሀገር አቋርጠው ወደ ጎጃም እንደተሻገሩና የአሁኗ መርጡለ ማሪያም ሲደርሱ የኦሪቱን ቤተ ምኩራብ ሲያው በመደመምና በማድነቅ ይህንን ለታሪክ መዘክርነት ትተን የሃዲስ ኪዳን ቤተ ፀሎት እንስራ እንዳሉ፣ ሆኖም ግን

የእግዚያብሄር ፈቃድ ሳይሆን የሚሰራው ቦታ የእሳት ትንታግ ቦግ እያለ እንቢ ስላላቸውና በኋላም መስራት ያለባቸውን ቦታ በሱባኤ እንደተጠቆማቸው ተመልክቷል፡፡

ገዳሟም በተለያየ ጊዜ የተለያ ስያሜ እንደነበራት የተገለጸ ሲሆን የመጀመሪያው ሀገረ እግዚያብሄር፣ ሁለተኛው ሀገረ ሰላም፣ ሶስተኛው ጽርሃ አርያም እና የመጨረሻወ /የአሁኑ መጠሪያ/ መርጡለ ማሪያም እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

በጥናቱ እንዳየነው በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ይዘትን መሰረት ያደረገ ምደባ በማካሄድ በስምንት ተከፍለው ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው የገዳሟን ጥንታዊነት የሚዘክሩ ተረኮች ሲሆኑ እነዚህ ተረኮች ገዳሟ የጥንት ተብለው ከሚጠሩ ከሌሎች ገዳማትና አድባራት በአካባቢው የመጀመሪያዋ እንደሆነች፣ ከዛሬ 3740 ዓ.ዓ በፊት ይህች ቦታ የሀዲስ ኪዳን መንገሪያና የቃል ኪዳን ቦታ እንደሆነች የሚናገሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ማህበረሰቡ ለቦታው የሚሰጠው ክብርና ዝና ቀላል እንዳማይሆን ጥናቱ አመልክቷል፡፡

ቀጣዩ ለገዳሟ የተገባላት የቃል ኪዳን ተረኮች ሲሆኑ አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን መርጡለ ማሪያም ገዳምን ባርከውና ቀድሰው በመርጡለ ማሪያም ገዳም ክልል ውስጥ እባብ ሰውን ነድፎ እንዳይጎዳና ረሃብ ቸነፈር እንዳይኖር አባታዊ ቃል እንዳሳደሩ፤ በጥር 21ቀን 333 ዓ.ም የኪዳን ጽላቱ ወደ ቤተ መቅደሱ በገባበት ዕለት ለእናታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ በመርጡለ ማሪያም ገዳም የተገባላት የቃል ኪዳን ተረክ መኖሩ ተመልክቷል፡፡

ሌላው አባ ተጠምቀ መድህን የተባሉ መነኩሴ በዚህች ገዳም እያገለገሉ ይኖሩ እንደነበርና ከፍፁምነታቸው የተነሳ ከእግዚያብሄር ጋር ቃል በቃል እንደተነጋገሩና እግዚያብሄርም ስምህን የጠራ፣ ዝክርህን የዘከረ፣ በዓልህን ያከበረ፣ ገድልህን የጻፈ ያጻፈ ሁሉ ለመንግስተ ሰማያት የበቃ ይሆናል የሚል ቃል ኪዳን እንደተገባላቸው ተጠቅሷል፡፡

እነዚህ ተረኮች መነገራቸው ማህበረሰቡን በእምነቱና በማህበራዊ ጉዳዩ ለማጽናት /ለመትከል/፣ ለመቆጣጠርና ለመግታት ግብረ ገብነትን፣ ለጋስነትን ከማስተማር አንጻር የሚጫወቱት ሚና ቀላል እንዳልሆነ ተጠቁሟል፡፡

ሶስተኛው የገዳሟን ቅድስናና ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች ናቸው፡፡ በዚህ ስር ማህበረሰቡ ገዳሟን በማክበረ እንዲንከባከብ፣ አካባቢውን እንዲወድ፣ እምነቱን አጥብቆ እንዲይዝና እንዲመለከት፣ በመንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ኑሮው ተስፈኛ እንዲሆን የሚያደርጉ ተረኮች እንደሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

አራተኛው በገዳሟ የተፈፀሙ የገቢራተ ተዓምራት ተረኮች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ዓጼ በዕደ ማሪያም አሁን በማገልገል ላይ የምትገኘውን የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን እያሳደሱ እያለ በሰሜንና በደቡብ በኩል የሚገኙ ሁለት የጥንት የወይራ ዛፎች የቤተ ክርስቲያኑን ጣራ ለመስራት ከላይ ሆነው ስለከለሉ ንጉሱ እንዲቆረጡ በአዘዙ ጊዜ በሚገርም ሁኔታ ጣሪያውን የያዘው የሁለቱም የወይራ ዛፎች ክፍል ለቆ እንደተገኘ ተዘርዝሯል፡፡

በመርጡለ ማሪያም ገዳም በተሰበሰበው ህዝበ ክርስቲያን ላይ የደርግ ጦር ሰራዊት ሊያደርሰው የነበረው ጭፍጨፋ በእመቤታችን ድንቅ ተዓምር ሳይሳካ እንደቀረና በአባ እንድሪያስ አድሮ በክፉዎች ላይ አድርጓል የተባለው ተረክን ጨምሮ ተብራርቷል፡፡

እነዚህ የተዓምራት ተረኮች መነገራቸው ማህበረሰቡ ለእምነቱ ትልቅ ክብር እንዲኖረው፣ ቅድስት ድንግል ማሪያምን አምኖ የተጠጋ ከጭንቅና ከመከራ እንደሚድን፣ ጥላና ከለላ እንደምትሆነው ለማሳሰብ እንደሆነ ወይም ደግሞ ምዕመኗን የሚዳፈር ማንኛውም ኃይል እንደማይሳካለትና ሊያደርጉ ከሚያስቡት መጥፎ ተግባር እራሳቸውን ማራቅ እንደሚገባቸው፤ ማህበረሰቡ ለሃይማኖቱ ያለው ቦታና አተያይ እጅግ በጣም ጠንካራ መሆኑን፤ ማህበረሰቡ ሀቀኛ፣ ሰው አክባሪ፣ ይቅር ባይነትን ወዘተ የሚያስተምሩ ተረኮች መሆናቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመቀጠል በጥናቱ የተካተተው ከገዳሟ መመስረት ጋር ተያይዞ የሚነገሩ ትንቢት ነክ ተረኮች ናቸው፡፡ አብረሃ ወ አጽበሐና አባ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን /ፍሬ ምናጦስ/ ከወሎ ወደ ጎጃም በሚሻገሩ ጊዜ የአባይን ወንዝ በመስቀል ባርከው ውሃው ለሁለት ተከፍሎላቸው እንደተሻገሩ እና ከገዳሟ አጠገብ ስለሚገኘው ጠበል ከዛሬ ብዙ ዓመት በፊት ተነግሮ ስለነበር ትንቢት የሚያወሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮች መነገራቸው ማህበረሰቡ የአባቶችን ቃል ምን ያህል ትክክለኛና ጠቃሚ እንደሆነ ለማስገንዘብና ማክበር እንደሚገባቸው

ለማሳየት ተፈልጎ እንደሆነ፤ አማኙ ማህበረሰብ ለጠበሉ የሚሰጠው ቅድስናና ክብር ከፍተኛ መሆን ማስቻሉን እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ከራዕይ ጋር በተየያዘ የሚነገረው ተረክ ደግሞ ቀጣዩ ነው፡፡ የሀዲስ ኪዳኑን ቤተ ፀሎት ለመስራት ሙከራ ባደረጉ ጊዜ መሬቱ እሳት እየተፋ፣ ሰራተኞችም ጤናቸው እየታወከ እንደነበርና ይህንንም ችግር ለመፍታት ሱባኤ እንደገቡና ሁሉም አንድ አይነት ራዕይ እንዳዩ የሚዘረዝር ነው፡፡ ይህ ተረክ መነገሩም ማህበረሰቡ ገዳሟ በእግዚያብሄር ፈቃድ የተሰራች ነች ብሎ ስለሚያምን ለቅድስናዋና ክብሯ ሲል ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ እንደሚያደርግ፤ ለእምነቱም ትልቅ አክብሮት እንደሚኖረው ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም የገዳሟን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ ተረኮችን እናገኛለን፡፡ የመጀመሪያው በደርግ ዘመነ መንግስት ዕቃ ቤቱን ሰብረው በመግባት ውድ የሆኑ እቃዎችን ወደ ወታደራዊ ካምፕ በወሰዱ ጊዜ የተፈጠረ የገዳሟን ልዕልና የሚያስጠብቅ ሁነት ሲሆን ቀጣዩ ደግሞ በአንድ ወቅት የገዳሟን ከወርቅ የተሰራ ቃጭል ሰርቆ የነበረ ግለሰብ በተደረገው ሱባኤና ፀሎት መልሶ አምጥቶ ከገዳሟ በር እንዳስቀመጠ እና በገዳሟ ጣሪያ ላይ የተጣለባት የአውሮፕላን ቦንብ ሳይመታትና ሳያቃጥላት ስለመቅረቱ የሚናገሩ ተረኮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የእነዚህ ተረኮች መነገር በመጀመሪያ በገዳሟ ውስጥ ወይም ውጭ የሚገኙ የእሷን ሀብትና ንብረት ለመስረቅም ሆነ ለማሰረቅ እንዲሁም በጉልበት ለመውሰድ የሚያስብ ማንኛውም ግለሰብ /ቡድን/ እንደማይሳካለትና ከዚህ እርኩስ ተግባር እራሱን እንዲያርቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ገዳሟን ለማፍረስ፣ ለማውደም፣ ለማቃጠልም ሆነ ለሌላ እኩይ ተግባር የተሰለፈ ወይም ሊሰለፍ የሚያስብ ማንኛውም ግለሰብ /ቡድን/ አይሳካልህምና አርፈህ ተቀመጥ የሚል መልዕክት እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ በርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም የሚነገሩ ተረኮች የገዳሟን ጥንታዊነት የሚዘክሩ፣ ገዳሟ እንድትከበርና እንድትጠበቅ የማድረግ፣ አማኙ ማህበረሰብ በእምነታቸው እንዲፀኑና እንዲጠነክሩ የማድረግ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ገዳሟን በማክበር እንዲንከባከብ፣ አካባቢውን እንዲወድ፣ በመንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ኑሮው ተስፈኛ እንዲሆን የማድረግ፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች የገዳሟ ጠባቂ፣ ደጋፊና ተቆርቋሪ እንዲሆኑ የማድረግ አገልግሎት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 6.2 የይሁንታ ሀሳቦች

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ስሰራ ከታዘብኳቸው ነገሮች በመነሳት የሚከተሉትን የይሁንታ ሀሳቦች /አስተያት/ ለማስቀመጥ ወደድኩ፡፡

ይህች ጥንታዊትና ታሪካዊት ገዳም ከተመሰረተች ከ3740 ዓመት በላይ እንደሆነ የቃልና የጽሁፍ ሰነዶች አመልክተዋል፡፡ ሆኖም ግን የጥንታዊነቷንና የታሪካዊነቷን ያህል የጎብኝ ቁጥር ወደ ገዳሟ ሲመጣ አይታይም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ገዳሟ ማግኘት የሚገባትን ጥቅምና እውቅና በሚገባ እንዳላገኘች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይንንን ክፍተት የፈጠረው የገዳሟ ሙሉ ታሪክ በጽሁፍ መልክ ለህዝብ ስላልቀረበና እውቅና ስላልተፈጠረ መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህንን ችግር ለመቅረፍ በተደራጀና በተሟላ መልኩ ጽሁፋዊ ማስረጃዎች ቢዘጋጁ እና ሌሎች የማስተዋወቂያ አጋጣሚዎችንና ስልቶችን በመጠቀም እውቅና መፍጠር ቢቻል ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የተሻለ እንደሚሆን ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

ስለርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ተሪካዊ አመሰራረት ከሀብታሙ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ውጭ ቤተ መጽሃፍት በመሄድም ሆነ በገዳሟ የሚገኙና ቁልፍ መረጃ አቀባየ የነበሩትን አባቶች በመጠየቅ ሌላ ተጨማሪ ስራ ስለመሰራቱ የቃል መረጃም ሆነ ጥናታዊ ጽሁፍ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህም በመሆኑ ገዳሟ ካላት የረጅም ዕድሜ ታሪክ አንጻር በቂ ነው ብዬ ስለማላምን ሙሉ ታሪኳን ሊያሳይ፣ ሊያስተዋውቅና ሊያስተምር የሚችል በሳል የሆኑ ስራዎች ቢሰሩ የሀገራችንን ታሪክ ከማስተዋወቅ አንጻር የሚኖረው ፋይዳ ቀላል እንደማይሆን ለማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡

ሌላው ይህን ጥናት በምሰራበት ጊዜ በገዳሟ ውስጥ በሀገራችን የትም ገዳምም ሆነ ቤተ ክርስቲያን የማይገኙና እጅግ ጥንታዊ የሆኑና በጣም ብዙ ከኦሪት ዘመን ጀምሮ እስከ ሀዲስ ኪዳን ብሎም እስከ አሁን ያለውን የአባቶቻችንን የረቀቀ ጥበብና ስልጣኔ ደረጃ የሚያስቃኙ በርካታ መንፈሳዊና ዓለማዊ የቁሳዊ ባህል ዓይነቶች እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በቦታው ተገኝቼ ቢያንስ ከ50 ዓመት ያላነሰ በገዳሟ ያገለገሉትን ርዕሰ ርዑሳን አባ ኃይለ ማሪያምን ጠይቄ ለማወቅ እንደቻልኩት ምንም ዓይነት ጥናት እንዳልተሰራባቸው ነው፡፡ ስለሆነም ምሁራን በነዚህ ቁሶች ላይ ትኩረት አድርገው ጥናት ቢሰሩ መልካም ነው እላለሁ፡፡

ቀጣዩ ደግሞ ምንም እንኳ የጥናቱ ትኩረት ባይሆንም ከተረኮች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሶችን ለማጥናት ስል ከላይ እንደተገለጸው ብዙዎችን የማየት ዕድሉ ገጥሞኝ ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህ ለሀገር ሀብትና የረጅም ታሪክ ባለቤት የሆኑት ንብረቶች አሁን ያሉበት ሁኔታ የቦታ ጥበት የሚስተዋልበትና ደህንነታቸውም ከረጅም ጊዜ በኋላ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ስለሚችል /ወደ ፊት ዘመናዊ ሙዚየም ለመስራት በዕቅድ የተያዘ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፡፡/ ሰፊ ቦታ ያለውና የቁሶችን ደህንነት ለአደጋ የማያጋልጥ ደረጃውን የጠበቀ እቃ ቤት ቢሰራ የተሻለ ይሆናል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

በመጨረሻም በዓባሪ ስምንት ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በወረዳው በሚገኙ ቀበሌዎች ከአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን በፊት የተሰሩ ከፍተኛ የሆነ የሀገር ቅርስና ታሪክ ሊኖራቸው የሚችል ከሰማንያ በላይ የሆኑ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም እያለን የሌለን ከምንመስል እነዚህ ቋሚ ቅርሶች ቢጠኑና ለወረዳውም ሆነ ለሀገር የሚሰጡትን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ መስጠት ቢችሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ሉሌ መልአኩ፡፡ (1997)፡፡የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኢትዩጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ማህበረ ቅዱሳን፡፡ (2005 ዓ.ም)፡፡**ሐመር ዘ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ**፡፡አዲስ አበባ፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን፡፡ (1999)፡፡ **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊትና መንፈሳዊ ህይወት**፡፡ አዲስ አበባ፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን፡፡

መሪማ መሐመድ፡፡ (2009)፡፡ ‹‹የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት፡፡››አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡

ምህረት ተስፋዬ፡፡ (2003)፡፡ ‹‹ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት፡፡›› አዲስ አበባዩኒቨርሲቲ፡፡ የኢትዮጵያ ስና ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም፣ኤ፣ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡

ምትኩ ደምሌ (መ/ር) ፡፡ (1995)፡፡ **መርጡለ ማርያም እና ታሪኳ**፡፡ የታተመበት ቦታና ድርጅት ያልተጠቀሰ፡፡

ሞገስ ጀንበሬ፡፡ (2003) "ከዳጋእስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር

ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርዓቶች፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ስና ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም፣ኤ፣ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡

ሰሎሞን ተሾመ፡፡ (2007)፡፡ **የፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡** አዲስ አበባ፡፡ፋሪ ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ፡፡

ርዕሰ ርኡሳን ቆሞስ አባ ኃይለ ኢየሱስ ገብረማርያም፡፡(2010)፡፡ **የጥንታዊትና ታሪካዊት መርጡለ ማርያም ገዳም ታሪክ** በአጭሩ፡፡ የታተመበት ቦታና ድርጅት አልተገለጸም፡፡

ቴዎድሮስ ይበልጣል፡፡ (2005)፡፡ ‹‹የደብረ ወርቅ ገዳም ማሪያም ገዳም አመሰራረት እናበገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ስና ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርትየኤም፣ኤ፣ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001)፡፡ **በይነ-ዲሲፕሊናዊ የስነጽሁፍ ጥበብ፡፡** አዲስ አበባ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

አቤል አሰፋ፡፡ (2008)፡፡ ‹‹የጣራ ገዳም፣ ዋሻ እንድሪያስ እና ዋሻ ተክለሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናትና በዙሪያው የሚነገሩ ተረኮች፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨር ሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡

እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ ቤት በቅርስ ጥበቃናቱሪዝም ልማት ቡድን የተዘጋጀ መጽሄት፡፡ (2010)፡፡ የታተመበት ቦታና ድርጅት ያልተጠቀሰ፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ (1993)፡፡ የአማርኛመዝገበቃላት፡፡ አዲስአበባ፡፡ አርቲስቲክማተሚያቤት፡፡

ወንድወሰን ሞላ፡፡ (2007)፡፡ ‹‹በጻድቃኔ ማሪያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (2005)፡፡ **የስነጽሁፍ መሰረታውያን**፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ (1980፡፡) **መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻህፍት**፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብረሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ያረጋል አበጋዝ፡፡ (2001) **መድሎተ ጽድቅ (የእውነት ሚዛን ቅጽ** 1)፡፡

----------------፡፡ (1995 ዓ.ም)፡፡ **ፍኖተ ቅዱሳን**፡፡ ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡(1962)፡፡ **ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት**፡፡ አዲስ አበባ፡፡ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታቸው አንተነህ፡፡ (2009)፡፡ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር/ነገረ ሰብ/ ጥናት ዘርፍ ለአርት ማስተርስ ዲግሪ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ማስተማሪያ ማስታዎሻ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ **የስነቃል መምሪያ**፡፡አዲስ አበባ፡፡ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፍስሀ ያዜ፡፡ (2003)፡፡ **ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ ዓመት ታሪክ (መጽሐፍ**1)፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፍፁም ኩራባቸው፡፡ (2006)፡፡ ‹‹የዝዋይ ደሰያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት››፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡

A Snell Rachel. (2017). Introduction to Material Culture Studies. Material culture /Objects-Based Research፡ Chebacco 2018.

Bascom, William. (1965). The Form at Folklore: Prose Narrative. The Journal of American Folklore: American Folklore Society.

Cantale, Claudia, et al (-29 Jun 2018). **The Shape of a Benedictine** Monastery: The SaintGall Ontology (Extended Version).c Officine culturali, Italy.

David Jules Prown.(Winterthur Portfolio,Vol.17,No.1.(spring,1982)) Mind in matter: An Introduction to Material Culture Theory and Method.pp.1-19. Currently published by The University of Chicago press.

Degh, Linda. (1972). “Oral Folklore, Oral Narretives”. In Folklore And Folklife; Richard M. Dorson(ed) Chicago And London;The University of Chicago Press.

Deluxe Encyclopedic edition (    ) **The new International_WEBSTER,S comprehensive Dictionary of the English Language.**

Durkheim, Emile. (1995). The Elementary Forms of Religious Life, New York: Free Press.

Trident Press International. (Not listed year & pleace)

Feely Catherine. (march,1996). Introduction to material culture.The Journal of material culture.

Finnagane Ruth. (1992). Oral Traditions And The Verbal Arts.Londa And Newyork: Routle dge.

Habtamu Mengiste. (1988). "A History at Monastery at Mertulamariam (1500- 1974)".Addis Ababa University: Department History,B.A Thesis.

McKENDRY EUGENE ( ) An Introduction to Storytelling,Myths and Legends:B B C Northern Ireland Learning.

(Not listed year, place& printing press.)

Mike and Cook. (2007). Doing Ethnography. Londo: SAGE Publishing:

Oring, Elliot. (1986). Folk Groups And Folklore Geners: An Introduction .Logan. Utah: State University Press.

Piotr Krzyszto Blazewicz. (xll /2/1999,31-46). **Ethiopian Monasticism.** Warsaw University. Institute of Oriental Studies.

Barthes, Roland 1975:237 ‹‹**An Introduction to the the Structural Analysis of Narrative,**›› New Literary History

Sims, Martha C. And Martine Stephens. (2005). **Living Folklore:**

**An Introduction To The Study of People And Their Tradition.**

Logan; Ohio Weslenyan University.Utah State University Press,

## አባሪዎች

### አባሪ አንድ፡- ከገዳሟ የተሰበሰቡ ተረኮች

#### ተረክ አንድ

በነበረው ክርክር መርጡለ ማሪያምን ወክለው ሲከራከሩ የነበሩት ፊታውራሪ እንድሬ ዲማ ከመርጡለ ማሪያም ይቀድማል መባሉ እንኳንስ መብለጡ መስተካከሉስ አለን? የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በረከቱ ይድረሰንና ዲማ በትክል መርጡለ ማሪያምን እንኳን ሊቀድም መርጡለ ማሪያም ስትተከል የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አባት ዞሮንቶስ አልተወለደም፡፡ በማለት የገዳሟን ጥንታዊነት ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከዲማ ጊዮርጊስ የምትቀድም ስለመሆኑ በዳግማዊ ምኒልክ ቀደምትነቷ የተረጋገጠበት ፊርማቸው ያለበት ደብዳቤ በዕቃ ቤቱ ውስጥ ይገኛል፡፡

#### ተረክ ሁለት

ሙሴና ኢያሱ ኑሯቸው እግዚያብሄርን በማመስገን በንጽህና እና በቅድስና ስለነበር ከእግዚያብሄር ጋር ባላቸው ቀረቤታ አራቱ አፍላጋት ከመነጩበት ከእጸ ህይወት ስር ጠጠሮችን ይዘው በሚንቀሳቀሱበት ቦታ የእግዚያብሄር ቃል ኪዳን ያለባቸውን የሐዲስ ኪዳን መነገሪያ ቦታዎች ላይ ሲደርሱ እነዚህ ጠጠሮች በሚለመልሙ ጊዜ ምልክት አድርገው ሀውልት እንዲያቆሟቸው እግዚያብሄር በገባላቸው ቃል ኪዳን መሰረት ከዚሀ ቦታ ሲደርሱ ይዘውት የነበረው ጠጠር ለምልሞ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ3740 ዓ.ዓ በፊት ይህች ቦታ የሀዲስ ኪዳን መንገሪያና የቃል ኪዳን ቦታ መሆኗን በትንቢት በሙሴና በኢያሱ አማካኝነት የቆመ ባለ ስድስት ገጽ ድንጋዮች ናቸው፡፡

## ተረክ ሶስት

በመርጡለ ማሪያም ገዳም ክልል ውስጥ ዛሬውኑ ሰውን እባብ ቢነድፍ በገዳሚ ቃል ኪዳን ሰለሚያምን ወደ ህክምና አይሄድም፤ በዚህ በሰጡት አባታዊ ቃል መሰረት የጋማና የቀንድ ከብቶች እንዲሁም ሳር ነጭተው ቅጠል ቀንጥሰው የሚኖሩ በግና ፍየሎች ሁሉ በውጭ ሲያድሩ የለሊት አውሬ ጅብን ጨምሮ ሳይበላቸው በሜዳ አድረው ይገኛሉ፡፡ በረዶ፣ አንበጣ፣ ቸነፈር መቸም ቢሆን በገዳሚ ክልል ውስጥ ጉዳት አድርሶ አያውቅም፡፡ ያጣ የነጣ በደጀ ሰላም ደጅ እየጠና የሚኖር ፈላሲ /ከሌላ ቦታ የመጣ/ የገዳሚ ቃል ኪዳን ስለሚጠብቀው በረሃብ አይሞትም በረድኤተ እግዚያብሄር ጠግቦ ያድራልና፡፡(አባ ኃይለ ማሪያም፣መጋቢት19፣2011 ዓ.ም) በማለት ገልጸዋል፡፡

## ተረክ አራት

እናቴ ሆይ በዓለ እረፍትሽን አስቦ ዝክርሽን የዘከረ፣ በአንች ስም ስሙን የሰየመ፣ ለተቸገረ የሰጠ፣ በዓለ እረፍትሽን ለማክበር ከሩቅም ከቅርብም ተሰብስቦ ከዚህ ቦታ መጥቶ ስጋየን የበላ ውን፣ ደሜን የጠጣውን፣ በስምሽ ተማጽኖና ባንች ታምኖ ጸበል የጠጣውን፣ በዚህ ዕለት ከደጅሽ ተገኝቶ የተማጸነውን ሁሉ ምሬልሻለሁ፡፡ እናቴ ሆይ የጎደለኝን ሙላልኝ ኑሮየን አስተካክልልኝ ብሎ በአንች ስም በሱባኤ የጠየቀኝን ሁሉ ልመናውን አሰምርለታለሁ፡፡ ይህም ቦታ ላንች የድንግልናሽ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በንጽህና በድንግልና የፀኑ ደናግል መነኮሳት ያገልግሉሽ ሲል ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ሰጥቷታል፡፡(መርጌታ ዲበኩሉ፣መጋቢት30 ፣2011 ዓ.ም)

## ተረክ አምስት

አባ ተጠምቀ መድህን የተባሉ መነኩሴ በዚህች ገዳም እያገለገሉ ይኖሩ ነበር፡፡ እነዚህ መነኩሴ ከፍጽምነታቸው የተነሳ ከእግዚያብሄር ጋር ቃል በቃል እንደተነጋገሩና ስምህን የጠራ፣ ዝክርህን የዘከረ፣ በዓልህን ያከበረ፣ ገድልህን የጻፈ ያጻፈ ሁሉ ለመንግስተ ሰማያት የበቃ ይሆናል የሚል የክርስቶስን የማይታበል ቃል ቃል ኪዳን ተቀብለው ያረፉ አባት እንደሆኑ (አባ ኃይለ ማሪያም፣ መጋቢት 29፣2011 ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

## ተረክ ስድስት

መርጡለ ማሪያም ‹‹የግራኝ እመቤት›› የሚል ቅፅል ስም አላት፡፡ ምክንያቱም በ1519 ዓ.ም ግራኝ አህመድ ወደ ስልጣን በመምጣት የክርስትናን እምነት በማዳከም የእስልመና እምነትን ለማስፋፋት በነበረው ህልም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን፣ ብዙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያናትን እና ህዝበ ክርስቲያንን ጨምሮ ሲያቃጥል፣ ሲገድልና ሲያስገድል እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሆኖም በወቅቱ የነበሩት ንጉስ አፄ ልብና ድንግል ሲሆኑ የግራኝን ጦርነት መቋቋም አቅቷቸው ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ገቡ፡፡ ልጃቸው ገላውዲዎስም በእግራቸው ተተክቶ ወደ መንበረ ስልጣናቸው መጡ፡፡ ይህን የክርስቲያን መቅሰፍት የሆነውን ግራኝ አህመድንም ለመፋለም፣ አንዳንዶቹ ራሱ ገላውዲዎስ ሲሉ ፣ ሌሎቹ ደግሞ እናቱ የልብነ ድንግል ሚስት ንግስተ ሰብለ ወንጌል ሲሉ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ሁለቱም ይላሉ፡፡ ነገር ግን እኔ ቡድን ተኮር ውይይት አወያይቸ ትክክለኛ ነው ተብሎ የሚታመነው አፄ ገላውዲዮስ ጥር 21 ቀን 1535 ዓ.ም በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም የዕረፍት በዓል መታሰቢያ ንግስ በዓል ዕለት ከቦታው ድረስ መጥቶ ‹‹ ተዋግቸ ግራኝ አህመድን ድል ብነሳው (ባሸንፈው) የኔን የክብር ልብስ፣ የግራኝ አህመድን የወግ ዕቃ፣ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ እቃዎችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ገቢ አደርጋለሁ፡፡›› በማለት ብፅዓት ገብቶ (ተስሎ) እንደሄደና በየካቲት 27 ቀን 1935 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት ግራኝ በጥይት ተመትቶ እንደሞተ፣ ገላውዲዮስም አሸንፎ በብፅዓቱ መሰረት ገቢ እንዳደረገ እና አሁንም በዕቃ ቤቱ እንደሚገኝ መጋቢት 19፣2011 ዓ.ም ከአባ ኃይለ ኢየሱስ፣አባ ኃይለ ማሪያም፣ አባ ቃለ ጽድቅ  እና ፋሲካው ደጀን (መ/ር) ገልጸውልኛል፤ በአይኔም ተመልክቻለሁ፡፡

## ተረክ ሰባት

‹‹ዓፄ ገላውዲዮስ መርጡለ ማሪያም መጥቶ ግራኝ አህመድን እንዲያሸንፍ ብጽዓት ከገባ በኋላ በህልሙ ነጭ ንብ ከመርጡለ ማሪያም ገዳም ሄዳ የግራኝን ዓይን ስትወጋው እንዳየ ከዚያም በአሸናፊነት መንፈስ ተምልቶ ወደ ጦር ሜዳ እንደሄደና በስኬት እንደተመለሰ (አባ ኃይለ ማሪያም፣ሚያዚያ 12፣2011 ዓ.ም)››ነግረውኛል፡፡

## ተረክ ስምንት

አባ ሰላማ ምንም እንኳ ቦታዋ ተስማሚና ምቹ ብትሆንም ይህ ቦታ ለእሳቸው እንዳልተፈቀደ በአብሳሪው ቅዱስ ገብርኤል አማካኝነት ተነግሯቸው ወደ ትግራይ እንደሄዱ ይታውቃል፤ ሆኖም ከመሄዳቸው በፊት ህዝቡን ሰብስበው ‹‹ልጆቼ የእጃቹህ ስራ ይባረክ፣ ሴት ወንድ ልጆቻችሁ ህግ እግዚያብሄርን የሚያከብሩ፣ በኦርቶዶክስ ሐይማኖት የጸኑ፣ ለእናት አባታቸው ታዛዥም ይሁኑ፣ ከውጭ የገዛችሁት፣ በጋጥ በበረት ያዋለዳችሁት ይርባላችሁ፡፡ የምህረት ዝናብም ይዝነብላችሁ፤ የመሬታችሁ ፍሬ ይብዛላችሁ፤ ፍቅርና ሰላም፣ ደስታና ሀሴት በሁላችሁም ላይ ይሁን፡፡ እኔ እናንተና ቦታዋን በመውደዴ ምክንያት በዚህ መኖር ፈልጌ ነበር ሆኖም ወደ ትግራይ እንድሄድ የእግዚያብሄር መላክ ቅዱስ ገብርኤል ነግሮኛል፡፡›› በማለት ህዝቡን ከመከሩና ከዘከሩ በኋላ የመለያያ ቃለ እግዚያብሄርን እያስተማሩ እያለ መሸ፡፡ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃንም ፀሀይን በእግዚያብሄር ሀይል ቁሚ ብለው አቁመው ህዝቡን እያስተማሩ ሲያቆርቡ ፈቃደ እግዚያብሄርን ተከትሎ ለሚሄድ ሰው ሁሉ ይደረግለታልና ለኖህ በቀስተ ደመና፣ ለሙሴ በሐመልማልና በነበልባ መካከል ሆኖ እንዳናገራቸው ሁሉ ለአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃንም አራት ህብር መልክ ባላት ቀስተ ደመና መካከል ሆኖ ሰላማ፣ ሰላማ፣ ሰላማ ሆይ ህግጋቱን ስረዓቱን ማስተማሩን ቀጥል፤ ያንተ አካል እንደፀሀይ ያብራ፤ፀሀይን ከስልጣንህ ማሰሪያ ፍታት፤ ወደ መግቢያዋም ትገባ ዘንድ ስደዳት በማለት እንደነገረው፣ ይህንንም ቃል ሰምተው ፀሀይን ፈቷት ፀሀይም ወደ መስኮቷ ገባች፡፡ የአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ሰውነታቸው እንደ ፀሀይ አበራ ብረሃኑም የተሰበሰቡትን ሰዎች ሁሉ ዓይን ያንጸባርቅ ነበር፡፡ (መጋቢት 18፣2011ዓ.ም)

## ተረክ ዘጠኝ

‹‹ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ አሐድር እስመ ሐረ ይክዋ›› (ትርጉም ለዘላለም መቀመጫየ ያች ያልኳት ይህች ናት በዚህ አድር ዘንድ መርጫለሁ) ብላ ነግራቸዋለች፡፡ (አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ 20፣ 2010 ዓ.ም) በማለት ጽፈዋል፡፡

## ተረክ አስር

ሆኖም ጥር 21 ቀን 333 ዓ.ም ተጠናቆ አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን (ፍሬ ምናጦስ) ቤተ መቅደሱን ባርከው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማሪያምን የቃል ኪዳን ታቦት ደናግል መነኮሳት ይዘው፣ምዕመናን በዕልልታ፣ካህናት በዝማሬ ዙረው ወደ ቤተ መቅደሱ ሲገቡ አብረሃና አጽበሐ እንዲሁም አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃንና ሌሎችም እግዚያብሄር የገለጠላቸው ቅዱሳን ሰዎች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ከታቦተ ህጉ ፊት ወደ ቤተ መቅደሱ ከልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስትገባ በግልጽ ታይታቸዋለች፡፡

## ተረክ አስራ አንድ

ከዚሁ አካባቢ የተወለደ አንድ ዲያቆን ነበር፡፡ እሱም በፀሎተኝነቱና በደግነቱ የታወቀ እንደነበር ይነገራል፡፡ በዚህም የተነሳ የሚሰወርበትም ጊዜ እንደነበር ይነገራል፡፡ በመጨረሻም ዲያቆናቱን ሰብስቦ እንግዲህ እኔ ቦታዬና ቤቴ ይህች ዕድ ነት ብሎ እየተናገረ ጓደኞችን ተሰናብቶ ከዚህ ዕድ ተሰወረ (መርጌታ ዲበኩሉ፣መጋቢት 24፣2011 ዓ.ም)

## ተረክ አስራ ሁለት

ሰለዚች ስዕል ሲናገሩ ይህች ስዕል አባታችን ጸሎተኛና ደግ ስለነበሩ ከእለታት አንድ ቀን ጸሎት አድርገው ሲጨርሱ ቀና ብለው ወደ ስዕሏ ሲመለከቱ ‹‹አባ ዘውዱ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና ዕለተ ዕረፍትህ ደርሷልና ደስታ ይገባሃል›› ብላ አነጋግራቸዋለች በዚህም ምክንያት ‹‹ኦሆ በሐሊት›› ማለትም ተናጋሪት የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷታል ዲበኩሉ /መርጌታ/የካቲት 25፣2011 ዓ.ም፡፡ ሲሉ ነግረውኛል፡፡

## ተረክ አስራ ሶስት

መምህር ፊላታዎስ ይባሉ የነበሩት የርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም 23ኛው ርዕሰ ርዑሳን በፀሎታቸው የበቁና ለእግዚያብሄር ቅርብ የሆኑ እንደነበሩ ይነገራል፡፡ እኚህ ደግ አባት ዕለተ እረፍታቸው በደረሰ ጊዜ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ቀናቸው የቀረበ መሆኑን በዚች ገዳም ቃል በቃል እንዳነጋገረቻቸው ይነገራል (ፋሲካው፣ የካቲት30፣2011 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ አስራ አራት

አባ እንጦንስ የተባሉ በገዳሚ ይኖሩ የነበሩ መነኩሴ ከደግነታቸውና ከመንፈሳዊ ብቃታቸው የተነሳ በሚቀድሱበት ጊዜ መላ ሰውነታቸው ከፀሃይ ሰባት እጥፍ ያበራ እንደነበርና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም ሁለት ጊዜ አንዴ ፀሎታቸው እንደሰመረና በመጨረሻም ዜና ዕረፍታቸውን ለማብሰር በአካል ተገልጣ እንዳነጋገረቻቸው (አባ ቃለ ጽድቅ፣ የካቲት 28፣ 2011 ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

## ተረክ አስራ አምስት

እኒህን ቅዱሳን ነገስታትና አባ ሰላማን ለመቀበል የመጡ ዐይነ ስውራን ሴቶች ዓይናቸው ስለበራላቸው ደስ ብሏቸው የእግዚያብሄር ሰዎች ናቸው ብለው ሲያደንቁ ሰምተው ‹‹ርዕያ አንስት ወ አንክራ›› ብለው ስለነበር ያቦታ ዛሬ ድርስ ‹‹ወርያ›› እየተባለ ይጠራል፡፡ ቀጥሎ ወደ ደብር መድሃኒት አምርተዋል፡፡ ከቦታው ላይ ሲደርሱ እነሱን ለመቀበል ከቤቱ ከወጣው ሰው ለምጻሞች እየነጹ፣ አንካሶች እየረቱ፣ ዐይነ ስውሮች ዓይናቸው እየበራ፣ ጎባጦች እየቀኑ፣ መስማት የተሳናቸው እየሰሙ፣ህመምተኞች እየተፈወሱ ያዩበትን ቦታ ደብር መድሃኒት ብለው ሰይመውታል፡፡ በዚህም ምክንያት ለዚህ ቦታ መጠሪያ ስም ሆኖት ‹‹ደብረ መድሃኒት›› ተብሎ እየተጠራበት ይገኛል፡፡ (17፣2010 ዓ.ም)

## ተረክ አስራ ስድስት

ዓፄ በዕደ ማሪያም ዩዲት ጉዲት /አስቴር/ ካቃጠለቻው ቤተ ክርስቲያን በስተ ምዕራብ በኩል ባለው ፍርስራሽ ላይ የቤተ ክርስቲያኑን ስራ አስጀምረው ሳለ ከዚህ መጣ ያልተባለ ዘንዶ የልጃቸውን የዓፄ ናኦድን ልጅ ማርታን ነክሶ ገደላት፡፡

ንጉሱም በእኔ ክፉ ስራ እንጅ የእሷ ሆኖ አይደለም በማለት ወደ እመቤቴ ፀሎት አደረጉ፡፡ ፀሎታቸውም ሰምሮ በእመቤታችን ትዕዛዝ አባ ኤልያስ በነፋስ ሰረገላ ከእንጦጦ ሃመረ ኖኀ ኪዳነ ምህረት ገዳም (የቀድሞዋ አሽክላ ገዳም)፣ አባ ሰርፀ ጴጥሮስ ከደብረወርቅ ማሪያም (ምስራቅ ጎጃም ከምትገኘው) በቦታው በመገኘት አባ ሰርፀ ጴጥሮስ ወደ ህጻኗ ሙት አካል በመሄድ ‹‹በአምላክ እናት በድንግል ማሪያም ስም በአባ ኤልያስ ፀሎት አንቺ ህጻን ተነሽ›› ባሏት ጊዜ እንደ ፀሃይ የምታበር እጅ በድኗን ዳሰሰቻት፤በድኑም ተንቀሳቀሰ፤ ‹‹መግነዙን ፍቱልኝ በአባ ኤልያስና በዚህ መነኩሴ ፀሎት ነፍሴ ወደ ስጋየ ተመልሳለች፡፡ ይህም በፊታቹህ የቆመው መነኩሴ የእመቤታችን የድንግል ማሪያም ወዳጅ ስለሆነ ስለዕርሱ ከሞት ዳንኩ›› ብላ ድምፅ አሰምታ ስትናገር መግነዟን ፈቱና በህዝብ መካከል አቆሟት፡፡ አባ ኃይለ ኢየሱስ፣(2010፣39-40፤ዲበኩሉ /መርጌታ/) ይላል፡፡

## ተረክ አስራ ሰባት

ዓፄ በዕደ ማሪያም አሁን በማገልግል ላይ የምትገኘውን የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን እያሳደሱ እያለ በሰሜንና በደቡብ በኩል የሚገኙ ሁለት የጥንት የወይራ ዛፎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ጣራ ለመስራት ከላይ ሆነው ስለከለከሉ ንጉሱ እንዲቆረጡ በአዘዙ ጊዜ በሚገርም ሁኔታ ጣሪያውን የያዘው የሁለቱም የወይራ ዛፎች ክፍል ለቆ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ዛፎቹ እንዲቆረጡ እመቤታችን ስላልፈቀደች ነው ብለው የሰራችውን ድንቅ ተአምር ለመግለጽ ከዚያ ወዲህ የዛፎቹን መጣመም ‹‹ግንደ አጥም ማሪያም›› ይላሉ፡፡(ፋሲካው፣ መጋቢት 30፣2011 ዓ.ም)

## ተረክ አስራ ስምንት

ከዕለታት አንድ ቀን ከደጀ ሰላም ሄደው አይኑ የጠፋ ደካማ ሰው እንዳገኙና ሊያናግሩት ቢሞክሩ ዝም እንዳላቸው፤ ጓደኞቹን ሲጠይቁ ዓይኑ ብቻ ሳይሆን ጆሮውም እንደማይሰማ ይነግሯቸዋል፡፡ ያኔ እኒህ ደግ አባት ልባቸው ተሰብሮ ለሊቱን ሙሉ በዋይታ ፀሎት ሲያደርጉ አድረው ጠዋት ላይ እምባቸውን በእፍኛቸው አምጥተው ሲረጩትና ሲዳስሱት ዓይኑም አየ፤ ጆሮውም ሰማ ብለዋል፡፡

## ተረክ አስራ ዘጠኝ

ጥር 10 ቀን 1968 ዓ.ም ከሌሊቱ ስድስተ ሰዓት ጀምሮ ቤተ መዘክሩን ሰብረው በመግባት ውድ የሆኑ ዕቃዎችን ወደ ካምፕ ጭነው ወሰዱ፡፡ ይህ አልበቃ ብሏቸው ለሊት ቤታቸውን እየሰበሩ ሲደበድቧቸው እያመለጡ ወደ ገዳሚ መጥተው የተጠለሉ ክርስቲያኖችን እየሰበሰቡ ከገዳሚ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኘው የስላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካስገቡ በኋላ በሶስቱም በር ባለ ሁለት እግር መትረየስ ጠምደው ክርስቲያኖችን ለመፍጀት የተመደቡ ወታደሮች ትዕዛዝ እየተጠባበቁ ሳለ ከህዝቡ ጋር የነበሩ በጸሎት ተግተው የሚኖሩ ከእኔ ጋር ሁለት የገዳሚ አገልጋይ ካህናት ማለትም ታዋቂ የቆሜ ድጓ መምህር የሆኑት መርጌታ ምትኩ ተገኘ እና በገዳሚ ከነበሩት መደበኛ ቀዳሽ ደናግል መነኮሳት በነባርነትና በአጽንኦት በአት የሚታወቁት ፀሎተኛው አባ ዩሐንስ ታደለ መትረየስ ከተጠመደባቸው ፊት ቆመው ‹‹የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማሪያም ከዚህ ጭንቅ ታድናለች በፍጽም እምነት ድረሽልን›› እያላችሁ ወደ አምላክ እናት አልቅሱ በማለት እኒህ አባት አወጁ፡፡ ህዝቡም አዘነ፣ እነሱም ተዘባበቱ በመጨረሻም በጦር አዛገሮቹ በመቶ አለቃ አበበና በመቶ አለቃ ምስጋናው ለተኳሾች ህዝቡን እንዲመቱ ትዕዛዝ ተሰጠ፡፡ በሶስቱም በር የተጠመዱ መትረየስ ተኳሾች በህዝቡ ላይ አነጣጥረው ሊመቱ ምላጭ ሲስቡ የሶስቱም ተኳሾች መሳሪያ መተኮስ አልቻለም፤ ወደ ሰማይ ሲሉት ይተኩሳል፡፡ ያኔ በንዴት መቶ አለቃ ምስጋናው ተኳሹን ልቀቅ ብሎ ገፍትሮ ካህናቱ ባሉበት በር የተጠመደውን መትረየስ ተቀብሎ ምላጭ ሲስብ በጦር እንደተወጋ ድምፅ አሰምቶ ወደ ኋላ ተፈነገለ፡፡ ያኔ የደነገጡ ሌሎች ወታደሮች አለቃቸውን ይዘው ወደ ካምፓቸው ሄዱ ሲሉ ነግረውኛል፡፡

## ተረክ ሃያ

አባ እንድሪያስ ይባሉ የነበረ በንጽህናና በድንግልና ተወስነው በገዳሚ ይኖሩ የነበሩ አባት ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንዱ በቅኔ ማህሌት በመገኘት ውዳሴ ማሪያም ሲያድሉ ከሚታደሉት መካከል አንዱ አንተ ውዳሴ ማሪያም ማደል አይገባህም፡፡ አንተ ኃጢያተኛ መነኩሴ ነህ እንዲያውም ልጅ ወልደሃል በማለት እንደሰደባቸውና ወደ ቤቱ ሄዶም የእሳቸውን ስም እያጠፋ እያለ የገዛ ምራቁ ትን

ብሎት ይሞታል፡፡ ያኔ ቤተሰቦቹ ከመነኩሴው በዓት ሄደው ከፉኛ ይደበድቧቸዋል፡፡ የተደባደቡትም ሰዎች ሰውነታቸው አብጠ፣ ቆሰለ፣ሁሎችም ተዝለፍልፈው ወደቁ፣ በዚህን ጊዜ ስቃዩ ስለፀናባቸው አባታችን እጅግ ደግ ሰው ተሳድቦ የእኛም እጅ ስለተላለፈ እግዚያብሄር ተቆጥቶ ነው በማለት እኒህ ጻዲቅ አባት ፀሎት እንዲያደርጉላቸው ይጠይቃሉ፡፡ መነኩሴውም ፀሎት አድርገው እግዚያብሄርን ተማጽነው ቢዳስሷቸው ሁሎችም ድነው በሰላም ወደ ቤታቸው እንደተመለሱ (አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ የካቲት 29፣ 2011 ዓ.ም) አጫውተውኛል፡፡

## ተረክ ሃያ አንድ

እሱም፣ አብረሃ ወ አጽበሐ እና አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በወሎ ህዝብ መልካም ሽኝት ተደርጎላቸው አባይ ወንዝ ደረሱ የአባይንም ወንዝ ሙሴ ህዝበ እስራኤልን ከግብጽ ይዞ ሲሄድ የኤርትራ ባህር ምልቶ አላሻግርው ቢል በያዘው ትምህርተ መስቀል ባህሩን ሲባርከው ግራና ቀኝ እንደተከፈለለት እና ህዝቡን ይዞ ባህረ ኤርትራን በደረቅ እንደተሻገረ ሁሉ አኒህም ነገስተ ኢትዮጵያ አብረሃ ወ አጽበሐና አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብረሃን ልክ እንደ ሙሴ እግዚያብሄርን በጽሎት ጠይቀው ዓባይን በመስቀል ሲባርኩት ውሃው ለሁለት ተከፍሎላቸው እንኳን ውሃ ጭቃም ሳይነካቸው በደረቅ ምድር ላይ ተሻግረው ጎጃም ምድር እንደደረሱ የጎጃምና የወሎን ህዝብ ሰብስበው ቃለ እግዚያብሄር ካስተማሩ በኋላ ከጊዜ በኋላ የጎጃምና የወሎ ህዝብ ያለ ምንም ችግር ክረምት ከበጋ በደረቅ መገናኘት እንደሚችል ተናገረው ከጎጃም ህዝብ ጋር ጉዟቸውን ጀመሩ(መርጌታ ዲበኩሉ፣ መጋቢት፣ 21፣ 2011ዓ.ም) በማለት ነግረውኛል፡፡

## ተረክ ሃያ ሁለት

‹‹ይህ ፀበል እንዲሁ በአጋጣሚ የፈለቀ ሳይሆን ከዛሬ ብዙ ዓመት በፊት እዚህ ቦታ ላይ ብዙ ሰዎችን የሚያድንና ታምራትን የሚሰራ ፀበል እንደሚፈልቅ በትንቢት ተነግሮለት እንደነበርና የትንቢቱም ቀን ደርሶ ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ጀምሮ ብዙ ፈውስን እያስገኘ ይገኛል (ፋሲካው፣ መጋቢት 3፣ 2011 ዓ.ም)›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

## ተረክ ሃያ ሶስት

ሱባኤ በገቡ በሶስተኛው ቀን ሁሉም አንድ አይነት ራዕይ አዩ፡፡ እሱም ህንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ሊሰሩ ከፈለጉበት ቦታ ግንብ በወሬ፣ /በወሬ የቀረ ግንብ ለማለት ነው/ አስራ ሁለት በር ያለው የብርሃን ድንኳን ተዘርግቶ ከውስጡ መልከ መልካም ጎልማሳ ተቀምጠ መላእክት መሰል ሰዎች ከድንኳኑ ውስጥ ካለው ሰው ላይ ሲደርሱ ሰግደው ሲወጡ ሲገቡ እያዩ ያ ባለአስራ ሁለት በር የብርሃን ድንኳን ተነስቶ ቀደም ሲል የሀዲስ ኪዳን ቤተ ፀሎት ከብሉይ ኪዳን ቤተ ፀሎት (ምኩራብ) አናጠጋጋም ወደ ተባለበት ቦታ ሄዶ ሲያርፍ ድንኳኑ ሜዳውን ሞልቶ ወደ ላይም ሰማይ ገጭቶ ሳለ እኒያ መላእክት መሰል ሰዎች እጅግ በዝተውና ሜዳውን ሞልተው ሰው በሰው እየሆኑ ከድንኳኑ ውስጥ ካለው ሰው ላይ ሰግደው ሲወጡ ሲገቡ ያያሉ፡፡ (መረጌታ ዲበኩሉ፣ መጋቢት፣18፣ 2011 ዓ.ም) ይላል፡፡

## ተረክ ሃያ አራት

ከገዳሚ ዕቃ ቤት የወርቅ ጉብጉባት ያላቸው ሁለት የብራና መጽሐፍት፣ ሶስት የራስ ቁሮች እና በርካታ ስጋጃ ምንጣፎች ሌሎችም ልዩ ልዩ ንብረቶች ወስደው ነበር፡፡ ነገር ግን ስጋጃውን እያነጠፉ በሚተኙበት ጊዜ የጤና መታወክ ችግር ሲገጥማቸው ከቤተ ክርስቲያን ያመጡት መሆኑን ስለተገነዘቡ ወደ ገዳሚ ሲመለሱ ከጤናቸው እንደተመለሱ እና የወርቅ እራስ ቁሮችንና መጽሃፍቶችን ሹሞች ለመውሰድ አስበው በሂልኮብተር ጭነው ለመሄድ ሲሞክሩ የሂልኮብተሩ ሞተር አልነሳም በማለት ያስቸገራቸዋል ከዚያ ሲያስቡ ምናልባት ፊት በስጋጃው ገጥሟቸው የነበረውን የጤና እክል በማስታወስ ሞተሩም እንቢያለ ከነዚህ ንብረቶች ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል ብለው በመጠርጠር ካህናቱን አስጠርተው ‹‹ይሄ በስህተት የወስድነው የገዳሚ ቅርስ ነው ይቅር በሉን›› በማለት ሲመለሱ እንቢያለው የሂልኮብተሩ ሞተር በመነሳት መሄድ ወደ ፈለጉበት እንደሄዱ ነግረውኛል፡፡

## ተረክ ሃያ አምስት

‹‹በአንድ ወቅት የቤተ ክርስቲያኗን ከወርቅ የተሰራ ቃጭል ተሰርቆ እንደነበር ይነገራል፡፡ ሆኖም ግን በተደረገው ሱባኤና ፀሎት መልሰው አምጥተው ከቤተ ክርስቲያኑ

በር ላይ በማስቀመጥ ተመልሶ እንደተገኘ (ገብረ ህይወት፣ መጋቢት 30፣2011 ዓ.ም)›› አጫውቶኛል፡፡

## ተረክ ሃያ ስድስት


ዓመተ ምህረቱና ቀኑ መቼ እንደሆነ በግልጽ ባይታወቅም ገዳሚን ለማቃጠልና ለማውደም ፈልጎ የነበረ ጠላት አሁን ድረስ በማገልገል ከምትገኘው ከክቧ /ቤተ ንጉሷ/ ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበረች አድርጎ ማፍረስና ማቃጠል ቀርቶ ከሰማይ የወረደው ቦንብ ጣሪያውን እንኳ ሳይጎዳ እንደጠጠር ኮለል እያለ መሬት ላይ እንዳረፈ (ሹምየ /መምህር/፣ መጋቢት 2፣2011 ዓ.ም) ነግሮኛል፡፡

አባሪ ሁለት፡- አጥኚው በመስክ ላይ መረጃ ሲሰበስብ የሚያሳዩ ፎቶዎች በከፊል፡፡



ፎቶ ቀጥር አንድ

## አባሪ ሶስት፡- ከገዳሚ የተሰሰበሰቡ ፎቶዎች




ፎቶ ቁጥር ሁለት፡- ገዳሚ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ስያሜ እንደነበራት የሚያሳየው ከገዳሚ በር ላይ የሚገኘው ጠቋሚ ፎቶ፡፡



ፎቶ ቁጥር ሶስት፡- ተዘርፈው በአስደናቂ ተዓምር ከተመለሱ ቅርሶች ውስጥ በከፊል፡፡



ፎቶ ቁጥር አራት፡- በአሁኑ ሰዓት በገዳሚ ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኙ ሶስት አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ አራተኛው አሁን በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡ (ከላይ ከቀኝ ወደ ግራ የመጀመሪያው አብረሃና ወ አጽበሐ በ333ዓ.ም ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ፍርስራሽ፣ በአጼ ሃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በ1947 ዓ.ም የተሰራው የቅዱስ ስላሴ ህንጻ ቤተ ክርስቲያን፣ አሁንም ከታች ከቀኝ ወደ ግራ አንበሳ ውድም በ892 ዓ.ም እንዳሰራውየሚነገርው አሁንም በማገልገል ላይ የሚገኘው ክብ /ቤተ ንጉስ/ የእመቤታችን ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን በመቀጠል አሁን በመገንባት ላይ የሚገኘው ዘመናዊ ህንጻ ቤተ ክርስቲያን የወረቀት ላይ ምስሉ ነው)፡፡



ፎቶ ቁጥር አምስት፡- ከገዳሟ አጠገብ የሚገኘው የፀበል ቦታ በከፊል፡፡

**ዓባሪ አራት፡-ክፍል አንድ መረጃ ለመሰብሰቢያነት ያገለገሉ ጥያቄዎች፡፡**

❖ **ስለርዕሰ አድባራት ወ ገዳማት መርጡለ ማሪያም ገዳም ታሪካዊ አመሰራረት ጋር በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ ጥያቄዎች፡፡**

1. አመነሰግናለሁ!

2. ስምዎትን ማን ልበል?

3. የስራ ድርሻዎ /ሃላፊነትዎ/ ምንድን ነው? ቢነግሩኝ?

4. የገዳሚን ታሪካዊ አመሰራረት በተመለከተ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ? በነማንስ ነው የተመሰረተችው?

5. የዚች ጥንታዊትና ታሪካዊት ገዳም አመሰራረት ከንግስት ሳባ ልጅ ሚኒልክ ቀዳማዊ ጋር የተያያዘ እንደሆነ የተጻፈ ነገር አለ በዚህ ላይ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ?

6. ስለአብረሃ ወ አጽበሐ እና ስለአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን /ፍሬ ምናጦስ/ ወደ ዚህ ቦታ እንዴት ሊመጡ እንደቻሉ ቢነግሩኝ? ከገዳሚ መመስረት ጋር የሰሯቸው ዋና ዋና ተግባራት ካሉ ቢነግሩኝ?

7. ገዳሚ በተለያየ ጊዜ የስም መለዋወጥ ያጋጠማት ገዳም እንደሆነች ከመግቢያ በሩ ላይ ያለው ጽሁፍ ይገልጻል ማን ማን ትባል ነበር? በምንስ ምክንያት ነበር?

8. መጀመሪያ ገዳሚ ልትሰራ የተፈለገው ከዚህ ቦታ ነበር? ወይስ ሌላ ቦታ ?

9. የአሁን መጠሪያዋን እንዴት ልታገኝ ቻለች?

**ክፍል ሁለት**

❖ **ከገዳሚ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮችን ለመሰብሰብ የቀረቡ ጥያቄዎች፡፡**

10. ገዳሚ በጣም ጥንታዊ እንደሆነች ይነገራል፤ ለዚህ ምናልባት ምን ጽሁፋዊ ማስረጃ አለ?

11. ስለነዚህ ሁለት ትክል ድንጋዮች የተለያየ ሰው የተለያ ሀሳብ ሲሰነዝር ይደመጣል እንዳው እናንተ የምታውቁትን ብትነግሩኝ?

12. በገዳሚ በቅዱሳን አባቶች፣በጻድቃን፣ በመላእክትም ሆነ በኢየሱሰ ክርስቶስ የተገባላት ቃል ኪዳን ካለ ቢነግሩኝ?

13. ገዳሚን ቅድስና እና ክብር የሚናገሩ ታሪኮች ካሉ ቢነግሩኝ?

14. ስለግራኝ አህመድ የክብር ልብስ እንዴት ከዚህ ቦታ ሊመጣ ቻለ?

15. በገዳሚና በገዳሚ ዙሪያ በቅዱሳን አባቶችና ቅዱሳን ነገስታት የተፈጸሙ ፈውሶችን ቢነግሩኝ?

16. በገዳሚ የተፈጸሙ የገቢራተ ተዓምራት ካለ ቢነግሩኝ?

17. ከገዳሚ አመሰራረት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ትንቢት ነክ ተረኮችን ቢነግሩኝ?

18. ከራዕይ ጋር ተያይዞ የሚባሉ /የሚነገሩ/ ነገሮች ካሉ ቢነግሩኝ?

19. በደርግ ዘመን በዚች ገዳም ተፈጥሮ የነበረ ሁኔታ እንደነበር የሚነገር ነገር አለ፣ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ?

20. ከገዳሚ አጠገብ ስለሚገኘው ተዓምረኛ ጠበል ታሪካዊ አመሰራረት እና በጠበሉ ስለተገኙ ፈውሶች ቢነግሩኝ?

**ዓባሪ አምስት፡-በገዳሚ ህግና ስረዓት መሰረት ርዕሰ ርዑሳን ተብለው እየተሾሙ ገዳሚን ያገለገሉ አባቶች ስም ዝርዝር በጊዜ ቅደም ተከተል፡፡ (ከ333 ዓ.ም-2011 ዓ.ም)**

የኦሪቱ ሊቀ ካህን ሚናስ

ርዕሰ ርዑሳን ዝክረ ማሪያም

ርዕሰ ርዑሳን ተክለ ማሪያም

መምህር ኪዳነ ማሪያም

መምህር ቢኖር

መምህር ወልደ ሴም

መምህር ወልደ ሚካኤል

መምህር ወልደ ማሪያም

መምህር እሸቴ

መምህር እንግዳ

መምህር ክንፈ ሚካኤል

መምህር ሳህሉ

መምህር ዘውዱ

መምህር ወልደ ኤወስጣቴወስ

መምህር ሀብተ ድንግል

መምህር ገብረ ሚካኤል

መምህር ፀሃይ

መምህር ክንፉ

መምህር ካሳ /ቅዱሱ/

መምህር ውቤ

መምህር ወልድ ጊዮርጊስ

መምህር አሰጋኸኝ

መምህር ፍላታዎስ

ርዕሰ ርዑሳን አባ ላዕከ ማሪያም አየለ

ርዕሰ ርዑሳን አባ ኃይለ ኢየሱስ ገብረ ማሪያም

ርዕሰ ርዑሳን አባ ወልደ ማሪያም አማረ

ርዕሰ ርዑሳን አባ ሀብተ ሚካኤል ታደሰ

ርዕሰ ርዑሳን አባ ሃይለ ማሪያም ታገለ

ርዕሰ ርዑሳን አባ ተክለ ማሪያም ባዩ


ርዕሰ ርዑሳን አባ ወልደ መድኅን ታዴ

ርዕሰ ርዑሳን አባ ገብረ ማሪያም ገረመው ናቸው፡፡

የኦሪቱ ሚናስ በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ የተሾሙ የገዳሚ የመጀመሪያው ርዕሰ ርዑሳን ናቸው፡፡

ከተራ ቁጥር 4 እስከ 23 ድረስ የማዕረግ ስሙ ቀርቶ ‹‹መምህር›› በሚለው ይጠሩ ነበር፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት የጎጃሙ ገዥ ራስ ሃይሉ ተክለ ሃይማኖት የማዕረግ ስሙ የኔ ነው ብለው ወስደውት ስለነበር ነው፡፡ ኋላ ላይም ርዕሰ ርዑሳን አባ ላዕከ ማሪያም አየለ ተከራክረው እንዳስመለሱት እና ከእርሳቸው ጀምሮ እንደገና መጠራት እንደተጀመረ (አባ ኃይለ ኢየሱስ፣ 2010 ዓ.ም፣65) ተጠቅሷል፡፡

**ዓባሪ ስድስት፡-ለመረጃ ስብሰባ በተንቀሳቀስኩበት ወቅት ለህጋዊነት ከተጠቀምኳቸው ደብዳቤዎች ውስጥ በከፊል፡፡**



ቁጥር፡አ/ቋ/ሥ/ጽ/አማ/64/11
Ref.No.

ቀን፡ 16/05/2011 ዓ.ም.

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም (IES) ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ትብብር ስለመጠየቅ ይመለከታል

መ/ር እንተነህ አየነው በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል መደበኛ ድኅረ ምረቃ ዕጩ ተመራቂ ተማሪ ሲሆን፣"በርዕሰ አድባራት ወገዳማት መርጦለማርያም ገዳም ታሪካዊ አመሰራረት፣ተረኮችና የቁሳዊ ባህል ጥናት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት መረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መ/ር እንተነህ አየነው ከጥናታዊ ጽሁፉ ጋር በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ በቤተመጻህፍታችሁ እንዲገለገል መልካም ፈቃዳችሁን እየጠየቅን፣ ለሚደረግለት ትብብርም ምስጋናችን ላቅ ያለ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

Tel + 251 0471120534

ቁጥር፡አ/ቋ/ሥ/ጽ/አማ/65/11
Ref.No.

ቀን፡16/05/2011 ዓ.ም.

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም (ILS) ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ትብብር ስለመጠየቅ ይመለከታል

መ/ር እንተነህ አየነው በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል መደበኛ ድኅረ ምረቃ ዕጩ ተመራቂ ተማሪ ሲሆን፣"በርዕሰ አድባራት ወገዳማት መርጦለማርያም ገዳም ታሪካዊ አመሰራረት፣ተረኮችና የቁሳዊ ባህል ጥናት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት መረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መ/ር እንተነህ አየነው ከጥናታዊ ጽሁፉ ጋር በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ በቤተመጻህፍታችሁ እንዲገለገል መልካም ፈቃዳችሁን እየጠየቅን፣ ለሚደረግለት ትብብርም ምስጋናችን ላቅ ያለ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

Tel + 251 0471120534

**ፎቶ ቁጥር ስድስት**

## የሰንጠረዥ ማውጫዎች

### ዓባሪ ሰባት፡-የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | እድሜ | የስራ ድርሻ | የሰጡት መረጃ ዓይነት | መረጃ የሰጡበት ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ርዕሰ ርውሳን ቆሞስ አባ ኃይለ ኢየሱስ ገብረ ማሪያም | ወ | 85 | የቀድሞ የገዳሚ ርዕሰ ርውሳን | ስለገዳሚ ታሪካዊ አመሰራረትና ስለሚነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |
| 2. | ርዕሰ ርውሳን አባ ኃይለ ማሪያም ታገለ | ወ | 70 | የገዳሚ ርዕሰ ርውሳን | ስለገዳሚ ታሪካዊ አመሰራረትና ስለሚነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |
| | | | | | | |
| 4. | መርጌታ ዲበኩሉ ዳምጤ | ወ | 65 | በገዳሚ የቅኔ መምህር | በገዳሚ ስለሚነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |
| 5. | አባ ቃለ ጽድቅ | ወ | 45 | የዕቃ ቤቱ ኃላፊ | ስለገዳሚ ታሪካዊ አመሰራረት፣ በገዳሚ ስለሚነገሩ ተረኮችና ከተረኮቹ ጋር ስለሚየያዙ ቁሶች | በመቅረጸ ድምጽ |
| 6. | መምህር ፋሲካው ደጀን | ወ | 35 | የገዳሚ ሰ/ት/ት/ቤ/ት ኃላፊ | በገዳሚ ስለሚነገሩ ተረኮችና ጽሁፋዊ ሰነዶችን በመስጠት | በመቅረጽ ድምጽ |
| 7. | መምህር ገብረ ህይወት አያሌው | ወ | 42 | የገዳሚ ሰ/ት/ት/ቤ/ት አባል | በገዳሚ ስለሚነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |
| 8. | መምህር ሹምየ አያሌው | ወ | 45 | የገዳሚ ሰ/ት/ት/ቤ/ት አባል | በገዳሚ ስለሚነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |

## ዓባሪ ስምንት፡-ከ18ኛው ክ/ዘመን በፊት የተሰሩና ጥንታዊ ታሪክ ያላቸው ቋሚ ቅርሶች

| ተ.ቁ | የቤተ-ክርስቲያኑ ስም | ከዋና ከተማው ያለው ርቀት | የሚገኝበት ቀበሌ | የሚገኝበት ጎጥ | የተሰራ በት ዓ.ም | የተሰራበት ቁሳቁስ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ቆርቆሮ | ሳር | ድንጋይ |
| 1 | አብርሃ ወአጽብሃ ቤተ መቅደስ ፍርስራሽ | - | 01 | መ/ማ | 333 | | | X |
| 2 | ደብረ መንክራት ድቦ ኪዳነ ምህረት | 15 ኪ.ሜ | 011 | ድቦ | 525 | X | | X |
| 3 | ደብረ ቅዱሳን ጃንገበያ አቡነ ገብረ መ/ቅዱስ | 5 ኪ.ሜ | 06 | ገጠር | 661 | X | | X |
| 4 | ደብረ ገነት ላይ ሚካኤል | 8 ኪ.ሜ | 018 | ገጠር | 760 | X | | X |
| 5 | ደጋኝ ኢየሱስ | 32 ኪ.ሜ | 027 | ገጠር | 1062 | X | | X |
| 6 | ማህደረ ማርያም ደብረ መድሀኒት | 20 ኪ.ሜ | 020 | ገጠር | 800 | X | | X |
| 7 | ዘቦት ገብርኤል | 5 ኪ.ሜ | 03 | ገጠር | 1700 | X | | X |
| 8 | ጎደፌ ፂዮን | 13 ኪ.ሜ | 013 | ገጠር | 535 | X | | X |
| 9 | ሽብር አምባ ኢየሱስ | 5 ኪ.ሜ | 03 | ገጠር | 400 | X | | X |
| 10 | ሌቃ መድሀኒትዓለም | 7 ኪ.ሜ | 07 | ገጠር | 800 | X | | X |
| 11 | ገዳም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | 30 ኪ.ሜ | 030 | ገጠር | 1500 | X | | X |
| 12 | ፈለገ ሰላም ጉናጉና ጊዮርጊስ | 5 ኪ.ሜ | 07 | ገጠር | 500 | X | | X |
| 13 | እግር ሰብራ ማርያም | 12 ኪ.ሜ | 019 | ገጠር | 1885 | X | | X |
| 14 | ደ/ብ/ይሳባ ማርያም | 16 ኪ.ሜ | 012 | ገጠር | 1500 | X | | X |
| 15 | ደ/መ/ይብሳና ማርያም | 6 ኪ.ሜ | 06 | ገጠር | 600 | X | | X |
| 16 | ደብረ ፀሃይ ገንቦጫ እየሱስ | 6 ኪ.ሜ | 06 | ገጠር | 670 | X | | X |
| 17 | ዝምብቲት ቁስቋም | 13 ኪ.ሜ | 013 | ገጠር | 835 | X | | X |
| 18 | ሰለልኩላ አቦ | 6.5 ኪ.ሜ | 09 | ገጠር | 1200 | X | | X |
| 19 | ደ/ብ/ዶማ ሚካኤል | 10 ኪ.ሜ | 08 | ገጠር | 1876 | X | | X |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | ደ/ብ ይብራዛ ስላሴ | 5 ኪ.ሜ | 03 | ገጠር | 1500 | X | | X | |
| 21 | መ/ሰ/እነብሬ ፋሲለደስ | 14 ኪ.ሜ | 015 | ገጠር | 1150 | X | | X | |
| 22 | ደ/ም/ የጉጭ ሚካኤል | 13 ኪ.ሜ | 014 | ገጠር | 1400 | X | | X | |
| 23 | ቀጭን አምባ ማርያም | 24 ኪ.ሜ | 021 | ገጠር | 760 | X | | X | |
| 24 | ዘወትር ጊዮርጊስ | 8 ኪ.ሜ | 022 | ገጠር | 1674 | X | | X | |
| 25 | ቆርሽ ማርያ<br>ም | 15 ኪ.ሜ | 034 | ገጠር | 1335 | X | | X | |
| 26 | ይጠፋት ጊዮርጊስ | 24 ኪ.ሜ | 021 | ገጠር | 1200 | X | | X | |
| 27 | ጉመር አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | 16 ኪ.ሜ | 016 | ገጠር | 1560 | X | | X | |
| 28 | ዛጋይ ማርያም | 10 ኪ.ሜ | 018 | ገጠር | 590 | X | | X | |
| 29 | ደምበዛ ጊዮርጊስ | 12 ኪ.ሜ | 019 | ገጠር | 700 | X | | X | |
| 30 | እነጀንበር ማርያም | 9 ኪ.ሜ | 022 | ገጠር | 680 | X | | X | |
| 31 | ደ/ኃ/ሽጓት ጊዮርጊስ | 5 ኪ.ሜ | 03 | ገጠር | 964 | X | | X | |
| 32 | ይግ ጊዮርጊስ | 30 ኪ.ሜ | 030 | ገጠር | 1400 | X | | X | |
| 33 | ይደራ ኪዳነምህረት | 20 ኪ.ሜ | 019 | ገጠር | 950 | X | | X | |
| 34 | እነገራም ጊዮርጊስ | 20 ኪ.ሜ | 016 | ገጠር | 800 | X | | X | |
| 35 | ጉንድብ ሚካኤል | 8 ኪ.ሜ | 09 | ገጠር | 1570 | X | | X | |
| 36 | ነጭየ ጨርቆስ | 25 ኪ.ሜ | 021 | ገጠር | 1600 | X | | X | |
| 37 | ዥጣ ማርያም | 30 ኪ.ሜ | 026 | ገጠር | 1500 | X | | X | |
| 38 | አህጉሮች ማርያም | 10 ኪ.ሜ | 010 | ገጠር | 1275 | X | | X | |
| 39 | አመድውሃ ጊዮርጊስ | 32 ኪ.ሜ | 027 | ገጠር | 671 | X | | X | |
| 40 | ቀግማ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | 15 ኪ.ሜ | 017 | ገጠር | 1600 | X | | X | |
| 41 | የቀንዳች እየሱስ | 15 ኪ.ሜ | 017 | ገጠር | 866 | X | | X | |
| 42 | ጎሽዱር ማርያም | 5.5 ኪ.ሜ | 033 | ገጠር | 950 | X | | | |
| 43 | የሸዋ አውነአቢብ | 11 ኪ.ሜ | 018 | ገጠር | 1300 | X | | X | |
| 44 | ይመር ሚካኤል | 25 ኪ.ሜ | 025 | ገጠር | 1200 | X | | X | |
| 45 | ኢዛና ማርያም | 32 ኪ.ሜ | 030 | ገጠር | 1333 | X | | X | |
| 46 | ጉልት አማንኤል | 11 ኪ.ሜ | 012 | ገጠር | 689 | X | | X | |
| 47 | ደ/ድ/ወርያ መስቀል | 40 ኪ.ሜ | 032 | ገጠር | 911 | X | | X | |
| 48 | ምጥ አማንኤል | 40 ኪ.ሜ | 031 | ገጠር | 1900 | X | | X | |
| 49 | ደ/ድ/ ተንታ ማርያም | 17 ኪ.ሜ | 016 | ገጠር | 1500 | X | | X | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 50 | ደርጅ ቁስቋም | 5 ኪ.ሜ | 04 | ገጠር | 1600 | X | | X |
| 51 | ጠድማ ጊዮርጊስ | 6 ኪ.ሜ | 05 | ገጠር | 1300 | X | | X |
| 52 | ገደብ ሚካኤል | 14 ኪ.ሜ | 013 | ገጠር | 1200 | X | | X |
| 53 | ከነር ኪዳነምህረት | 33 ኪ.ሜ | 027 | ገጠር | 1500 | X | | X |
| 54 | አምኙ ማርያም | 22 ኪ.ሜ | 020 | ገጠር | 870 | X | | X |
| 55 | ጭንኩር ሚካኤል | 12 ኪ.ሜ | 010 | ገጠር | 1300 | X | | X |
| 56 | ደ/ገ/እኔሳ ጊዮርጊስ | 15 ኪ.ሜ | 025 | ገጠር | 1200 | X | | X |
| 57 | ወንብያ ጊዮርጊስ | 13 ኪ.ሜ | 024 | ገጠር | 676 | X | | X |
| 58 | ጠናየ ጊዮርጊስ | 13 ኪ.ሜ | 024 | ገጠር | 676 | X | | X |
| 59 | የፈረሴ መድሀኒት ዓለም | 12 ኪ.ሜ | 014 | ገጠር | 1556 | X | | X |
| 60 | ይዶግ ማርያም | 14 ኪ.ሜ | 015 | ገጠር | 675 | X | | X |
| 61 | ጅባገሰና ማርም | 7.5 ኪ.ሜ | 09 | ገጠር | 986 | X | | X |
| 62 | አንሳ ማርያም | 7 ኪ.ሜ | 09 | ገጠር | 476 | X | | X |
| 63 | ምጥግና ማርያም | 18 ኪ.ሜ | 011 | ገጠር | 600 | X | | X |
| 64 | ይዳይ ኪዳነምህረት | 20 ኪ.ሜ | 020 | ገጠር | 1200 | X | | X |
| 65 | ይጮባት ማርያም | 30 ኪ.ሜ | 027 | ገጠር | 1500 | X | | X |
| 66 | ሸመር ማርያም | 32 ኪ.ሜ | 029 | ገጠር | 1119 | X | | X |
| 67 | ዘማን ማርያም | 10 ኪ.ሜ | 022 | ገጠር | 676 | X | | X |
| 68 | ደምበዛ ሚካኤል | 13 ኪ.ሜ | 019 | ገጠር | 790 | X | | X |
| 69 | ጉፉ ጊዮርጊስ | 5 ኪ.ሜ | 05 | ገጠር | 1800 | X | | X |
| 70 | ጉራብ ጊዮርጊስ | 35 ኪ.ሜ | 029 | ገጠር | 676 | X | | X |
| 71 | ፈያ ሚካኤል | 28 ኪ.ሜ | 026 | ገጠር | 1800 | X | | X |
| 72 | ባቁላየ ማርያም | 4 ኪ.ሜ | 05 | ገጠር | 600 | X | | X |
| 73 | ደ/ግ/ገሰስ ሚካኤል | 36 ኪ.ሜ | 031 | ገጠር | 1347 | X | | X |
| 74 | አርግዳት ቁስቋም | 10 ኪ.ሜ | 08 | ገጠር | 1500 | X | | X |
| 75 | እነጉዚ እየሱስ | 12 ኪ.ሜ | 010 | ገጠር | 675 | X | | X |
| 76 | እነጉዚ ማርያም | 12 ኪ.ሜ | 010 | ገጠር | 674 | X | | X |
| 77 | ቦናያ ማርም | 16 ኪ.ሜ | 025 | ገጠር | 1300 | X | | X |
| 80 | መርዝአራጣ ጊዮርጊስ | 27 ኪ.ሜ | 023 | ገጠር | 1250 | X | | X |
| 81 | ወረበኛ ማርያም | 27 ኪ.ሜ | 023 | ገጠር | 1470 | X | | X |
| 82 | መዝገብ እየሱስ | 20 ኪ.ሜ | 016 | ገጠር | 1150 | X | | X |

**(የመረጃ ምንጭ፡-የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት ቡድን ካዘጋጀው መጽሄት እና ከወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የተገኘና በሚመች መልክ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)**